
# የኢትዮጵያ መለኮታዊ ዕጣ

# በንግሥተ አዜብ የፍርድ ሚዛን ላይ

## የኢትዮጵያ የ"ኢካቦድ" ዘመን ይፈጸማል (1966 – 2008):

### የመጨረሻው ቀን የፍርድ ቀመር ና ግራፍ

## [59 X 260] = [42 X 365 ¼]




## 1{1፣1፣1} አቤል ጋሼ - (5/8/57-5/8/01)፡ 0(1)

# መንፈሳዊ ኢትዮጵያ ለአለም የምትገልጠው የፍርድ ቀመር።

## ሰማያዊው የፍርድ ኮምፓስ (42ኛ ዲግሪ)

አብ

ኢትዮጵያ = 5/10/6

ጽዮን (6 በ 7)

ምድያም (2 በ 21) = 42

ፍርድ “1221” (ABBA)

አዋዲ-አድዋ-አዋጅ

ሮም (12/12/12)

የኢትዮጵያ ቃል ኪዳን

(ግንቦት 20 1982– May 18, 2012)

የወልድ ሕይወት

“መንፈስ ቅዱስ ዘተአምር ኩሎ”

የአብ ሕይወት

9/11/01 - 5/2/11

9/1/24 – 9/1/66

100= አሠመ + አሰመ

“ዘእምነገደ ይሁዳ” (1924-1966)

ግብጽ (14 በ 3)

ከነዓን = (1 በ 42)

የአዳም

(የእሰራኤል ቃልኪዳን)

ኃጢአት ፍርድ

እያንዳንዱ ነፍስ በሚዛን ላይ

ወልድ

አዳም በቀደመ ክብሩ እንዲቆም፣ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ትንሳኤ መልሕቅ ነው። የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ትንሳኤ ደግሞ ፀሐይ ከምስራቅ እንደ መውጣቷ የማይገፋት ሐቅ ነው። ኢትዮጵያ ቦዘኔ አይደለችም፤ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ያልዘረጋችበት ጊዜ የለም፣ እግዚአብሔርም በእስራኤል ኃይሉን ሲገልጥ ያለ ኢትዮጵያ አላሰበውም! ኢትዮጵያን ረስቶ አስቦት የሚያውቅ ሌላ ፍጡርም የለውም። እስራኤል የጥበብ በኩር ነው፣ ኢትዮጵያ የክህነት በኩር ናት! በሁለቱ ቃል ኪዳን ውህደት የአዳም ድህነት ይፈጸማል፡ ፡

## በመልከጼዴቅ ወንበር የዘላለም የክህነት ሥርዓት የምታገለግሎ፣ የበኵር ክህነት ተወካዮች፣ በጴጥሮስ ወጳውሎስ ወንበር የተሾማችሁ፡

## የአሐቲ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ካህናት።

**“እኔ በቤተ መቅደስ በጉባኤያችሁ አብሬያችሁ እቀመጣለሁ፤ ለሰጣኋችሁ መክሊት ልጠይቅ እወዳለሁ፤ ማን አገለገለኝ? ማን በመክሊቱ አተረፈ? ማን ነው በመቅረዙ ውስጥ ዘይት ያለው? ማነው በብርሃን ውስጥ የሚመላለስ? ማነው ለነፍሱ ብሎ አለምን ፡የተወ? ኑ እንተሳሰብ። አደራዬን መልሱልኝ። በእምነት የሰጠሁት በእምነት ይመልስልኝ። እውን በእምነቱ የቆመ ከመካከላችሁ አገኝ ይሆን? ከመስዋእቴ ጎሎብኛል፣ ጾሜን ሽራችኋል፣ መቅደሴን አርክሳችኋል፣ በትዕቢት ተገልጣችኋል፤የአለምን አረም፣ ይዛችሁ ስሜን ነካክታችሁኛል። በግጻዌ ቀመር የነደፍኩትን  የአምልኮት ስርዓቴን፣ የቃሌን ክብር፣ እያቃለላችሁ ቁርባኔን አስቀርታችሁብኛል፣ የጸሎት ቤቴን ዘግታችኋል።የቃል ኪዳን ታቦቴን በስርዓት አታጥኑም። የቤቴን መዓዛ ዕጣኔን ነፈጋችሁኝ። አባቶችን ታቃልላችሁ፤ ትንሹ ኮከብ ለትልቁ ኮከብ አይታዘዝም፤ የትዕቢትን የሽቶ ቢልቃጥ በቤቴ ደፋችሁ፤ ልባችሁ ወፍሮ የትዕቢትን ዛፍ በስሜ ጎን ተከላችሁ፤ በምሕረት አደባባይ ስሜን እየጠራችሁ ነፍሳትን ታሰድዳላችሁ፤ ስሜን ተገዳደራችሁበት፣ የስድብ አንደበት በአንደበታችሁ ሰለጠነ፣ በጎቼን፣ ጠቦቶቼን፣ ግልገሎቼን  በሜዳ በተናችሁ፣ ሲቅበዘበዙ አየሁ፣ በፈራሹ የሥጋ ባሕሪያችሁ ተገልጣችኋል፣ ቁጣዬን አታንድዱት…ተመለሱ..ማቃችሁን ለብሳችሁ የነነዌን ልቅሶ አልቅሱ… እኔ ለስሜ እሰራለሁ…እናንተ ስለ አክሊላችሁ ስሩ…”የቤትህ ቅናት በላኝ።” ያለ መልአኬን እልካለሁ…ስለስሜ ክብር በጉባኤያችሁ እቀመጣለሁ… እኔ ቁጣዬ የዘገየ፣ ምሕረቴ የበዛ መሐሪ አምላክ ነኝ ….ኑ እንዋቀስ።” ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።**

## ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!

## እዚህ ጽሁፍ ላይ የተነሳው የኢትዮጵያዊ የህልውና ጥያቄ ነው። ። ለምን?

ሀ. ለምን በኢትዮጵያ የቃልኪዳን ወንበር ላይ የተቀመጡ የኢትዮጵያ ሁለት በኩሮች ማለትም ክቡር ጠ/ሚ. መለስ ዜናዊና ብጹእ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ በአንድነት በፍልሰታ ወቅት፣ በ40(ነሐሴ/ንስሐ) ቀመር ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ተጠሩ? ለምን ሁለቱም እኩል 21 ዓመት ገዝተው በ42 ዲግሪ ተፈረጁ?

ለ. ለምን በዘመኑ መጠንቀቂያ ኢትዮጵያ የክርስቶስን ልደት 2000 ዓመት ስታከብር ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰውን የንግሥት አዜብን ስም የያዙ በአለም ክብርና ሞገስ የተገለጡ ቀዳማዊት እመቤት አዜብ በኢትዮጵያ ዙፋን አካባቢ ታይተው ተሾሙ? እግዚአብሔር ምን እያለን ነበር? ሰማያዊዋ ንግሥት አዜብ (129) መቼ ትመጣለች?

ሐ. ለምንድነው በአሜሪካ ምድር የተከሰተው የ9-11 ምስጢር ከኢትዮጵያ የቅዱስ ዮሐንስ በዓል(መስከረም ፩) ጋር እንዳይለያይ ሆኖ በአንድ ቀን የተሳሰረው? “9-11 ምን መንፈሳዊ ምስጢር ይኖረው ይሆን? 5/18/12፣ 6/29/2012፤8/20/2012፤ መልዕክቱ ምንድን ነው?

መ. ለምንድን ነው እንዲሁ በ9-11 ኮድ፡ያማከለው የአጼ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን መውረድ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በመስከረም ፩ ቀን 1967 ዓመት ምሕረት (9=11) ተከውኖ የኢትዮጵያ የኢካቦድ ጀመር በዚህ አይነት የጀመረው? ለምን 42 ዘመን ላይ መንግሥታቸው ተጠራ?

ሠ. ለምንድን ነው በ81 (ሀነከ) ምስጢር የተያዘው የኢትዮጵያ ሰማያዊ የክህነት ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ ተባርኮ ለጃንደረባው የተሰጠ፣ ከዚያም በፊት መልከጸዴቅ የያዘው፣ መጥምቁ ዮሐንስ (በኢትዮጵያ 9-11 ኮድ ቅዱስ ዮሐንስ የተባለ) የጌታን ቤተሰብ ወክሎ ለእግዚአብሔር መንግሥት መክፈቻ ክርስቶስን ያጠመቀበት የክህነት ምስጢር በአለም መንፈስ ተወጥሮ የሚፈተነው?

ይኸ ጽሁፍ እነዚህን አንኳር ምስጢሮች በመንፈሳዊ እይታ የሚቃኝ ነው። መልሱ ፡የኢትዮጵያን መለኮታዊ ዕጣ ያማከለ፣ አሁን ሀገሪቱ ያለችበትን የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ተብሎ ሊታወቅ የሚገባው፣ **የ”መንግሥቱ ኃይለማርያም ደሣለኝ”** ዘመንን የ42 ዘመን (1966-2008) ቀመር የሚገልጥ የኢትዮጵያን ልብና ጭንቅላት የሚመረምር ነው። የሁሉም ኢትዮጵያዊ የህልውና ጥያቄ ነው። ሕያው ኢትዮጵያዊ ለአፍታም ቢሆን ጊዜ ወስዶ ሊያስብበት የሚገባ ነው። ቱባ ምስጢር ነው። አዎ የኢትዮጵያዊን ሁሉ የነፍስ ሕቅታ ያማከለ ነው። እግዚአብሔር ምስጢሩን ይግለጥልን!!!

## ማስታወሻ ፩

ውድ አንባቢ ሆይ፡...

1. ይኽ ጽሑፍ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው የተሰራ አይደለምና ሰማያዊ ጥበብንና ምስጢርን በብርሃን(ኡር/ዑር=46/76) ስርዓት ለሚገልጥ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው። እግዚአብሔር የሚገልጠው ብርሃን ሰሃ አይወጣለትም። ፍጹም እውነት ነው። በብርሃን መንገድ የጥበብን ልጆች የሚመራ ቅዱስ ዑራኤል ነው።
2. .ይኽ ጽሁፍ የኢትዮጵያን መንፈሳዊ ትንሳኤ ለማየት ከሚጣምን አንድ ተራ ዜጋ የተጻፈ ነው። የያዘው መልዕክት ሁኔታ አስገድዶት ጸሐፊው "እንደወረደ" ለአንባቢ አይን ያበቃው ጽሑፍ ነው። ስህተት ቢኖረው አንባቢ ስህተቱን ክቅን መንፈስ ይወስድልኝ ዘንድ በትሕትና እጠይቃለሁ። ሰው እንደመሆኔ በጣም ከስህተት ጋር የኖርኩ ስለሆንሁ አሁንም በዚህ ጽሑፍ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሰራኋቸውን ስህተቶች እንዲያርሙኝ በከፍተኛ ትህትና እጠይቃለሁ።
3. በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስማቸው ከኢትዮጵያ ዕጣ ጋር የተያየዙ ግለሰቦች ተጠቅሰዋል። ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር አምሳል ሆኖ እንደመፈጠሩ፣ ሁሉንም በአክብሮት ልጠራቸው እወዳለሁ፡፤ በዚህ ጽሑፍ ላይ የተገለጡበት ሁኔታ በኢትዮጵያ መለኮታዊ ዕጣ ዙሪያ ስማቸውና ማንነታቸው ስለተገኘ ነው። ሆኖም ጽሁፉ ስለግለሰቦች አይደለም። ይከ ጽሑፍ በሙሉ የሚያተኩረው ጤዛ ከሆነው ከሰው በበለጠ ፍጹም መንፈሳዊ በሆነ በኢትየጵያ መለኮታዊ ቃል ኪዳን ዙሪያ ላይ ነው። በሰዎች ላይ ነግሶ የሰራን መንፈስ ለመግለጽ ሰዎችን መግለጽ አስፈላጊ ነበር። ስለዚህ የማንኛቸውንም ግለሰቦች ክብር ለመንካት ጸሐፊው ምንም አላማ የለውም። የሰውንም ክብር የሚነካ ነገር ሁሉ ይጸየፋል። በዚህ ረገድ በአጻጻፍ ጉድለት የሰዎችን የሰውነት ክብር የሚነካ ነገር የተነገረ ካለ አንባቢ የአገላለጽ ችግር እንደሆነ እንዲያውቅልኝ እሻለሁ። ከወዲሁም ይቅርታ እጠይቃለሁ። ግን የኢትዮጵያን መለኮታዊ ዕጣ በተነካካ ግለሰቦች ለወሰዱት ኃላፊነት የተጠየቁበትን ሁኔታ በግልጽ መናገር፡ ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ቃየልን "ወንድምህ ወዴት አለ?" ያለው ጥያቄ የኃላፊነት ጥያቄ ነው። ሁላችንም በሰራነው ሥራና በመረጥናቸው ምርጫዎች በሃለፊነት መጠየቅ የሕይወት ሕግ ነው። የዘሩትን ማጨድ ነው። ይቅርታም እንዲሁ አብሮ የተሰራ ነው። "ተውሕቦ ምሕረት ለሚካኤል" እንላለን። ሰአሊ ለነ ቅድስት እንላለን።
4. ይኽ ጽሑፍ ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ትንሣኤ መስዋዕት የተከፈለ ነውና በገንዘብ መሸጥ የሚገባው አይደለም። ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ግን በነጻ ደርሶ የኢትዮጵያን በክብር መቆም ለማየት በሚደረገው ትግል ቶሎ ለሕዝብ አይን መግባት ያለበት ነውና፣ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ትንሳኤ የሚጓጓ ሁሉ በነጻ ለሚቀጥለው ኢትዮጵያዊ ቶሎ ያቀብለው። የኢትዮጵያ ትንሳኤ በገንዘብ አይተመንም። ለገንዘብ ቢሆን ይኽንን የጻፈው ይሸጠው ነበር።

5. የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ትንሳኤና የሥልጣኔ ሁሉ በኩር የሆነች መሆኗ ፥የሚመሰክርበት ጊዜ ፀሐይ በምሥራቅ እንደመውጣቷ የማይቀርና እሙን ሐቅ ነው። የኢትዮጵያ አምላክ ከቃሉ ዘነፍ አይልም። ነቅቷል! ይመጣል። ዘእምነገደ ይሁዳ እያገሳ ነው።

## ማስታወሻ ፪፡ የኢትዮጵያ ቃል ኪዳን... የኢትዮጵያዊ መልኩ።

የኢትዮጵያ ምድር የእግዚአብሔር ስም የሚከብርባት እንደመሆኗ፣ ማቲው ሄነሪ እንደጠራት “የእግዚአብሔር የጸሎት ግምጃ ቤት (his prayer house) ናት። “እግዚአብሔር” ሲባል፣ “ኤሎሄም” ሲባል “አላሕ” ሲባል፣ “ኢየሱስ ክርሰቶስ” ሲባል ሁሉ የኢትዮጵያዊ ምድር የእግዚአብሔር ስም መክበሪያ መሆኑ መገለጫ ነው። የዚህ ሁሉ ማሰሪያው ግን የኢትዮጵያ ቃል ኪዳን በታቦተ ጽዮን የተገለጠ የምስለ ፍቁር ወልዳ ቃል ኪዳን መሆኑን ማወቅ ነው። የኢትዮጵያ መለኮታዊ ጥበቃ የሚመነጭ ከዚህ ቃል ኪዳን ነው። በሴት የሚወከለው የኢትዮጵያ ቃል ኪዳን በወንድ ለሚገለጠው የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ለመንፈሳዊ እስራኤል መቀደሻ፣ መከበሪያ፣ መሰገጃ ነው። በሰዎች የድምጽ ብልጫ የሚወሰን ሳይሆን ሰማያዊ ሕግ ነው።

መልኩን የማይቀይር ኢትዮጵያዊ በእግዚአብሔር መመካት የሕይወቱ ብሂል የሆነ ማለት ነው። ኢትዮጵያ የምድር ቃል ኪዳን የሆነች ስለሆነች ሰላሙን የያዘ ሁሉ አገሬ ብሏት ሊኖር ይችላል። ሰላሙን የያዘ ደግሞ የራሱን ነፍስ ግዕዝነት የሚያስከብር እንጂ የሃይማኖት ወይም የፖለቲካ አብዮትና ነውጥ እየጠነሰሰ፣ ሰላምን የሚያደፈርስ አይደለም። ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን አውቆ እጁን ወደ እግዚአብሔር የሚዘረጋ ነው። ይኸ አባባል ኃይማኖት፣ ዘር፣ ቋንቋ፣..ወዘተ አይጠቅስም። የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን መሠረት ታቦተ ጽዮን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አገሪቱ በሰላም ምድርነቷ ሁሉንም የሰው ልጅ በሰላም ለሚኖሩባት አገር ምልክት እንድትሆን በብርሃን አምድ የተሰመረች ነች። ይኸ የኢትዮጵያ ሰላም መሠረት ነው። የአብርሃማዊ ሃይማኖቶች ምንጭ የዳዊት ከተማ ኢየሩሳሌም፣ የእስልምና መሠረት የተከበረው የካባ ደንጋይ ያለበት ሜካ፣ እንዲሁም የክርስትና እምብርት ታቦተ ጽዮን ናቸው። እኒህ የማይነቃነቁ የቃል ኪዳን መሠረቶች ናቸው። እነዚህን ሶስት መሠረቶች የሚያማክል ጥበብን ይዞ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሰላም ይዞ በእግዚአብሔር ምድር መኖር ማለት መልኩን የማይቀይር ኢትዮጵያዊ መሆን ማለት ነው። ለሶስቱም አብራሃማዊ ሃይማኖቶች ቤት የሆነች ኢትዮጵያ ሶስቱንም በሰላም ልታኖር ቃል ኪዳን አላት። የሰላም ምድር ስለሆነች ነው። የቃል ኪዳኗ መልሕቅ ግን የታቦተ ጽዮን ምስጢር ብሎም መስቀሉ የመሆኑ ደግሞ ጸሐይ በምስራቅ እንደምትወጣ የተገለጠ የ”ተበተ” (29) ምስጢር ነው። የፍርድ ሚዛንም የተማከለበት ነው። ኢየሩሳሌም የዳዊት ከተማ! ሜካ የታላቁ ነቢይ ሞሐመድ መሠረት እንደመሆኑ የት ቦታ ጽዮን መክበሪያ ከመሆኗ ባሻገር የቃል ኪዳኗ ዋጋ በእግዚአብሔር የስም ቀመር በግዮን ምስጢር የተሰፈረ/የተለካ ነው። ቃል ኪዳኑም ግዮን ነው። በምድሪቱ ላይ የእግዚአብሔር ስም በተለያየ መገለጫ መጠራቱ ማለትም እግዚአብሔር ፣ አላሕ፣ ኤል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወዘተ የሚያመለክተው ምድሪቱ ከአግዚአብሔር ስም ጋር በተያያዘ የተሸከመችው ምስጢር ስላለ ነው። መሰረቷ ታቦተ ጽዮን የሆነች ኢትዮጵያ ለሁሉም የሰላም እጆቿን ትዘረጋለች። ንግሥተ አዜብ ከነነዌ ሕዝብ ጋር ሆና ልትፈርድ ተነስታለች። ኢትዮጵያ ትነሳለች!

ማስታወሻ ፫ - ስለ ቀመር ስታስብ።

1. በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተገለጡትን ሰማያዊ ቀመሮች ለመስራት ከአራቱ መደቦች ያለፈ መማር የለብህም። የእግዚአብሔር መንገድ ቅንነት፣ የዋህነት ነው። አወቅሁ ማለት አይደለም። የጥበብ መጨረሻው አለማወቅን ማወቅና እግዚአብሔር ፡የጥበብ ሁሉ ባለቤት መሆኑን መገንዘብ፣ በሕይወት ጉዞም መመስከር ነው። ይኸንን ጽሁፍ ለመረዳት የሚያስፈልግህ ሁለት መሳሪያ ነው። (ሀ) ከታች በሠንጠረዥ የተጠቀሱት በግዕዝ ፊደላት የተገለጡ የጸፍጸፍ ሰማይ ፊደላትና ቁጥራቸው። (ለ) የአራቱ የሂሳብ መደቦችን (+፣ - ፣ X , /ማካፈል) እነዚህም በግዕዝና በዕብራይስጥ ሊሆኑ ይችላሉ። ትልቁና ትንሹ ብርሃን ይባላሉ። ፀሐይና ጨረቃ አምሳል መርገፍ ናቸው።

2. ለዚህ ሥራ ከዕብራይስጥ የምትፈልግ የ26 ን ምስጢር ብቻ ነው። ይኸውም የእግዚአብሔር ስም ስለሆነ ነው "YHVH" Y=10, H=5, V=6, H=5 total= 26 የሚል ነው በግዕዝ "ሀሎ ዘይሄሎ' የሚለው ለሙሴ የተነገረው ስሙ ነው። (ዘጸ. 3፡14-15) ላይ ታገኘዋለህ፡፤

3. ለግዕዝ ደግሞ 26ቱን ፊደላት ከነቁጥራቸው ተጠቀምባቸው። በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ላይ ተመልከታቸው።

ሰንጠረዥ

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ = 1 | ለ =2 | ሐ = 3 | መ = 4 | ሠ = 5 | ረ = 6 | ሰ = 7 | ቀ = 8 | በ=9 |
| ተ = 10 | ኀ = 20 | ነ = 30 | አ = 40 | ከ = 50 | ወ = 60 | ዐ = 70 | ዘ = 80 | የ = 90 |
| ደ = 100 | ገ = 200 | ጠ = 300 | ጰ = 400 | ፀ = 500 | ጸ = 600 | ፈ = 700 | ፐ = 800 | |

4. የቀመር ምሳሌ። እግዚእ ወይም ጌታ የሚለው 360 ዲግሪ ነው። ለምን ብትል፣ አ=40፣ ገ=200፣ ዘ=80፣ አ=40 በድምር 360 ይሆናል፡፤ የክብ መለኪያ ነው።

ክብ ባየህበት ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም ታስባለህ። ኢትዮጵያም በ"ክብ" ምስጢር መነደፏን አትርሳ "ዘፍ. 2፡13 ላይ ትሰማዋለህ። ቃል ደግሞ ሥጋ የሆነ፣ ከድንግል ተወልዶ ምሕረትን በመስቀል የሠራ ነው። "ተ" ን ፊደል ተመልከት መስቀል ነው። 'ቃል የሚለውን ውሰድና ቀምረው "ቀ=8፣ ለ=2 በድምር 10 ነው። ከ "ተ" ፊደል ጋር የተስማማ ነው። የራስህን ቅርጽ ተመልከተው። ሁለት እጅህን ዘርግተህ ቀጥ ብለህ ቁምና ራስህን እየው። መስቀል ነህ። በመስቀል ቅርጽ የሰራህን አምላክ መካድ፣ አንተ በመስቀል ቅርጽ የተሰራህ መሆንህን መካድ ነው።

5. ግዕዝ ስትቀምር በግንዱ ነው። ግንዱ የምልህ 26ቱን ከላይ በሠንጠረዥ የተሰጡትን ነው። የዘላለም የብርሃን አምድ የ"ብሔር" አምድ ናቸው። ብሔር (18)፣ ቀመር (18) ናቸው። የእግዚአብሔር ማደሪያው ለማለት ነው። እነዚህ የግንዱ መገለጫዎች ግዕዝን በሰባት ስታግዝ (ስታራባ) ከምትፈጥራቸው የፊደል ቅጠሎች የተለየ ባህሪ አላቸው። ቅጠል ይበቅላል፣ ይረግፋል፣ ይተካል። ግንዱ ግን ሁልጊዜ ቋሚ ነው። ግን ግንዱ እኮ "እኔ የወይን ግንድ ነኝ" ያለ "እግዚእ" ነው። ለማንኛውም ግዕዙን ለቀመር ተጠቀም። "ቃል" የሚለውን "በ "ቀለ" አስበው።

## ማስታወሻ ፬፡ መልኩን ያልቀየረ ኢትዮጵያዊ

የኢትዮጵያዊ መልኩ ለአምልኮ እጅን ወደእግዚአብሔር መዘርጋቱ ፣ በፍቅር ከሁሉም ሰው ጋር ሰላምን መያዙ ነው። ይኽ መንፈስ በውስጡ የሌለ ከእግዚአብሔር ፊት የራቀ፣ ኢትዮጵያዊ መልኩን የቀየረ ኢትዮጵያዊ ነው። ከዚህ በመንደርደር……

እግዚአብሔር በፊትህም ያቆመልህ ሰው (ማንም ይሁን ማን ) እግዚአብሔር “በመልካችን እንደ ምሳሌያችን” ብሎ የፈጠረው እንዳንተ ክቡር ፍጡር ነው። ማንም ይሁን ማን ሰውን ውደደው፣ አክብረው፣ አገልግለው። መውደደህ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ማክበርህ ነው። ማክበርህ እምነትህን መግለጥህ ነው። ማገልገልህ የመክሊትህ መገለጫ ነው። ሰውን ክብሩን አትንካው፣ ይጠላሃል፤ ክብሩ፣ ማንነቱ፣ ሃይማኖቱ፣ ስብዕናው፣ ሥጋውና መንፈሳዊ መገለጫዎቹ ናቸው። ብዙ ሳትጨነቅ፣ ለራስህ ክብር ምን ማለት እንደሆነ አስብና ለሌላውም ሰው አንተ ለራስህ የምትጨነቅለትን ያህል ክብርና ስብዕና እንዳለው አውቀህ፣ ለአንተ የምትፈልገውን ለሱም እንደሚገባው አስብ፤፡ የሁለተኛው ህግ አስኳሉ ይኸው ነው። ጎረቤትህን እንደራስህ ውደድ የሚል። ለዚህ ሁሉ የባሕሪህ መገለጫ ትሕትና ነው፡ በሙሴ እየው፣ በድንግል ማርያም እየው። ከሁሉም በላይ የፈጠረውን ፍጡር፣ ዝቅብሎ እግሩን ያጠበ የክርስቶስን ትሕትና ተመልከት። ብዙም ጠቢብ መሆን አያስፈልገውም። አንተ ፍጡርና ባዶ፣ እግዚአብሔር ግን ሁሉን ማድረግ የሚችል መሆኑን እወቅ፣ ሁሉን የሚያውቅ አምላክ መሆኑን ሁልጊዜ የሕይወትህ መርሆ አድርገህ በሕይወትህ ውስጥ መተግበር ማለት ነው። የትሕትና መልሕቅ ይኸው ነው። “ፈሪሀ እግዚአብሔር”!!! ትሕትናን መኖር ካልቻልህና ምስጢሯ ጥልቅ ከሆነብህ ትዕቢትን ሞክራት….ከከፍታ መውደቅን ታስተምርሃለች፡፤ ትዕቢት ይዞህ ወድቀህ ከተነሳህ የተነሳህበት ምስጢሩ ትሕትና ናት። በሰማያዊ ይኽ ሞቶ የመነሳት ምሳሌ ነው። በህግም ደግሞ አይዛነፍም። ሕግ በትሕትና ውስጥ ሲገለጥ፣ ትዕዛዛትን ማክበር ማለት ነው። ከፈለግህ ሕጉን ስበረውና ሞክረው፣ መልሶ ሲሰብርህ ትሕትናን ትማራለህ። ሕጉን ሰብረህ መልሶ ሳይሰብርህ ራስህን በክብር ቆመህ ካገኘኸው። “እግዚአብሔር ኃጢአቱን የማያስብበት ሰው ብጼዕ ነው” ስለሚባል ነው”” ምሕረቱ የበዛ፣ ቁጣው የዘገየ፣ ቸርና ይቅር ባይ ስለሆነ!!!

# መልዕክተ ኢትዮጵያ

# ይድረስ መልኩን ለማይቀየር ኢትዮጵያዊ!

**ማሳሰቢያ፡ ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ፡-**

**ይህ ደብዳቤ ለአንድ በስራቸው ሕያው ለሆኑ፣ ነቢዩ ኤርምያስ ቢያገኛቸው “ይኸ መልኩን ያልለወጠ ኢትዮጵያዊ” ለሚላቸው አንጋፋና ባለታሪክ ለወገን መስዋዕት ለሚሆኑ ኢትዮጵያዊ የተላከ መልእክት ነው። ለአንድ ሕያው ነፍስ የተነገረ ለሁሉም ሕያዊ ኢትዮጵያዊ የተጻፈ ..ይሆናል። ኢትዮጵያን አማክለው ለኖሩ ታላቅ አባት በመጻፍ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ መልእክት ለማስተላለፍ የታቀደ ጽሁፍ ነው። ኢትዮጵያዊ መልኩ አንድ ነው። ኢትዮጵያዊ መልኩን አይለውጥም… የኢትዮጵያዊ መልኩ ደግሞ እግዚአብሔርን ማመስገን መቻሉ ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያዊ ብሂል አዳማዊ ነው።** “ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር” አዎን ነቢዩ ኤርምያስ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ሲል.....ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያመሳስለውን የቅንነት፣ የሰላማዊነት፣ የመባረክን የመቀደስን መንፈስ ተላብሶ ራስን የመሆንን ብሂል ነው። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ያለው የሕያው ነፍስ መገለጫ ነው።**ኢትዮጵያዊ በእግዚአብሔር ቃል የጸና ነው። ኢትዮጵያዊ እግዚአብሔርን ይታመናል፡ “እግዚአብሔርን ይመስገን” መገለጫው ነው፤ እግዚአብሔር መመኪያው ያደርጋል፣ እግዚአብሔር ያውቃል ይላል፤ ለሁሉም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይጠብቃል፤ የኢትዮጵያዊ ፈተና የኢትዮጵያዊን ሰው የሚቸረውን ያይደለ እግዚአብሔር በበረከቱ የሚያላብሰውን መንፈሳዊ ነጻነት አውን ሲሆን ማየት። የግዕዝ መንፈስ መመለስ አለበት፣ የአክሱም ጽዮን ክብር በቦታው ልቆና ደምቆ መታየት አለበት። ለሰው ነጻነቱን የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው። ለሰው ሰው ምንም አይሰጠውም። “እኛ ኢትዮጵያውያን ለእግዚአብሔር እንጂ ለማንም አንሰግድም።” (አንድ ለናቱ።)**

**አዎ ይኸ ጽሁፍ በፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በኩል የተላከ ውስጠ መልእክቱ ግን ለሁሉም የሀገሬ ልጅ፣ ለኢትዮጵያ ልጅ ነው። <u>አዎ ኢትዮጵያዊ ማለት በኢትዮጵያ ቃል ኪዳን ፊቱን የማያዞር፣ ነቢዩ ኤርምያስ በመንፈስ ቢያየው “መልኩን የማይቀይር” በጋዛ መንገድ ቢጓዝ ፊልጶስ ሲያገኘው ኢትዮጵያዊው የሚለው ማለት ነው።መልኩን የማይቀይረውን ኢትዮጵያዊ ታላቁ ነቢይ ሞሐመድ ቢያገኙት ‘ይኸ ኢትዮጵያዊ የሰላም ሰው” የሚሉት ነው።</u> ይኸ ኢትዮጵያዊነት የአለም እንቶፈንቶ፣ የፖለቲካ ማስቲካ፣ የሆድ አምልኮ የሚስለው በጠፊው በስጋ ምድብ የተፈረጀ አይደለም። ኢትዮጵያዊነት በገንዘብ የማይገዙት፣ የእግዘአብሔር ጸጋ የሚያላብሰው በስብዕና ውስጥ የሚፈስ፣ የመንፈሳዊ ነጻነት ብሂል ሲሆን የሚገለጠው፣ በቅንነት፣ በትሑትነት፣ በሰላም ወዳድነት፣ በእንግዳ ተቀባይነትና፣ ለሀገርና ለወገን ቀናኢ በመሆን ነው። ይኸ ሁሉ ተጠቃሎ በአንድ ይታሰራል። ኢትዮጵያዊ መመካቱን በእግዚአብሔር ያደረገ እጁን ወደ እግዚአብሔር የዘረጋ ነው። አዎ ኢትዮጵያዊነት የልብ አሻራ፣ የሕሊና ባንዲራ፣ የነፍስ አምደ ብርሃን ነው። ኢትዮጵያዊነት ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ሕይወት ነው። ላወቀው ኢትዮጵያዊነት ሰማያዊ አክሊል ነው!!!**

## ይድረስ በጣም ለማከብርዎ፣ ኢትዮጵያዊው ስምዖን

## ታላቅ አባትና፣ መምሕር፣ የሀገር አዛውንት

## ክቡር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም።

በቅድሚያ በልዑል እግዚአብሔር ስም የከበረ ሰላምታ አቀርባለሁ። ከልብ የመነጨ አክብሮት አለኝ። በምድረ በዳ እንደ ዮሐንስ መጥምቅ ለሚጮሁት ጩኸት እግዚአብሔር ይክፈልዎት!

እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት እስከ መጨረሻው ሕቅታ የሚናገር ነው። ይኸ የግዕዝ መንፈስ ነው። ይኸንን ለተከታይ ትውልድ አርኣያ ሆነው ስምዎን ከመቃብር በላይ አውለዋል። እግዚአብሔር ይስጥልን። አዎ እንደ እርስዎ ያለ ቀናኢ ኢትዮጵያን ኢያሳጣት።

ከታላቅ አክብሮትና ትሕትና ጋር አሁን የተሰማዎት የጠለቀ ሃዘንና ንዴት አሳስቦኝ የምትከተለዋን ሀሳብ ልሰነዝር ፈለግሁ። የደረሰብዎትን በደል፣ ሥቃይና መገፋት ባውቅም ኢትዮጵያዊ ደግሞ "የኢትዮጵያን ታሪክ መክሸፍ" ሊያስበውም አይገባም እላለሁ… የኢትዮጵያ ልጆች አድዋ፣ ማይጨው ያለቁት..የእግዚአብሔርን ተስፋ ይዘው፣ በኢትዮጵያ አምላክ፣ በእስራኤል አምላክ ተስፋቸውን እንደያዙ ነውና… ንዴትዎን ወደ ተስፋ መቁረጥ እንዳያሻግርዎት አስብልዎታለሁ። ኢትዮጵያዊ እኮ መልኩን አይቀይርም… ይኸ ማለት በእግዚአብሔር መታመኑን ለማለት ነው። አዳምን "በመልካችን እንፍጠር" ያለ ኤሎሂም ለአላማ ያስታቀፈን በአዳማዊ ብሂል እግዚአብሔርን መምሰል የሕይወት ተልዕኮ አድርጎ ነው። ፈጣሪ መምሰል የአዳም ተልዕኮው ነው…እግዚአብሔር አዳምን እንደፈጠረው በፈጣሪ አምሳል ሆኖ እግዚአብሔርን በነፍስ ማምለክና ለሰው ልጅ የሕይወት አላማ ምልክት መሆን ለኢትዮጵያ መሬት የተሰጠ ዕጣ፣ የኢትዮጵያዊም ዕጣው ነው። እግዚአብሔርን መምሰል፣ በእግዚአብሔር መታመን፣ እግዚአብሔር፡ያውቃል ማለት፣….

አባቴ ሆይ አይዞዎት! ፈተናዎን እግዚአብሔር ይሰማል፣ የኢትዮጵያ ልጅን ልቅሶ እግዚአብሔር ይሰማል። ሁሉም ስለጊዜው ቀመር ነው። በአሞጽ ፱፡፯ የተነገረልን የእግዚአብሔር ልጅነት ማተባችን ነው። "የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር።

በሽምግልና ዘመንዎ የሚደርስብዎት የማይለካ፣ የአካል፣ የአእምሮ፣ የነፍስና የሕሊና ፈተና የኢትዮጵያ ስምዖን ለመሆን ስለታጩ ነው። (ሉቃ 2). በእርስዎ ፈተና ውስጥ፣

የደረሰብዎትን የሽምግልና እንግልት ሳስበው የኢትዮጵያም መለኮታዊ ዕጣ ገዝፎ ይታየኛል። ግን ሁሉም ለበጎ ነው። የኢትዮጵያ ትንሳኤ አሁን ነው። የአግዚአብሔር ትንቢት ያሰበውን ሳያደርስ ሰይፉ ወደ አፎቱ ተመልሶ አያውቅም እግዚአብሔር አያፍርም።

አይዞዎት!!!

አዎን "የኢትዮጵያ ታሪክ ሲከሽፍ" ብለው ምን ያህል ልብዎ እንዳዘነ የገለጡበትን ጽሁፍ አይቻለሁ። "ቁም....." ብሎ ኢትዮጵያዊነትን የሚፈትን ማሰጠንቀቂያ ስለሚሰጥ ልብ ያቆማል። ምን ያክል እንደተጎዱ ይገለጣል፡፡ አዎን ኢትዮጵያም ምን ያህል እንደተጎዳች ሕያው ነፍስ ሁሉ ያውቃል። ልክ ነው። መከራችን በዝቶአል፣ "የራሔል እንባ በራማ እንደተሰማ፣ የኢትዮጵያ ዕንባ መቼ ነው የሚሰማው ይሆን?" ብለው በልብዎ እንደሚያነቡ አውቃለሁ። ልክ ነው ተስፋ ቀጽቦብናል፤ ወንድም በወንድም ላይ ጨክኗል። መልካችን ርሃብ ሆኗል፤ ጨካኞች ሆነናል፣ ሰው ለሰው ተኩላ ሆኖአል...ልክ ነው የውጭ ጠላት መለኮታዊ ቃል ኪዳኗን መንካት ያልቻለውን በሶሻሊዝምና በኮሚኒዝም አለቅት፣ በምሥራቃዊነትና በምዕራባዊነት የባዕድ፡አምልኮ ኢትዮጵያን አስጨንቀናታል፣ አራክሰናታል። ልክ ነው አዛውንትተን አቃለናል..ልክ ነው ሀገራችንን በድለናል...ልክ ነው የእግዚአብሔርን ስም አጉድፈናል! (ሎቱ ስብሐት!) ልክ ነው የሕዝባችንን አደራ በልተናል።... ሁላችንም!

በዚህም ምክንያትም ኢትዮጵያ በነጻነት እግዚአብሔር የሚመለክባት ምድር አልሆነችም፤ ከእግዚአብሔር አምልኮ፣ ወደ ሥጋ (ለተነ = 42) አምልኮ፣ ወደ አለም አምልኮ እንድትወርድ ተገደደች፣ የገንዘብ መንፈስ ሰፈነ፣ የቤተ ክርስቲያን መንፈስና፣ የባቢሎን መንፈስ ሕብረት ፈጥረው ጎን ለጎን ተቃቅፈው ተገለጡ።እውን ክርስቶስ ከቤልሖር ጋር ሕብረት አለው?...የተዋሕዶ ምስጢር ክርስቶስ ተሳደደ፣ የሴቲቱ ስደት ተገለጠ፣ ኢትዮጵያ የሰላም ምድር ናት ብለው የመጡ፣ ነቢያት መስክረውላቸው ኢትዮጵያን ሀገሬ ያሉ፣ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ምድር ሰላምን የሚፈልጉ እየተሳደዱ ነው። ይኸ ግን ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡

አዎን የሁለት አለም ስደተኞች ሆነናል... ኢትዮጵያ ሆነን አሜሪካ ይናፍቀናል... አሜሪካ ሆነን ኢትዮጵያ ሕልም ትሆንብናለች... አዎን አሁን እርስ በእርስ ተጠማምደን በአንድ ለአምስት በጥርጣሬ ተጠባብቀናል። "አብረንም ብንሆንም ተለያይተናል።" ብሎናል ነፍሱ የጣመነች ኢትዮጵያዊ። በዚህ ሁሉ ግርግር መካል ግን የኢትዮጵያ መለኮታዊ ትንሳኤ ቀመር አለበት። ለዚህም ነው የርስዎ ማሳሰቢያ ሕያው ኢትዮጵያዊ የሆነን ሁሉ ልብ የሚያቆመው። አዎን ቆም ብሎ ማሰብ ያሻናል፣... ማንነትን ማጠየቅ ኢትዮጵያዊነትን ማጠየቅ... አክሱም ደቡብ ሰሜን፣ ምሥራቅ ምዕራብ የሚል ክፍፍል

የለውም፤ የማይከስመው፣ የጽዮን ታቦት ጠባቂ ምልክት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ነው። ለሁሉም ኢትዮጵያዊ መሆኑን ማወቅ ኢትዮጵያን ማክበር ነው። አክሱም ለሰሜን ልጅም ለደቡብ ልጅም ሰማያዊ ሐብት ነው። ገና ከአራቱም የምድር ማዕዘን ተደምመው መጠው ያዩታል!!! አክሱም ለኢትዮጵያዊ ሁሉ ሕይወቱ ነው። አክሱም ሀገሩ የሆነ፣ አባይን ሳይዝ አይሆንም፣  ግን ደግሞ አክሱም የኔ አባይ ግን የኔና የእናንተ የሚል የተከፈለ መንፈስ የሚያራምድ አስተሳሰብ የኢትዮጵያዊነትን ቃል ኪዳን፣ በአንድነት የሚጸናን የግዕዝና የነጻነት መንፈስ ይኀለዋል። ኢትዮጵያዊ በአለም መንፈስ፣ በሥጋ አስተሳሰብ እያሰበ፣ ሰላምን ሳይዝ፣ በወንድሙ ላይ ጦርን እየመዘዘ የኢትዮጵያን ቃል ኪዳን ሊያከብር አይችልም። እግዚአብሔር የማይወደው ኢትዮጵያዊ መልክ ሰላምን የማይፈልግ፣ በጦር የሚያምንና፣ የሰውነትን ክብር ጠልቶ ልቡሰ-ሥጋ የሆነ ነው። እግዚአብሔር የማይወደው ኢትዮጵያዊ የምድሪቱን የቃልኪዳን መሰረት የሚወጋ ነው። የወንድሙን ደም በእጁ ላይ እያሳየ ኢትዮጵያዊ ለመሆን መሞከር አስኳሉ የፈሰሰ እንቁላል መሆን ማለት ነው። ሰላምን የሚይዝ ኢትዮጵያዊ ደግሞ እንኳን የሀገሩን ልጅ ለባዕዳ ለስደተኛ የሚመች፣ "ቤት የእግዚአብሔር" ብሎ የሚቀበል ነው። ኢትዮጵያዊ የሚታወቀው ያለውን ተካፍሎ በመብላቱ ነው። "what is yours is mine; what is mine is not even negotiable" "የአንተ ለኔ ይገባኛል፤ የኔን ግን እካፈላለሁ ብለህ አታስብ።" የሚል ከኢትዮጵያ ልጅ የማይታሰብ የግለኝነት መንፈስ ነው። አክሱምም፣ አባይም፣ ሶፎ ኦመርም፣ ላሊበላም፣ አርባምንጭም፣ አፋርም የኢትዮጵያ ምስጢር ነው። አረ ይኸ የአእመረ (ሰማያዊ ጥበብ) ምስጢር ነው።  የግዕዝ የነጻነት ምስጢር ነው፡፡

የኢትዮጵያ የቅድስት ድንግል ማርያም የአስራት ሐገር ስለሆነች በተሰጣት ቤተ መንግሥትንና ቤተ ክህነትን ያማከለ ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል። በነሐሴ 2004 በፍልሰቷ መታሰቢያ የተተወነው ሁለቱን የቃል ኪዳን ወንበር ላይ የተቀመጡትን ሁለት የሀገሪቱ በኩሮች የጠራ የፍልሰት ሥርዓት ለኢትዮጵያ ብሎም በማቴዎስ ፲፪፡፵፪ ፡የተጠቀሰውን ንግሥት ኣዜብን ትንቢት ለሚጠብቅ መልዕክት ነበር። የአውሬው (666) መንፈስ ስግደትን ከእግዚአብሔር ቀምቶ ለሰው ሊያደርግ ግዛቱን የገለጠበትን ሂደት የእግዚአብሔር አይን እያየው ነው። እውነተኛውን የእግዚአብሔር ኃይል ማን ያቆመዋል? የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ማለቅ አለበት። ክብር ለኢትዮጵያ መመለስ አለበት። ኢትዮጵያ ትንሳኤዋ አሁን ነው። እየተከወነም ነው። አጫጁ መኸሩን ሊሰበስብ መላእክተኞችን ልኮአል።

የባቢሎንን ግንብ ገንብተን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ፈተና ላይ ጥለነዋል። ግን የዳቦው ግንብ (Food Security) በጽዮን ታቦት ምስጢር በ29 ቀመር በ58 ኮድ ፈርሷል። በዘፍጥረት ፫ ላይ የተጠቀሰው ሄዋንን በምግብ ያሳተው እባብ ምስጢር አለበት፤ ብሎም በዘፍጥረት ፲፩ የተጻፈው የባቢሎን ግንብ ምስጢርም ለዚህ ምልክት ለሚፈልግ ትውልድ

የተላከ ነው። እባብ የሚለው በግዕዝ ቀመር 58 ነው። የተናገረው መንፈስ 58 ነው። ትዕዛዙን የሰጠ ሰማያዊ አባባ ነው፣ 58 ነው። “ABBA” (አባባ) የአሌፍ-ቤት ብሂል(1221) በማያ ካሌንደር የ26000 የሰው ልጅ ዘመን አክሲስ (spiritual axial precession) የቀየረበት ቱባ መንፈሳዊ ምስጢር ነው። (በቀመር ሶስቱም “ማለት፣ አባባ፣ እባብ፣ አበበ የሚሉት ግዕዛዊ መሰረታቸው “አበበ” የሚል ነው፤ አ=40፣ በ=9፣ በ=9 ድምር=58 ነው።)

በ42ኛ የአዜብ ፍርድ ምስጢር የተተገበረው የፍልሰታው መልዕክት በ ግዕዝ ቀመር በ “ሀ=ሐ=ኀ” የተከወነው መሐላ (ሄኖክ 20) ምስጢር ነው። ግዕዝ የኢትዮጵያ ሕይወት ነው። የንግሥት አዜብ ፍርድ በ5/8/12 ተገልጧል፤ ቀዳማዊት እመቤት አዜብ የአለም መንፈስ ማለቁን ሊመሰክሩ በስማቸው ዕጣ በተገለጠ የታቦተ ጽዮን ምስጢር በ (100 + 29) ኮድ በዘመኑ መጨረሻ የተላኩልን ምልክት ናቸው። በምትካቸው ግን እውነተኛዋ የኢትዮጵያን ክብር በቦታዋ የምትመልሰው ንግሥት አዜብ በ42 ዲግሪ ቀመር ተነስታ ፍርዷን እየገለጠች ነው። የኢትዮጵያ ክብር ወደ ቦታው ይመለሳል፡፡ ሶስት የሄኖክ ዘመን የቀረው የኢካቦድ ዘመን ነው። የኢትዮጵያ ትንሳኤ ግን በሰው እጅ አይደለም፣ በእግዚአብሔር እጅ ነው። በ9-11 ቀመር የተያዘ ነው። ኢትዮጵያንና ፡የምድያምን ምሰጢር ያካተተ ነው። ኢሳይያስ 18 እውን እየሆነ ነው። ምልክት በየአቅጣጫው ነው። እግዚአብሔር ደብረ ሲናን የገለጠበት የምድያም ሕግና የጽዮን ህግ፣ በ 42 ዲግሪ የተቀመረ ሁለቱን የኢትዮጵያን በኩሮች ወደ ፍርድ የጠራ ቀመር የማይዛባ ነው። ከዚህ ላይ ባላብራራውም የደብረ ሲና ሕግና የደብረ ጽዮን ሕግጋት በሚቀጥሉት የግዕዝ ቀመሮች የተነደፉ ናቸው፡፡

ሀ. ደብረ ሲና፡ የምድያም ሕግ= {59 X 260 = 42 X 365 ¼}

ለ. ደብረ ጽዮን = 44 = (12 X 12 ) + (13 X 7) = 235

እነዚህ የግዕዝ ቀመሮች የአስትሮኖሚ ሳይንስ የከዋክብትን ዑደትና የነፋሳትን ሥርዓት ለመግለጥ የሚጠቀምባቸው ስሌቶች ናቸው። የደብረ ሲና ቀመር ብለን በግዕዝ ምስጢር ያስቀመጥነው የማያ ካሌንደርንና የትሮፒካል ካሌንደርን እኩልዮሽ የሚያመዛዝን ነው። ግን ይኸ አፋዊ ነው። በውስጠት ትርጉሙ መንፈሳዊ የሆነ መልእክት አለው ለአብራም (59) የተሰጠ ቃል ኪዳን በ42ኛው የዘር ሐረግ በተቆጠረ ኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ ፩) የተሟላ ቃል ኪዳን መሆኑን የሚገልጽ ነው። ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ክብ ጂኦሜትሪ (ክብ = 59) ሲወክል በ42 ዲግሪ የተቆጠረ የ14 ቀመር የጽድቅ ጎዳና ሄኖካዊ ብሂልን ይይዛል። የደብረ ጽዮን ቀመር ሆኖ የተቀመጠው ደግሞ አበው “አበቅቴ” ብለው የሚጠሩት በግሪክ አለም ፡”Metonic Cycle” የተባለ የጸሐይ፣ የጨረቃና የምድርና ግንኙነት የሚገልጥ ቀመር ነው። በመንፈሳዊ ይዘቱ ግን የኢየሱስ ክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያንን ግንኙነት የሚያመሰጥር ነው። 44ኛ ዲግሪ የሚሆን የሕይወት “ተመን” ስለሆነ ነው፤ የጋብቻ

ምስጢርም በዚህ ቀመር ፡ይጠናል። 144 አዳም ነው፣ 91 ሄዋን ናት። በደብረ ጽዮን የሚቆመው በግ ኢየሱስ (144) ነው፤ ሙሽራው የሰላም ቤት ቤተ ክርስቲያን እንደ መስዋዕተ አቤል የተወደደ የጥበብ መስዋዕት ፡የሚቀርብባት ሙሽራዋ ናት፤ ሰማያዊዋ ኢየሩሳሌም ናት።

በዚህ ፣መንፈሳዊ ቀመር እያንዳንዱ ሰው በትንፋሹ፣ እንዲሁም በደሙ ውስጥ ከፈጣሪው ጋር የሚኖረው ግንኙነት የሚለካበት የሰለሞን መርበብት ይገለጣል። መርበብቱ እያንዳንዱን ነፍሳት የሚይዝ ሲሆን የኢትዮጵያን ክብር ወደ ቦታው ሳይመልስ አያርፍም!

ይኸ ምስጢር ለኢትዮጵያ ድኅነትና መሠረት የሚሆን ሲሆን የአዳም ልጅ ሁሉ ተመልሶ በክብር እንዲቆምና በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ የተሰበረ የልብ መስዋዕት እንዲያቀርብ መንገዱን የሚጠርግና በደምና በውኃ ብሎም በመንፈስ የሚሰራ ምስጢር ነው። ይኸ እንዲሆን ተስፋ፡የሚያስቀርጠውን ፡የአለምን ቋንቋ መተው የግድ ያስፈልገናል። ይኸንን ምስጢር እንድንፈታ የተቀናጁ መናፍስትን የሚጋብዝ የሰው አእምሮ የፈጠረውን የ”ቅንጅትን የአለም መንፈስ”ን እንደ ዮርዳኖስ ውኃ ተሻግረን አዲሲቷን ኢትዮጵያ እንድናያት የእግዚአብሔርን መንፈስ ብቻ መያዝ ይኖርብናል። የሰው መንፈስ ከእግዚአብሔር መንፈስ እንዲለይ፣ የኢትዮጵያ መለኮታዊ ዕጣ በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በሮማ-ግሪክ የአእምሮ ጥበብ፣ የሚፈታ ስላልሆነ፣ የአለም መንፈስ ለእግዚአብሔር መንፈስ እንዲገብር ያስፈልጋል።አዎን ከአእምሮ የፈለቁ፣ በምድሪቱ ላይ የተበተኑ መናፍስት ልከኛ ቦታቸውን በእግዚአብሔር ኅለተ ወርቅ እንድንለካቸው ያስፈልጋል። ይለካሉም! እውን ከዋክብትን የሚቆጥር መድኃኔ ዓለም ይኸ ይሳነዋል?

ለማንኛውም የአስረስ የኔሰው “ትቤ አክሱም መኑ አንተ?” ብሎም የካም መታሰቢያ የሚሉ የመንፈስ ፍሬዎች መሠረት ይሆኑናል። አዎን የእኔነትን መንፈስ በኢትዮጵያ ምድር ላይ የበተነውን የአለም የአውሬው መንፈስ በግዕዝ ቀመር ልናውቀው ያሻል። አይገርምዎትም በግዕዝ ቀመር የእግዚእ ስም 360 ዲግሪ ይመጣል። (አ=40፣ ገ=200፣ ዘ=80፣ አ=40፣ ድምር እግዚእ=360)፣ ግዕዝ እንዲህ ረቂቅ ነው። ሌላው ዝርው ነው። በእርስዎ ብርታትና ገላጭነት የተማርኩበት የ”ኢትዮጵያ ጂኦግራፊ” (Ethiopian Geography) አምሳል መርገፍ ነው። በርግጥም እንደሚያውቁት ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር የቃል ቲኦግራፊ (Theography of the Word) የተሳለች የቃል ኪዳን ሀገር ነች። ይኸ ንዑድና ክቡር መንፈስ ነው እርስዎን ስለኢትዮጵያ የሚያቃጥልዎት። ግን የእግዚአብሔርን መንፈስ ንዴትን ያበርዳልና.. የኢዮብን ትዕግሥት ለጥቂት ይስጥዎት…ስምዖን የእስራኤልን መዳን እንደጠበቀ እርስዎም የኢትዮጵያ ስምዖን ይሆኑናል፣ እንደርስዎ ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ትንሳኤ ለሚጣምኑ በኩር ሆነውናል።

አይዞዎት አባቴ ሆይ! እግዚአብሔር መልሱን ይሰጠናል። በርግጥ የሰዎች የቅንጅት መንፈስ አእምሮአዊ ይዘት ስላለው እንደ ሰዎች ስሜት ሲወጣና ሲወርድ፣ የድቡሽት ላይ ሕንጻ ሊሆን ይችላል። የተማመኑበት በሰው ሰውኛ ተመሰቃቅሎ እንደ እንቧይ ካብ ሲፈርስ ንዴት ስለሚያመጣም “የኢትዮጵያ ታሪክ እንደከሸፈ” ሊያሳስብ ይችላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ግን “ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።” የሚል ነው፡፤ የኢትዮጵያ ምስጢር በ “ተየ” ምስጢር በ “እ-ተየ'ጰ-የ” ቱባ ምስጢር የተያዘ ጥልቅ ነው። ይኸ ግሪካዊ ሀሳብ አይደለም። ኢትዮጵያዊ የሆነ የሰማያዊ ግዕዝ ትሩፋት ነው። “የዘንዶውን ራስ ትቀጠቅጣለህ።” የሚል ነው፤ “ለኢትዮጵያ ሰዎች ምግባቸውን ሰጠሃቸው።” የሚል ነው። ከተቀናጀው የሰው መንፈስ የማይናወጠው፣ አንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ይበልጣል። ዘይትና ውሃ ካልቀላቀልን በጥሞና የኢትዮጵያን ትንሳኤ እናያለን። አዎ “ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ” ይላልና መተማመናችን በእግዚአብሔር ብቻ መሆን አለብን። ንዴት ይገለናል። የእግዚአብሔር ተስፋ ያድነናል። እግዚአብሔርም ለኢትዮጵያ ክብሩን ይገልጣል። ለልጆቿ እውነተኛውን ምግብ ይሰጣቸዋል።

አዎን ንዴት መፍትሔ አይሆነንም፡ የእግዚአብሔር የይቅርታና የሰላም መንፈስ ያሻናል… እውነት ነው የተቀናጀ የሰው መንፈስ ሲበተን ያናድዳል፤ ለኢትዮጵያ የተቀናጀ የሰው መንፈስ የ666 በሽታ አለበት ይልቅስ ቀደም ብለን ይሉን እንደነበረው ይቅር ምንተእግዚአብሔርን እንያዝ፣….ግን አእምሮን ሳንቀላቅልበት በፍጹም የእግዚአብሔር መንፈስ ይሁን።

አይዞዎት!፡በራዕይ የተገለጠው የእግዚአብሔር ድንኳን የሚገለጥበት ምስጢር እውን የሚሆንበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፦

> “እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። በዙፋንም የተቀመጠው። እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም። እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ። “ (ራዕይ 21፡3-5)

ይኸ ለኢትዮጵያ ልጆች እውን መሆን አለበት!!! ይሆናልም፤ ይኸ በየቦታው የሚራኮተውን የሰውነት መናፍስት ስብስብ ይተዉት… ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ ነው…ኢትዮጵያ መንፈሷ አንድ ነው። አዎን የተቀናጀ የሰው መንፈስ በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጥ ይገዛል። **የኢትዮጵያ ትንሳኤ ፀሐይ ከምስራቅ በኩል እንደመውጣቷ እውን ነው።**ንግሥተ አዜብ በቤተ መንግሥትና በቤተ ክህነት የ 29 ምስጢር ገልጣለች። የ29 ፍርድ የተገለጠው ሂዋንን በገነት ባሳተ በ”እባብ” መንፈስ ላይ በተሰጠው ፍርድ ነው።

ትእዛዝ ከሰማያዊ አባባ ነው = አባባ = 58

የዳቦ ግንብ ፡የሚገነባ መንፈስ፣ ሂዋንን በገነት ያታለለ = እባብ = 58

ሬጋን ህንጻ ውስጥ "ግዕዝ፣ ግዕዝ፣ ግዕዝ ብሎ ፡የለፈፈው  መንፈስ = 58

በግዕዝ ቀመር "አበበ" የሚለው ቃል "58" የሚሆነው "አ=40፣ በ=9፣ በ=9፣ ድምር=58"  ሆኖ የሚቀመር ነው። ይኸውም 58 ታቦት በሰማይ፣ ታቦት በምድር በሁለት አንጻር 58 ነው። ነጻነት ብሎ የሰራ የተሳደደውን የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ የወከለ "አበበ" በሚባል የኢሳት ጋዜጠኛ ላይያደረ "ባርነት ለኢትዮጵያ አይመችም" የሚል የእምቢተኝነት የመወየን መንፈስ ነው። ይኽ ግን በእርሻ፤ ሕግ (law of the farm) የሚተዳደር የምላስ ሕግ ነው። ዐይን ላወጣ ዐይኑ ይውጣ የሚል የኦሪት ሕግ ነው።  ለጽሁፍ አርታኢ እንደሚያስፈልግ ለሚናገርም አርታኢ (editor) ያስፈልገዋል። የጥበብ ፍሊጋ ጉዞ ሁለት ስርዓት አለው (ለማወቅ ተራራ መውጣት፣ ስህተትን ለማረም ከተራራ መውረድ የማያቋርጥ ዑደት ነው) ሁለቱም ተናጋሪዎች የነፍስ ዕጣ ሆኖባቸው ተገናኙ። ተናጋሪን ተናጋሪ አረመው። በ29 መንፈስ የተላከ ነው። ለቀልድ አይደለም የኢትዮጵያ ቅዱሳን 'ሰአሊ ለነ ቅድስት" የሚሉት። የታቦቱ (29) ቱባ ምስጢር ነው።

ለሰዎች ጉባኤ የተሰጠው ፍርድ የዳቦን ግንብ በባቢሎን ስርዓት ያፈረሰው በ5/18/2012 የተገለጠው ነው። ይኽ በዘፍጥረት የተሰጠውን የባቢሎን ግንብ በ9/11 ምስጢር ያካተተ ነው።  በበ42ኛው ወን በ6/29/12 እግዚአብሔር ድምጹን በምድያም ምድር አሰምቶ ንግሥተ አዜብን ገልጧል። ለቤተ ክህነቱ ስርዓት መዛባት በ (5፤10 የሙሴ ምስጢር በአሮናዊ አካሄድ በ360 ዲግሪ እንዲሁ ፍርድ ተሰጥቷል። ይህ የ58 ሕግ ግን ስለ ጽዮን ታቦት ነው። ተ=10፣ በ=9፣ ተ=10 በድምር 29 ነው። ጽዮን በሰማይ፣ በምድር 58 ነው። ይኽንን የኢትዮጵያ ትንሳኤ ፍርድ በቀመር የተያዘ ነው። አይዛነፍም፤ እውን ነው።

አይዞዎት... ኢትዮጵያን እንደ ሁልጊዜው ዛሬም አይዞሽ ይበሉአት። አዎን በአባቶች ፈለግ ለኢትዮጵያ መሰዋት የነፍስ ማህተምዎ መሆኑን አስተምረውናል። ግን የኢትዮጵያን ትንሳኤ እንዲያዩ የተቀናጀ የሰው መንፈስ ፋይዳ ሳይኖረው በመቅረቱ ሊፈጥረው የሚችለውን ንዴት ትተው፣ የእግዚአብሔርን መንፈስ ብቻ ይያዙ። በእግዚአብሔር ተስፋ ብርሃን ብቻ አለ። ንዴቱ የሰውነት ነው። የሰውን ለሰው፣ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ነው። በቃ ሰውን አየነው...እግዚአብሔር የሚለንን እንስማ። እባክዎትን ትንሽ ነው የቀረን ...ተስፋ አይቁረጡብኝ።

አዎን ... ፕሮፌሰር መስፍን የኢትዮጵያን ትንሳኤ ስለሚጠባበቁ የኢትዮጵያ ስምዖን (ሉቃ. ፪፡፳፰-፴፬) ነዎት። ... ምንም ቢያደርጉ ለኢትዮጵያ ነበር፣ ነውም። የሰውነት ስራ የሙከራ ስራ ነው፣ መምህር ነበሩ የተዋጣለት... ለሰው ልጅ መብት ተከራከሩ... ኢሰመጉ አሉ... ጻፉልን እኛ አልገባን አለ... በክህደት ቁልቁለት እንደወረድን አሳዩን፣... በመንግሥታት እስር ቤት ተወሰዱ ..ተጋዙ...ወጣቶች በኢትዮጵያ ጢብ ጢብ ሲጫወቱ

ቢያዩ ያላሰቡትን በሽምግልና እድሜ የፖለቲካ ኳስ እንዲጫወቱ ተገደዱ….. አዎን ታድገውናል…ለኢትዮጵያ የተሰጠች ዕንቁ ነፍስ ምን እንደምትመስል አብነት ሆነውናል..

ታዲያ እንደ ትንቢቱ እጃችንን ወደ እግዚአብሔር ዘርግተን በጸሎታችን እንቆይ….

ለእርስዎና እንደ እርስዎ የኢትዮጵያን የነጻነት ቀን ሲናፍቁ ነፍሳቸው ለጣመነችና የትንሣኤን ተስፋ ለሚጠብቁ በስምያን ተስፋ ለሚኖሩ ሁሉ እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና ጨምሮ የኢትዮጵያን ተስፋ ያሳይልኝ።

የአክሱም ጽዮን ታቦት ዛሬም ትናገራለች። ዛሬም በ29 ምስጢር ትገለጣለች።ዛሬም ከማሕጸኗ የሚወጣው የምድራዊው ያይደለ የሰማያዊው የማርያም ኃይል የሚያሽከረክረው የኪሩቤል ነበልባላዊ ሰይፍ ሥራውን ይሰራል። ሥጋ ለባሽ ስለማይችለው በሰው አቅም ያህል ስለሚወረወር ነው። በምድያም ምድር በ1 ሰከንደ ትንፋሽ በ29 ምስጢር የነፈሰው ነፋስ ምልክት ነው፡፤ አዜብ እየፈረደች ነው። አይዞዎት!! አይዞዎት የኔ አባት!!!

ከታላቅ አክብሮት ጋር፡፤

አቤል ጋሻ

አክባሪ ተማሪዎ

## ምዕራፍ ፩፡ ጥቅልል መልዕክት፡ (Executive Summary)

## የኢትዮጵያ መለኮታዊ ዕጣ በፍርድ ሚዛን ላይ ነው።

## ደብረ ሲናና ደብረ ጽዮን እየተከወኑ ነው።

**ሶስት መሠረታዊ የሆኑ ሥር ነቀል መንፈሳዊ ክስተቶችን ልብ በል።**

ሀ. አለም በመጨረሻው ዘመን በፍርድ ቀለበት ውስጥ እየተሽከረከረች መሆኑን፣ የዘመኑን መፈጸም የሚናገር የአለም መንፈስ በ”9/11” ኮድ ታትሞ ወደ ምድር ተላከ። ይኸ መንፈስ አገዛዙን በምድር ላይ አስፍኖ በራዕይ ፲፫፡፭ ላይ የተፈቀደለትን የ42 ዘመን አገዛዝ አጠናቋል። ጊዜውም ከ9/11/2001 እስከ 5/2/2011 ድረስ የተቆጠረ ነው። ይኸ የፍርሃት መንፈስ የነገሰበት ወቅት በጠቅላላው የ1260 ወራትን ሰማያዊ ምስጢር ይጠቀልላል። መንፈሱ ያደረው ኦሳማ ቢላደን በሚባሉ ሰው ላይ ነበር። የኒህ ሰው አስከሬን በባሕር ላይ እንደተጣለ በራዕይ ፰፡፩-፱ ከተዘገበው ምስጢር ጋር ማገናዘቡ ይበጃል። ይኸ አንድም ሶስትም ሆኖ ለሚሰራ የአለምን መንፈስ (ዲያብሎስ አባት፣ ኃሳዊ መሲሕ ልጅና የሁለቱም ሕይወት የሆነ የውሸት መንፈስ) ለመፍረድ የተላከ መገለጫ ስለሆነ በሶስት የጊዜ ዘርፍ የተከወነ የጊዜ ቀመር ነበር። ይኸ የመጨረሻው ዘመን የፍርድ መለከት የተነፋበት ምሥጢር የተከወነው ስለሰማያዊው የእግዚአብሔር ስም ክብር ምልክት ይሆን ዘንድ ተቀመረው በ”9-11” ኮድ ነበር። “9-11” ግን “ሥም/ስም”የሚል የዘመኑ መሽብለያ፣ የዘመን መጀመሪያ ኮድ ነበር።

ለ. በዚህ ኮድ (9-11) የተቀመረ ሌላ የፍርድ ሰዓት እንዲሁ የአዜብ ንግሥት መሠረት በሆነችው የሴቲቱ የቃል ኪዳን አገር ኢትዮጵያ በአውሬው መንፈስ ተፈጽሟል።

ይኸውም በመስከረም ፩ 1967 (9/11/1974) ዓ.ም. አጼ ኃይለ ሥላሴ በውርደት መንፈስ ከዙፋናቸው መውረዳቸው ነበር። የተሳደደችበትን ዘመን ያስተዋወቀ የኢትዮጵያን የኢካቦድ ዘመን የጀመረበትን ጊዜ የሚያመለክት፣ ክብር ከኢትዮጵያ ዙፋን እንደተነሳ የሚያመለክት ክስተትም ነበር። በዚሁ በ9-11 ኮድ በተነደፈ ብሂል የተጀመረው የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከየካቲት 1966 እስክ የካቲት 2008 ያለውን ጊዜ ሲጠቀልል የእግዚአብሔር ስም በምድረ ኢትዮጵያ የተሳደደበትን ዘመን ይሸፍናል። የ42 ዘመን ይቆጠርበታል። 3 በእግዚአብሔር ስም ቀን የሚቆጠር፣ 3 የሰው አመታት ፡ይቀረናል። በዚህ 42 ዘመን ውስጥ በአንድ ሰማያዊ ቃል የተቀመረውን በሰው ሀሳብና ፍላጎት የተለያየውን የኢትዮጵያ የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት ጥምረት በ42 ዲግሪ ቀመር የጠራ የፍርድ ስርዓት ተከውኗል። ይኸውም በኢትዮጵያ ሰማያዊ የክህነት ወንበር ለ21 ዓመት የተቀመጡትን ብፁእ ፓትርያርክ ጳውሎስና፣ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ዙፋን ላይ ለ21 ዓመት ፡የነገሱትን ክቡር ጠ/ሚ መለስ ዜናዊን፣ ማለትም ሁለት የኢትዮጵያን በኩሮች በዕረፍት በአንድ ሰሞን የከወነ በ (አዋዲ- አድዋ- አዋጅ) ምስጢር የተያዘ በመንፈስ አይን ለሚያየው አስደንጋጭ ክስተት ነው። በ8/20/2012 እንደሞቱ የተነገረው ክቡር ጠ/ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ከ360 ዲግሪ ከሚቆጠረው የእግዚአብሔር ስም (እግዚእ) የሚያገናኝ መለኮታዊ ምስጢር ጋር በሚያስተሳስር መንገዱ ዕጣቸው በ8/25/2011 በአሜሪካ ምድር ከተገለጠው የመሬት መንቀጥቀጥ ጋር በሰማያዊ ሚዛን በእግዚአብሔር ፊት የአንድ ቀን የምልክት ማሰሪያ ተደርጎለት ነበር። ልብ ያለው ግን አልነበረም። የአክሱም ሐውልትና የዋሽንግቶን ሐውልት ምን አገናኘው? ያጠያይቃል።

ይኸ የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ተጠናቆ፣ ኢትዮጵያ እንደገና ሰማያዊ ቃል ኪዳኗ ታድሶ በእግዚአብሔር ፊት ከብራ፣ ምድሩ እግዚአብሔር እንደ ተለመው፣ የሰላም ምድር፣ መንፈሳዊ ነጻነትን የተላበሱ፣ ያለፍርሃት እግዚአብሔር ብቻ አምልከው፣ ለእግዚአብሔር ሰግደው የሚኖሩበት፣ በአለም ፍርሃት የማይሳደዱ እግዚአብሔር የኢትዮጵያ ልጆች ብሎ የሚኖሩበት፣ የታቦተ ጽዮን መሠረት የማይሳደድበት ጊዜ መምጣቱን ጠቋሚ መንፈሳዊ ምልክት ነው። ይኸም ፀሐይ በምስራቅ እንደመውጣቷ

የታመነና በቀመር የተለካ ነው። ይኸ ዘመን **"መንግሥቱ ኃይለማርያም ደሣለኝ"** የሚባል የጽዮንን "ኃይል" በስማቸው ይዘው፣ የጽዮንን ቃል ኪዳን ያሳደዱ ወይም የዘነጉ መሪዎች በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የተቀመጡበት የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን የሚጠነቀቅበትንና በኢሳይያስ ፲፰ ላይ የተጠቀሰው የኢትዮጵያን የቃል ኪዳን ትንቢት የሚፈጸምበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የሚከወንበት ዘመን በአድማሱ ላይ ተገልጦ እየታየ ነው። በትክክል ይኸ ዘመን የሚጠናቀቅበትን ሁኔታና የጊዜ ቀመር በመንበሩ ሁልጊዜ የሚኖር፣ ትሑቱ ሙሴ "ስቡሕ ዘተሰብሐ" ብሎ ያመሰገነውን የእስራኤል አምላክ ያውቃል። ሰዓቱን የሚያውቅ፣ ብሉየ መዋዕል የተባለ አብ አኃዜ ኩሉ የተባለ አብ ብቻ ነው፡፡

ሐ. እንዲሁም በኢትዮጵያ መለኮታዊ ዕጣ ዙሪያ የሚያጠነጥን ከነነዌ ሕዝብ ጋር ለፍርድ ትነሳለች የተባለች ንግሥት አዜብ መነሳቷን የሚገልጥ የ42 ቀን ምስጢር በአሜሪካ ምድር በ2012 ዓ.ም.ተከውኗል። ይኸውም የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስቴር በሬጋን ሕንጻ ውስጥ ንግግር ሲያደርጉ ተቃውሞ ከገጠማቸው ቀን ጀምሮ ሲቆጠር በዚሁ ምድር በ42ኛው ቀን የእግዚአብሔር ድምጽ የተሰማበትን ምሥጢር የሚያጠቃልል ቀን ነው። ይኸ ከ5/18/12 እስከ 6/29/12 ያለውን ጊዜ የሚቆጥር ነው።

በሶስቱም የ42 ቀመር የተለኩ ጊዜያት የአለም መንግሥት አብቅቶ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚተካ መሆኑና የእግዚአብሔር ድንኳን ከሰዎች ጋር የሚኖር መሆኑን የሚጠቁሙ ቀመሮች ናቸው። በአዳም ስህተት ምክንያት የተከፈለውን የሰማያዊና የምድራዊ መንግሥት ወደ አንድ ይመልስ ዘንድ ቃለ አዋዲ ሰጥቷል። ይኸ አዋጅ በአድዋ ምስጢር፣ በኢትዮጵያና በሮም ፍቅር የተጠቃለለ ነው። በድንግል ማርያም የፍልሰታ በዓል (በ40 የንስሐ ቀመር) ሁለቱ የኢትዮጵያ በኩሮች መጠራታቸው የዚሁ የንግሥተ አዜብ ከመነሳቷ ጋር የተያያዘ ነው። የኢትዮጵያ ቃል ኪዳን መታደስ ይኖርበታል፣ እየታደሰም ነው። ከቅድስት ድንግል ማርያም የአሥራት ሀገር ጋር በተያያዘ ስለሚገለጥ የንስሐ (ነሐሴ) ተፀምር ነው። (ነ=30፣ ሰ=7፣ ሐ=3፣ ድምር ንስሐ=-40)

ይኸ ለኢትዮጵያ የተሰጠውን ቃል ኪዳን ይታደስ ዘንድ፣ በራዕይ ፲፪ የተጠቀሰው ሴቲቱን የሚያሳድድ መንፈስ በእግዚአብሔር እርሻ ላይ የዘራው የአለም መናፍስት ፍሬ

ይነቀል ዘንድ የሚፈጸም የ42 ቀመር የንግሥተ አዜብ የፍርድ ሥርዓት ዘመኑ የሚታደስበት ምሥጢር ነው። ከዚህ ጥበብ ይኖራል…. ልብ ያለው ልብ ይበል….ለእያንዳንዱ ነፍስ ግን ሰዓቱ የፍርድ ይሆናል። ለዚህ ፍቱን የሆነ ምክር የድንግል ማርያም ጸሎት ነው።

> ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው። ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል። በክንዱ ኃይል አድርጎአል፤ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል፤ ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል፤ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል። ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ፥ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል። (ሉቃ.፩)

ድንግል ማርያም የጸለየችው፣ እንደ እናትነቷ ብቻ ሳይሆን እንደ ሰውነቷ ለፈጣሪዋ ያላትን ተገዥነት በመግለጥ ጭምር ነው። ይህቺ እመ አምላክ ለ42 ወር ለሰው ልጅ ድኅነት ብላ በግብጽ ምድር ንጉሷን፣ አምላኳን፣ ልጇን ይዛ የተሰደደችበት ዘመን ነው። ለዚች ድንግል ስምዖን የተናገረው (በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል) ፈተና እመቤታችን በአካል ስደት 42 ወራት እንደፈጸመች እንዲሁ ለመጨረሻው ዘመንም ንግሥተ አዜብን ለመግለጥ ኢትዮጵያ ልታልፍበት የተቀመረ የቃልኪዳን ስደት ዘመን ስለነበረ በድንግል አሥራት ሀገር ላይም እየተከወነ ነው። (1966-2008)፡፤ ከዚህ የስደት ዘመን ኢትዮጵያን የሚያወጣት፣ የድንግል ማርያም ልጅ፣ የታቦተ ጽዮን ጠባቂ፣ ንግሥተ አዜብ በጎኑ ቆማ የምትፈርድ ኃያሉ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይኸንን የሚያውቅ ግን “ምስለ ፍቁር ወልዳ”ን ያከበረ፣ የኢትዮጵያ እውነተኛ ገዢዋ ሰማያዊ “ኃይለማርያም” እንደሆነና በብረት ዘንግ ቀጥቅጦ ፡የሚገዛውን ልጇን ፈርቶ ቃል ኪዳኗን ያከበረ ሰው ነው።

በ42 ዘመን የተቆጠረው **የ”መንግሥቱ ኃይለማርያም ደሣለኝ”** የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ሊጠናቀቅ ሶስት ዓመት ቀርቶታል። በምድራዊው ያይደለ በሰማያዊው የማርያም ኃይል የመለኮት ሠይፍ የሚጸና መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ይጸናል። የኢትዮጵያን ልጆች እግዚአብሔር ምግባቸውን ይሰጣቸዋል። የአዜብ ነፋስ ነፍሷል፣ በግብጽ ሽውታው ተሰምቷል፤ የአረብ ምድር መልዕክቱ ደርሶታል፣ ነገሥታትና ፈርኦኖች እንደ አቧራ እየበነኑ ነው። የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ከዋክብት ትልቅም፣ ትንሽም በሚገርም የትዕቢትና ፡የማንአለብኝነት ገመድ ተተብትበው እየወደቁ ነው። በቤተ መንግሥትነ በቤተ

ክህነት የኃሳዊ መሢህ መንፈስ ነፍሳትን እግር ከወርች አስሮ የኢትዮጵያን የመለኮት ዕጣ በመስቀል ላይ የወጠረበት ሰዓት ነው። ጊዜው የሚያስፈራ ነው… የድኅነትን ተስፋ ግን አርግዟአል። የነፋሱ ባለቤት በጸጥታ ይመለከታል።

አዎን! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የፈተነባቸውን ሶስቱ አርእስተ ኃጣው ያማከለ ቅን ፍርድን በሰው ልጆች ጉባኤ እየገለጠ ነው። ሰው ከሥጋዊ አመለካከቱ ከፍ ብሎ በመንፈሳዊ አይን አለማየቱ እንጂ የአለም ፍጻሜ በደብረ ሲና ሕግ እየተከወነ፣ ጎን በጎን ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚገለጥባቸው መሠረታዊ ሁነቶች እየተከሰቱ ነው። ይኸንን አጉልተው የሚያሳዩ፣ በሰማያዊ ቀመር የማይዛነፉ ምልክቶች አሉ።

ሀ. ክርስቶስ በዳቦ ስለተፈተነበት የተሰጠ ፍርድ - በ5/8/12 በሬጋን ህንጻ ውስጥ የሆነው ክስተት። ይኸ ዳቦን ያማከለ አስተሳሰብ በአለም ያመነጨውን የሀሳብ አምልኮ የፈረደ ነው። በታቦተ ጽዮን ቀመር (29) የታሰበ፣ የ “58” ዲግሪ ፍርድ ነው። እባቡ ሄዋንን ያሳተበት የዳቦ ምኞትን የሚያገንን መንፈስ በዚህ ፍርድ ተቀስፏል።

ለ. እግዚአብሔርን በሥልጣን ለፈተነ ዲያብሎስ ፍርድ - የአለም ምልክት ቀዳማዊ እመቤት አዜብ፣ ለ21 ዓመት በአለም መድረክ በክብር ተረማምደው ያለፉበትን ዘመንና በምትካቸው ንግሥተ አዜብ ከነነዌ ሕዝብ ጋር ቆማ ለመፍረድ መንገዱ የተጠረገ መሆኑን የሚያመለክት የ42 ዲግሪ ምስጢር (5/18/2012 — 6/29/2012)

ሐ. ክርስቶስን ‘አለምን ልስጥልህና ስገድልኝ ያለን” ዲያብሎስ ስለአምልኮ የፈረደ። ይኸ ጠቅላላውን የአዳምን የድኅነት ፕላን የጠቀለለ በ”9-11” ኮድ የታተመ፣ የኢትዮጵያንና የአሜሪካን ዕጣ ለዘላለም ያስተሳሰረ፣ የአብርሃምን ቃልኪዳን ያማከለ፣ የይስሐቅና የእስማኤል ልጆችን ዕጣ የጠቀለለ የኢትዮጵያና የእስራኤል የቃል ኪዳንን ትስስር ያማከለ ምስጢር ነው። ይኸ በ42 ዘመን የተቆጠረው የአውሬው ግዛት የተገለጠበትና የተጠናቀቀበት ነው። በዚህ ውስጥ በ9/11/1974 የአጼ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን መወገድ፣ በ2000 ዓመት ምህረት በሥልጣን ላይ የነበሩት ፕሬዚዳንት ክሊንቶን በ42 ቁጥር ተወክለው፣ በ9-11 ኮድ፣ በ59 መንፈስ መፈረጃቸው፣ በ8/25/11 ዋሽንግቶንን “አለሁ” ያለው የ360 ዲግሪ ምስጢር፣ በ8/20/12 ኅልፈታቸው የሆነው የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት የጠቀለለው

የአለም ግዛት መንፈስ በጠቅላላው የእግዚአብሔር ድንኳን በምድር ላይ ሊገለጥ የታሰበበትን ቀመር የሚገልጡ ናቸው።

እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ የፍርድ ዘመን መልሕቆች ይሁኑ እንጂ ይኽ የዛሬው ትውልድ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በአዲስ መልክ የሚያጤንበት፣ ሲሆን በነዚህ የፍርድ ስርዓቶች የተገለጠው የደብረ ሲና ፍርድ፣ በአንጻሩ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የሚገለጥበትን የደብረ ጽዮን ጥበብም የሚያበስር ነው።

አዎን እግዚአብሔር ደብረ ሲናን ለፍርድ፣ ደብረ ጽዮንን ለአዲሱ የእግዚአብሔር መንግሥት እየገለጠ ያለበት ሰዓት ነው። ይኽም አሁን፣ ዛሬ እኛ የምንበላ፣ የምንጠጣ፣ የምንተነፍስ፣ የምንናገር፣ የምንንቀሳቀስ ሰዎች ባለንበት በአሁኑ ሰዓት ማለት ነው። ሁሉም የአዳም ልጅ ይኽንን ዘመን የጥበብ አይኑን ከፍቶ ሊመለከተው የሚገባ ነው።

ይኽንን ምስጢር ለአለም ሕዝብ ገልጣ የምታሳይና የዘመኑን መጠንቀቅ ምስጢር የምትፈታ ኢትዮጵያ ናት። በመለኮት ቃል ኪዳኗ የንግሥተ አዜብ፣ ሚዛኗን የምትይዝበት የኢትዮጵያ ምስጢር የሚገለጥበት ሰዓት ይህ ነው። ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር የጸሎት ግምጃ ቤት፣ እንደመሆኗ፣ ሰማያዊ የቤተክህነት ሐብታቷንና የቤተ ክህነት ሊቃውንቶቿን ይዛ ሰማያዊ የግዕዝ ምስጢሯን ገልጣ በአለም መድረክ የደብረ ሲናን መከወን፣ የደብረ ጽዮንን መገለጥ፣ ብሎም በጉ በጽዮን ቆሞ የሚሰገድለት መሆኑን የምታሳይ የእግዚአብሔር የፍጥረት መለኪያ ቀመር ናት። አዎን ኢትዮጵያ የንግሥተ አዜብን ምስጢር ትገልጣለች። ይኽንን ስራ ጀምራለች። የሰማያዊ ንግሥተ አዜብ መምጣት ምልክት ይሆኑ ዘንድ በአለም ክብር የተገለጡ፣ በኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ወንበር ተቀምጠው በእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን በሰው የሚመኩ፣ “የመለስ ጭንቅላት እኮ…”ብለው በባላቸው መመካታቸውን በኩራት የሚናገሩ ቀዳማዊት እመቤት አዜብ በኢትዮጵያ ዙፋን ዙሪያ ተገልጠው ዘመኑ ሲጠነቀቅ ታይተው ከመድረኩ ዘወር እንዲሉ ተገደዋል። የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን የሆነ በ42 ቀመር የተለካ የ”መንግሥቱ ኃይለማርያም ደግለኝ” ዘመን ሲጠነቀቅ ሰማያዊቷ ንግሥተ አዜብ ማንነቷ ይገለጣል። መንፈሷ ግን ዛሬ ምድሩን፣ አየሩን እየተቆጣጠረው ነው። በቅን መለኪያዋ እየተለኩ በትቢት ድር የተሰሩ የቤተ ክህነትና

የቤተ መንግሥት ከዋክብት በአለም ዙሪያ እየወደቁ ነው፡፡ አሐቲ ቤተ ክርስቲያን በክብሯ ትቆማለች፣ ቤተ መንግሥት እንደገና የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ ይሆናል።

አዎ ንግሥት አዜብ ትሑታንን ከፍ ልታደርግ ተነስታለች። ትዕቢተኞችን በልባቸው ሀሳብ እየበተነች ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ ሁልጊዜም ቅንና ትክክል ነው። ምህረቱም ለዘላለም ነው። በዚች ምስጢረኛ ንግሥት መነሳት ላይ መለኮታዊ ዕጣዋ የሚሸከረከው ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታለች።... እግዚአብሔርም .....

> "በፀሐይ ሙራ እንደ ደረቅ ትኩሳት፥ በአጨዳም ወራት እንደ ጠል ደመና ሆኜ በማደሪያዬ በጸጥታ ተቀምጬ እመለከታለሁ ብሎኛልና።" (ኢሳይያስ 18፡ 4)

አዎን ለኢትዮጵያ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽማል... እንደተናገረም "በዚያን ዘመን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር፥ ከረጅምና ከለስላሳ ሕዝብ፥ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ከሆነ ወገን፥ ከሚሰፍርና ከሚረግጥ፥ ወንዞችም ምድራቸውን ከሚከፍሉት ሕዝብ ዘንድ እጅ መንሻ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ስም ወደሚገኝበት ስፍራ ወደ ጽዮን ተራራ ይቀርባል።" (ኢሳ. 18፡11)

ይኸንን በጽዮን በጉ የመገለጡን ምስጢር መግለጥ ይቻል ዘንድ በራዕይ ፲፩ የተገለጡት ሁለት ምስክሮች ማቅ ለብሰው ቆመዋል። ማቅ የሚል ቃል በቀመር "12" ነው። በዚህ በአራቱ ማዕዘን በሶስቱ ስላሴ ስም የተሰበኩ የክርስቶስን ባሕርይ ያማከሉ ሁለት ምስክሮች ይጠራሉ። ይኸ የኢትዮጵያና የሮም ቤተክርስቲያን በሚዛን የሚለኩበት ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ሁለት ባሕርይ መሆኑ የሚፈረድበት ምስጢር ነው። የአለትነተን መንፈስ በጴጥሮስ ወንበር የሮም ተሰጥኦ ይፈረጃል። በመጋቤነት መንፈስ የኢትዮጵያው የክህነት ወንበር ይፈረጃል። ሁለቱም ተጣማሪ ስለሆኑ የጳውሎስ ወጴጥሮስ ወንበር በዘመኑ መጨረሻ የሚመዘንበት ሚዛን ነው። ኮዱ "1221" ነው፤ በእግዚአብሔር ስም ዙሪያ የሚሆን ነው። ለአብራም በተሰጠ ቃል ኪዳን ይታያል። አብራም በሚለው 59 ኮድ ሮም፣ አብርሃም (60 ወ 360) በሚለው ኮድ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ይመዘናሉ። እኒህ የሁለቱ ምስክሮች ምስጢር ነው። በፈራጁ ቀኝ ማን ይቆማል? ሁለት ባሕርይ ወይስ አንድ ባሕርይ? የቤተ ክርስቲያን ማዕዘን የሆነው ሕያው ድንጋይ ስሙን በፍርድ ካሰከበረ በኋላ፣ የሳሌም ንጉሥ፣

የጽድቅ ንጉሥ ይባላል። አዎን እንደ መልከጸዴቅ “የዘላለም ካህኔ” የተባለው የኢትዮጵያ የክህነት ስጦታ ምስጢር ነው።

ይህ ከመሆኑ በፊት ግን የአዜብ ሰይፍ መቀሰሩንና የኪሩብ ሰይፍ እየተወነጨፈ መሆኑን የተኛው ትውልድ ነቅቶ ማወቅ ይኖርበታል። በጠቅላላው የአዳምን ዘር የሚነካ የፍርድ ክንውን እየተገለጠ የእያንዳንዱን ሰው ሕይወት እየነካ መሆኑ በግልጥ የሚታይ ነው። በዚህ የዘመን መጨረሻ ወቅት በኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ዙሪያ እየተከወነ ያለውን የፍርድ ሥርዓት በጥቅሉ እንመልከት።

## ምዕራፍ ፪ - የፍርድ ሥርዓት የተጠነቀቀባቸው የንግሥት አዜብ

## ሰማያዊ ምስጢራት

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በዝርዝር ባይገለጡም የመጨረሻው ዘመን ፍርድ እየተከወነ መሆኑን ከተሰጡን ምልክቶች ውስጥ ጥቂቱን ለልብ መሰብሰቢያ ያህል እንመልከት።

ሰንጠረዥ" ፩ ፡ የፍርድ ቀመር የተጠነቀቀባቸው የንግሥት አዜብ የፍርድ መንፈስ የቆጠራቸው ሰማያዊ ቀመሮች

| የ42 ዘመን ቀመር መለኪያ | የፍርድ ሚዛን የተሰጠበት አካል። | የፍርዱ ምክንያት | ዋቢ |
|---|---|---|---|
| September `11 — May 2, 2011 | አለምን ለ42 ወር እንዲገዛ የተፈቀደለት የአውሬው መንፈስ<br><br>የአዳምን ልጆች ሕይወት የአብርሃም ቤትን ችግር፣ የእስማኤልና የይስሐቅን ዕጣ ይጠቀልላል። | በአለም መጨረሻ የተሰጠውን ለ42 ወር የመግዛት ስልጣን በአንድም በሶስትም ምስጢር ስላጠናቀቀ የአለም መንፈስ ከሥልጣኑ የተሻረበት ነው። | ራዕይ 13፡5፣ ራዕይ ፲፪፣<br><br>መንፈሱ አድሮ የሰራባቸውና የአለምን መንፈስ የተቆጣጠሩት ኦሳማ ቢላደን የተቀበሩት በባሕር ነው። ራዕይ 20 1-4 ልብ ይሏል፡፤ |
| 1/1/24-1/1/1966<br><br>ጥቅምት 23 1923 ነግሶ እስከ ጥቅምት 23፣ 1966 የተቆጠረ። | ስለእግዚአብሐር ስም ክብር። ራሱን "የይሁዳ አንበሳ" ብሎ የሚጠራ ነጋሢ መንፈስ፣ | "እግዚአብሔር ለስሙ የሚሰራ አምላክ ነው።በኢትዮጵያ ላይ የነገሰ፣ ራሱን "እኛ" ብሎ የሚጠራ ሶስቱን ሥላሴ በአንደ አካል የወከለ የ"እኔነት" አምልኮን በ"ጃ" መንፈስ በኢትዮጵያ ላይ የተከለ ፡፡ | ለአብርሃም ሥላሴዎች የታዩት በሦስት አካል ነው። ሰው-አምላክ፣ አምላክ ሰው ሆኖ ሲመጣ የሚናገርበት አንደበት ከሶስት አንድ ሆኖ ነው። "እኛ" የእግዚአብሔር በአካል ሶስት የመሆን መገለጫ ነው። በአንድ የሰው አካል አይገለጥም። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከ1966 — 2008<br><br>የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን | በኢትዮጵያ ምድር "እግዚአብሔር የለም" ብሎ በሁለት ሥርዓት የነገሰ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሰዳቢ መንፈስ፣ ቃል ኪዳን የሚረግጥ፣ ተዋሕዶን የወጋ፣ መንፈስ፣ ሴቲቱን፣ ጽዮንን ያሳደደ መንፈስ። | የቅድስት ሀገር ኢትዮጵያን በክብር መመለስ፣ የእግዚአብሔር የምስጋና ሀገር መሆኗን የተዋጋ፣ ግዕዝን የፈተነ፣ የአለም መንፈስ። | "መንግሥቱ ኃይለማርያም ደግለኝ" ተብሎ ሊጠራ የሚችል ዘመን ሲሆን በቅድስት ሀገር ልጁ ስም እየተጠሩ ቃልኪዳኗን ያዋረዱ ነፍሳት የሚፈረጁበት ፍርድ ነው። |
| ከግንቦት 20 (በኢትዮጵያ) እስከ ግንቦት 18 (በፈረንጆች)<br><br>42 = 21 (ቤተ ክህነት+ 21 ቤተ መንግሥት) | ለሁለት የተከፈለውን የኢትዮጵያ የቃልኪዳን ስጦታ ለፍርድ የተጠራበት ቀመር ነው። ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ወይስ ሁለት ባሕርይ? ይኸ የተፈረደበት ቀመር ነው። የማይከፈለው አይከፈልም። የሮምና የኢትዮጵያ ፈተና በአድዋ በደም የተፈረመ። | ሮምንና ኢትዮጵያን ያማከለ ፍርድ። የግዕዝ (፩) ና፡የላቲን (፹፪) ምስጢር ምንድን ነው? | አዋዲ - አድዋ - አዋጅ<br><br>ራዕይ ፲፪<br><br>እንግሊዝ = ግዕዝ + ለነ<br><br>በአንድ ሥጋዊ/የአለም መንፈስ የበቀሉ በ"አዋዲ/አድዋ/አዋጅ ቀመር ወደ ፍርድ የተጠሩበት ምስጢር |
| 42 ቀን አዋጅ።<br><br>ከግንቦት ፲ (May 18, 2011)እስከ ሰኔ ፳፪ ድረስ (June 29, 2011) | ቀዳማዊ እመቤት አዜብ ተሸረው ንግሥት አዜብ የተነሳችበት መንፈሳዊ የስልጣን ርክክብ አዋጅ ሲሆን፣ በኢሳይያስ 18 የተጠቀሰው ትንቢት በኢትዮጵያ ምድርና በአሜሪካ ምድር መለኮታዊ ምሥጢር የሚፈታ ራዕይ የታየበት | የኢትዮጵያ ንግሥት በሰው አትመካም። ሳባ ለእሥራኤል አምላክ እንደመሰከረች፣ ንግሥት ህንደኬ በጃንደረባዋ በኩል የኢየሱስን ስም እንደመሰከረች፣ የሙሴ አማት እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ፣ ንግሥት አዜብ የእግዚአብሔርን | በግንቦት ፲ የዳቦና የግዕዝ መንፈስ ተፋለሙ፤ የግዕዝ መንፈስ ሸፈተ፤ "…. 42 ቀን አስቆጥሮ (በሰኔ ፳፪) ከፈራጁ ጋር አብራ የምትቆም ንግሥት አዜብ መነሳቷን የሚጠቁም የእግዚአብሔር ድምጽ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የ42ኛው ዲግሪ ሥርዓት ነው። | ክብር ከፍ የምታደርግ መሆን ይገባታል። | አለፈ። ይኽ የአመረከ (100) ምስጢር ነው። |
| "42=6 ሲባዛ 7" | ጳውሎስ ወጴጥሮስ በያዙት ወንበር ዙሪያ የሚገለጥ የፍርድ ሥርዓት<br><br>**የሮም የአለትነት መንፈስ ወንበር-የጴጥሮስ ክህነት** = በ12/12=144 የተገለጠ ነው። (አብራም =59)<br><br>**የመጋቤነት መንፈስ በኢትዮጵያ ክህነት/መልከጸዴቅ** ክህነት ዙሪያ= "በአብርሃም" 12 በ 5 =60 በ 6 = 360 እግዚእ | በትዕቢት የሚገለጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚበትን መንፈስ ነው። በሰው ቁጥር "6" የተቀመረ በእግዚአብሔር ዕረፍት ስም የሚናገር የሚሰራ "7" (የእግዚአብሔርን ዕረፍት የሚሰብክ) አምላካዊ ባሕሪን ተላብሶ የሚቆም በሰው ላይ የሚሰለጥን የኃሳዊ መሢህ መንፈስ ነው።-በአሐቲ ቤ/ክ ፍርሃትን የሚለቅ የአውሬው መንፈስ የሚፈረጅበት ፍርድ ነው። | ይህ በ "12" ቁጥር ምስጢር የተገለጠ ፍርድ ነው። በ"አብ" ምስጢር የተከወነ ነው። "A-B-B-A" (1-2-2-1) — የ26000 ምስጢር ነው። አለም ያለፈችበት ሥርዓት ነው።ካህናት የተሰጣቸውን መክሊት ስተው በትዕቢት አምላክነትን እየተላበሱ የተገለጡበትን መንፈስ ነው። |
| 42 = 14 ሲባዛ 3 | ሰው ከእግዚአብሔር መንገድ ርቆ በሀብት፣ በሥልጣን፣ በባዕድ አምልኮ ሲገለጥ የሚሰለጥንበት መንፈስ ሁሉ በዚህ ፍርድ ይጠናቀቃል። | የዕድትን ጉዞ ያመለክታል። | ያዕቆብ ያገለገለው 14 ዓመት፣ የድንግል የግብጽ ጉዞ።ሐዋርያው ጴጥሮስ ወደ ሶስተኛው ሰማይ የተጠነቀበት በ14ኛው ቀን የተነጠቀበት ምስጢር ለዚህ ምልክት |
| 42 ዲግሪ የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ። | Dan Brown "Davinci Code" ብሎ በጻፈው የአለም አስተሳሰብ ላይ | "የእግዚአብሔር ስም መክበሪያ የሚሆን የምድያምን ምድር ምስጢር የገለጠ | በ8/25/ 2012 የዋሽንግቶን ህንጻ ሰንጥቆ ምልክት የሰጠ ነው። |

# ምዕራፍ ፫ -የፍርድ ዘመን መሆኑን እንዴት እናውቃለን?

አዎን ዘመኑ የፍርድ ዘመን ነው። ማለትም ሥጋ ለባሽ አይኑ ተከፍቶ ባያየውም የእግዚአብሔር የፍርድ ሥርዓት እየተከናወነ ነው። በዚህ የፍርድ ክንዋኔ ምክንያት ዛሬ በአለም ላይ ሁለት አንበሶች ጉርንቦ ለጉርንቦ ተናንቀዋል። አንደኛው አንበሣ በራዕይ 5፡5 የይሁዳ አንበሳ የተባለ የተጠቀሰው የክርስቶስ የብርሃን መንፈስ ሲሆን፣ በሁለተኛው ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ (2. ጴጥ. 5፡8) በምሳሌ የጠቀሰው የሰው ቁጥር ይዞ በኃሳዊ መሢህነት የነገሰ የዲያብሎስ መንፈስ ነው። ሁሉንም ነገር በጊዜው ለክቶ የሚፈጽም ልዑል እግዚአብሔር የአለም መንግሥት ንጉሥ ሽሮ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚገልጥበት ሰዓት መከወን ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል። የ አውሬው መንፈስ ሰፊ መዳፉን ከ አጽናፍ እስከ አጽናፍ ዘርግቶ አለምን ተቆጣጥሮታል። ብዙዎቹ ሰገዱለት፣ ዛሬም እየሰገዱለት ነው። አውሬው የ42 ወራት ሥልጣኑን ተረክቦ ሰርቷል። በስራውም ብዙውን የአለም ሕዝብ ማርኳል። ዛሬ አለም በአውሬው መንፈስ እጅ ነች። አውሬውን ማሸነፍ የሚችል የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበቡ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የክርስቶስም አዳኝነት እጅ ከተገለጠ ቆይቷል። የይሁዳ አንበሳ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር የለቀቀውን የእግዚአብሔርን ክብር ለመመለስ ተነሥቷል። ይህ የሁለቱ ኃይላት ፍልሚያ በጊዜውና በአፈጻጸሙ በጥበብ አይን የሚታይ ነው። ስለዚህ ይኸንን የመጨረሻው ዘመን አፈጻጸምና ክንውን ለመረዳት የመንፈስ ዓይን ያሻል። የሚያሳዝነው የዘመኑ ሰው በራሱ ፍላጎትና ጥረት እየተንደረደረ የአውሬው መንፈስ በዘረጋው ወጥመድ ውስጥ እየወደቀ ከፍተኛ ፈተና ላይ ይገኛል። ግን የእርሻ ሕግ ሳያዛንፍ ይሰራል፡ ማለትም ሁሉም የዘራውን ያጭዳል።...

ዛሬ በየአቅጣጫው የሚገለጠው ይኸው የፍርድ ሥርዓት ሥጋ ለለበሰው በምኞቱና በወሬ ለሚነዳው የአለም ሕዝብ አይታየው እንጂ፣ በእግዚአብሔር ቀመር ምንም ሳይዛነፍ እየተከወነ ነው። የመጨረሻው ዘመን የፍርድ ሥርዓት ከተከወነባቸው ምስጢራት ውስጥ

የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ከኢትዮጵያና ከአለም ሕዝብ ዕጣ ፈንታ ጋር አያይዞ መግለጥና ያለንበትን ዘመን ትክክለኛ ምንነት መገንዘብ ያሻል፡-

ሀ. የ ‘9-11” ምሥጢር

- (መስከረም 1 ቀን 1966 ዓ.ም (September 11, 1974)
- መስከረም 1 ቀን 1994 ዓ.ም. (September 11, 2001)

ለ. የ”አዜብ” ንግሥት የ42 ዲግሪ የፍርድ ምሥጢር

- 5/18/2012 (ስለዳቦ)
- 6/29/2012 ( ስለሥልጣን)
- 8/25/2012 (የጠፋው ምልክት - ስለጽዮን ስለአምልኮ መገለጥ)

ሐ. የጽዮን ታቦት ምሥጢር - 29 ዲግሪ ሕግ (ተ=10፣ በ=9፣ ተ=10

መ. የፍርድ ሚዛን ቀመር፡ { “59 * 260} = { 42 ሲባዛ 365 ¼ }

ሠ. የመንፈሳዊ ታቦት ምስጢር = የመንፈስ ኃይል ሲገለጥ

= 10 ሲባዛ $(10)^2$ = 1000

ረ. የጽዮን ቃልኪዳን ምስጢር። = (12 x 12) + ( 7 X 13)

ሰ. ሰማያዊው ንጉሥ አለምን አሳልፎ የአለምን ንጉሥ ሽሮ የሚነግሥበት ምስጢር (8/25/2011 — 8/20/2012) ይኸ በእግዚአብሔር አንድ ቀን (360) የተለካበት ምስጢር ነው ። የኢትዮጵያንና የአሜሪካን ዕጣ

በእግዚአብሔር ስም በ9-11 ኮድ የቆለፈ ነው። እግዚእ የሚለው ስም በቀመር 360 መሆኑን ልብ በል።

እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ በመከወን ላይ ስላለው የፍርድ ዘመን አይናችንን የምንገልጥባቸው ምስጢራት ናቸው። እነዚህን ምሥጢራት ለመረዳትና ያለንበትን ዘመን እንድንዋጀውና በላያችን ላይ ካንዣበበው የሞት መንፈስ እንድንድን መጀመሪያ ልባችን ለእግዚአብሔር ማስማረክና እንዲምረን፣ እንዲራራልን፣ይቅርም እንዲለን መለማመን ያስፈልጋል። በምድርም ያሉ በሰማይም ያሉ ኃይላትና ሥልጣናት ሁሉ ለዚህ አንድ አምላክ የሚገዙበት፣ የሚንበረከኩበት ሰዓት በእግዚአብሔር የጊዜ መሥፈርት ሳይዛነፍ እየተከወነ ስለሆነ ጊዜውን መዋጀት ከሥጋዊና ከአለም አካሄዳችን ነቅተን የመንፈስን ፍሬ እንድናፈራ እንገደዳለን። ይህ ግን የፍርድ ሰዓት ነውና “ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ” ሁሉም ለራሱ ሊያውቅበት የሚያስፈልግበት ዘመን ነው። “ማራናታ”!!!

# ምዕራፍ ፬ - በ9/11 የተቀመረ የአዜብ ፍርድ።

## ሀ. የመጨረሻው መለከት የተነፋበት የ9-11 ምስጢር።

እግዚአብሔር ምድርንና ሰማይን የሚሰራ በስሙ ነው። የእግዚአብሔር ስም በሰማይም ያለ በምድርም ያለ መንግሥቱ፣ ኃይሉ ክብሩ የሚገለጥበት ነው። ስለዚህም በሰማይ ያለ ስሙን ስንገልጥ በግዕዝ ፊደል “ሠ”፣ በምድር አምላክ-ሰው ሰው-አምላክ ሆኖ ማዳኑን ስናውቅ ስሙን በሰባተኛው ፊደል “ሰ” እንገልጣለን። ስለዚህ የእግዚአብሔር ስሙ በሰማይ “ሥም” ተብሎ በንጉስነቱ ይታወቃል፤ “ብሩክ ይመጽእ በስመ እግዚአብሔር” ይል ዘንድ በስሙ ክብሮ የሚመጣውን ሰው (ሰብ) የሆነ አምላክ ለማመልከት “ስም” ብለን እንጽፋለን። ይኸንን በሰማይ ያለ ንጉሥ ስም ስናስብ “ሥም”፣ በምድር ሰው ሆኖ የተገለጠ አምላክን ስም ስናስብ “ስም” ያልንበት አጻጻፍ ወደ ግዕዝ ቀመር ስንቀይረው (ሥም=)9 — (ስም= 11) የሚለውን ፍጥረትን ሁሉ የሚከውንበትን ቀመር ይሰጠናል። እግዚአብሔር በስሙ ሁሉን ይከውን የሚችል መሆኑን ምልክት ይሆነን ዘንድ በ “9-11” ቀመር መልእክቱን ልኮልናል። በ “9-11” ኮድ ተገልጠው የምናያቸው የእግዚአብሔር ምልክቶች ዋናዎቹ እንዲህ እንረዳቸዋለን፦

፩. የእግዚአብሔር ስም ቀመር ጋር በተያያዘ የይሁዳ አንበሣ የሚል ስም ይዞ ለ42 ዓመት የነገሠው የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፣ የዳዊትን ወንበር፣ በክብረ ነገሥት ምስጢር የተካተተበት ምስጢር የተፈጸመው በመስከረም ፩ 1967 (9/11/1974) ዓመተ ምሕረት ነው። በዚህ ቀን **የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ይጀምር ዘንድ** የእግዚአብሔር ክብር ከኢትዮጵያ የለቀቀበት በእግዚአብሔር ስም ማሕተም በ “9-11” ኮድ ነው። ይህ ፍርድ የተከወነው በእግዚአብሔር ስም ወደ ዙፋን የወጡት ንጉሥ በ”ይሁዳ አንበሳ” በሚል መጠሪያ የታወቁ፣ “ሥዩመ እግዚአብሔር” ተብለው በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሢመት ነግሰው “እኛ” ተብለው የሚጠሩ ነበሩ። እኒህ ንጉሥ የለውጥ ነፋስ ነፍሶ ከክብር በኀደለ

ሁኔታ ከሥልጣን የለቀቁ ንጉሥ ናቸው። በእሳቸው ላይ ያደረው የመግዛት መንፈስ በደም የተሸለመ ነበር።

፪. የመጨረሻው ዘመን ፍርድ እየተከወነ መሆኑን የመጨረሻው ጥሩንባ የተነፋውና የአውሬው መንፈስ የ42 ዘመን አገዛዝ የጀመረው በ9/11 ኮድ በመስከረም ፩ 1994 (September 11, 2001) ዓመተ ምሕረት ነው። በዚህ ቀን 19 ሰዎች 4 አውሮፕላን ጠልፈው በአሜሪካ ምድር ከፍተኛ ጭካኔ የተመላበት ግድያን ፈጸሙ። በዚህ ቀን አሜሪካን ሀገር በደረሰው ፈተና የአለም መንግሥት ለፍርድ ሲቀርብና የአውሬው መንፈስ ሲገለጥ፣ በዚሁ ቀን ስምንት ሰዓት ቀደም ብሎ ኢትዮጵያውያን "ዕንቁጣጣሽ" እያሉ እንኳን ለቅዱስ ዮሐንስ" አደረሰህ እያሉ የአዲስ አመት መልካም ምኞት ሰላምታ ይለዋወጡ ነበር። ለትውልዱ የተሰጠው ምልክት በ9/11 የተላከበት ምሥጢር ከኢትዮጵያ አዲስ አመት ጋር ለምን ተገጣጠመ? ይህ ካርል ጁንግ የሚባል የስዊዘርላንድ ሳይኮሎጂስት "serendipity" (ግጥምጥሞሽ) እንደሚለው የነሲብ አጋጣሚ አልነበረም። ይህ ሰማያዊ ቀመር ግን መንፈሳዊ የሆነ የዘመኑ ማለቂያ መድረሱን የሚነግር መለኮት የተነፋበት ምሥጢር ነበር። የአውሬው መንፈስ ስራውን ፈጽሞ በ42 ዘመን አቆጣጠር ተለክቶ ወደ ባሕር እንዲላክ ዘመን የተቆጠረበት የጊዜ ቀመር ነበር። ዮሐንስ በራዕዩ በነገረን ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ሆነ። ስለአውሬው ስለተፈቀደለት የአገዛዝ ዘመን ሲነግረን ዮሐንስ እንዲህ አለ፡ "ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፥ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው።" (ራዕ. 13፡5) መንፈሱን የእግዚአብሔር መልዐክ ሲያስረው የሚሆነውን ሲነግረንም 'የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥ ሺህ ዓመትም አሰረው፥ ወደ ጥልቅም ጣለው አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።" (ራዕይ 20፡1-4). ዘመኑ የሚቆጠረው አንድም ሶስትም በሆነ ምስጢር በአውሬው መንፈስ አነዋወር ነው። ይሕ ዘመን ተለክቷል። የአውሬው መንፈስ ከባሕር ተጥሏል። ከ3000 ሰው በላይ እንዲሞት ያደረገው መንፈስ በኦሳማ ቢላደን ስም ነግሶ ለ126 ወራት ነግሶ ጊዜው ሲደርስ ተጠንቅቋል። የኦሳማ ቢን

ላደን ቀብር በባሕር ውስጥ ተፈጽሟል መባሉን አስብ፡፡ (ራዕይ 20፡1-5) ይኸ መንፈስ በሶስት ገጽታ ሲለካ በምድር ላይ የዘረጋውን የ42 ወር የፍርሃት የንግሥ ዘመንሥርዓት የሚሸፍን ሲሆን በባሕር ውስጥ ተቀበሩ መባሉ የትንቢት ፍጻሜ ነው። በራዕይ ፲፪-፲፫ እንደሚገለጠው “ባሕር” የአውሬው መኖሪያ መንፈስ ሆኖ ሲገለጥ “ብሔር” ብለን በእግዚአብሔር ስም ጋር የምንገልጠው የእግዚአብሔርን ስም ማደሪያ የሚመሳሰል መሆኑን ልብ ይሏል። ሁለቱም በቀመር በ=9፣ ሐ=3፣ ረ=6 በድምር 18 ይሆናሉ በመንፈስ ቀመር (6.6.6) ወደሚለው የስድስት (6) ቁጥር ምስጢር ብሎም የሰው ልጅ ቁጥር (ራዕይ 13፡17-18) የሚሆንበት ቀመር ነው።

፫. በእግዚአብሔር ስም የተባረከ ምድርን ለማመልከት የኢትዮጵያ ምድር ቃል ኪዳን የተሰራው በእግዚአብሔር ስም ለምስጋና ነው። በክብ የመንፈስ ቅርጽ የተሰመረ ምድር የተገለጠው በዘፍጥረት ፪፡፲፫ ላይ ነው። መንፈሳዊ ማደሪያውን የለካበት ስሙ የተሰጠ ለኢትዮጵያ ነው። ይኸው ስሙም “እግዚእ” የሚል ነው። እግዚእ በግዕዝ ቀመር 360 ዲግሪ ነው። ኢትዮጵያን በስሙ ኮድ የገለጣት መሆኑን የምናውቀው በስሙ የተጠናቀረ(ሥም/ስም = 9/11) የሚጀምር ሄኖካዊ የቀን መቁጠሪያ በምድሪቱ ላይ የተተገበረ መሆኑን ስናጤን ነው። ይኸውም በኢትዮጵያ አቆጣጠር መስከረም ፩ (September 11) ይባላል። የወሩ ስም እንደሚያመለክተው “መሰከረ” “መ” ይላል። በአራቱ ማዕዘን የሚገለጠውን የእግዚአብሔርን ስም በአራቱ ማዕዘን የሚመሰክር ነው። ይኸ የ44ቱ ታቦታት ምሥጢር ነው። (“ስም” የሚለው በቀመር 11 ነው በአራቱ ማዕዘን 44 ነው።) በኋለኛው ዘመን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣቱን “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ” እያለ የመሰከረ መጥምቁ ዮሐንስ ስለሆነ የምድሪቱ የንስሐ ምልክት ትሆን ዘንድ፣ እጆቿን በመዘርጋት ትታወቅ ዘንድ፣ በአጥማቂው ዮሐንስ ስም ትከብር ዘንድ፣ አዲሱ ዓመት “ቅዱስ ዮሐንስ” ይባላል። በውኃ የሚያጠምቅ ዮሐንስ የከበረባት፣ በውሃ ሀብት የምትከብር፣ የሕይወት ውሃ አምሳል መርገፍ (ራዕይ 22፡1-5) የሆነ አባይ ከማሕጸኗ የሚፈልቅባት ምድር ኢትዮጵያ ናት። የኢትዮጵያ ምሥጢር የእግዚአብሔርን ስም መመስከር ነው። “መሰከረ +መ”። ከክርስቶስ ቀድሞ በ6 ወር የተወለደው ዮሐንስ መስካሪ ነበር፡ስለ መንግሥተ ሰማያት። በመስከረም ፩ ስለመስካሪው

በተሰጠ ስም ወር ይቆጠራል። "መ" አራት ነው። ዛሬም የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲቆም ፍርድ በንግሥት አዜብ በኩል ይገለጥ ዘንድ የተመረጠች የቃል ኪዳን ምድር ኢትዮጵያ ነች። ይህ ማለት ኢትዮጵያ ንጉሡ በዘመን መጨረሻ ሲገለጥ በደብረ ሲና ፍርድ፣ በደብረ ጽዮን ሰርግ አብራው ምስጢሩን ትገልጣለች ማለት ነው። ግን ደብረ ጽዮን ተገልጣለች፤ የደብረ ሲና ስርዓት እየተከወነ ነው። የንግሥት አዜብ ምድር ኢትዮጵያ ከፈራጁ ጋር አብራ ልትፈርድ የነነዌን ሰዎች (120) ማለትም የጌታን ቤተሰቦች ወክላ በጽዮን ሥርዓት ሰማያዊ ሙሽራ ቤተክርስቲያንን ወክላ ትገለጣለች።

# ምዕራፍ ፭ - የንግሥት አዜብ ፍርድ በኢትዮጵያ ላይ

ኢትዮጵያ በሶስት አቅጣጫ በመጨረሻው ዘመን የፍርድ ሚዛን ተቃኝታለች።

## ሀ. የንግሥት አዜብ መነሳትን ያበሰረ

## የኢትዮጵያን የኢካቦድ ዘመን የጠነቀቀ ፍርድ።

“መንግሥቱ ኃይለማርያም ደማለኝ” ተብሎ የሚጠራ የኢትዮጵያ የ”ኢካቦድ ዘመን” በ42ኛው የመንፈስ ቀመር ከሁለት የሄኖክ ዓመት ቆጠራ በኋላ ይጠነቀቃል። ይህ ከየካቲት 1966 ጀምሮ እስከ የካቲት 2008 ድረስ ያለውን ዘመን ይሸፍናል። ይኼ ዘመን በጠቅላላው ይዘቱ በኢትዮጵያ ለ2000 ዓመት የዲያብሎስ መንፈስ የዘራውን የአለም መንፈስ፣ በተለይ ‘ጸራዊ ብእሲ” (ማቴ.13፡28) ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው፣ በምድሪቱ ላይ የተዘራ፣ የበቀለ፣ ያደገ ፍሬ ያፈራና በመጨረሻም የኢትዮጵያን የቤተ መንግሥት ቃል ኪዳን ከቦታው አንስቶ በምትኩ “የሰው ዘመን” የተከለውን የአውሬው መንፈስ የሚጠቀልል ዘመን ነው። የኢካቦድ ዘመን የተባለውም ከኢትዮጵያ ምድር የእግዚአብሔር ስም ስለተሳደደና በምትኩ የሰው አምልኮ በአዋጅ ስለተተከለ ነው። ይኸንን የኢትዮጵያን ቃልኪዳን ወደጎን የተወ የአለም መንፈስ አስወግዳ በምትኩ ኢትዮጵያን በክብሯ የምታቆም በማቴዎስ 12፡42 የተጠቀሰች ንግሥተ አዜብ የተባለች ከነነዌ ሕዝብ ጋር ቆማ በትውልዱ የምትፈርድ ነች። ይህቺ ሰማያዊ ክብር የለበሰች ንግሥት፣ ቀደም ብሎ በሰሎሞን ዘመን ጥበብን ፈልጋ የሄደች ንግሥት ሳባ በትንሳኤ ጉባኤ የምትገለጥበት ምስጢር ሲሆን ይህቺ ሰማያዊ ንግሥት እንድትገለጥ ግን ምድራዊውን የአለም ክብር የለበሱ ቀዳማዊት እመቤት አዜብ የተባሉ ሴት በዘመኑ መጠንቀቂያ ላይ (2000 ሚሊኒየም ሲከበር) በኢትዮጵያ የሥልጣን ወንበር ዙሪያ በአለም ጥበባቸው የተደነቁ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ባለቤት ሆነው ለ21 ዓመት

ከብረዋል። እኒህ በአለም ክብርና ዝና የተገለጡ በጦረኝነት መንፈስ የተገለጡ እመቤት በፍርድ ሰዓት ለምትገለጥ ሰማያዊዋ ንግሥት አዜብ ምልክት ሰጪ ነበሩ። የአለምን ጥበብ የሰማያዊው ጥበብ ይበልጠው ዘንድ፣ ብሉይ አልፎ ሐዲስ እንደሚተካ፣ የሰማያዊው ክብር ከአለም ክብር የሚበልጥ መሆኑ ምስክር ነበሩ። በዚህ የአለም ንጉሥ ዘመን መጠናቀቁ የሚመሰከርበት ሰማያዊ ተውኔት ነበር።

ለ. **ለእግዚአብሔር ስም ክብር የተሰጠ የ42 ዲግሪ ፍርድ።**

ይኸ የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ከመጀመሩ በፊት የእኔነትን መንፈስ የተከለው የእግዚአብሔርን ስም ይዞ ወደ ሥልጣን የወጣው የአጼውን መንግሥት ይመለከታል። ለእውነተኛው አንድ ፈራጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠበቀውን ስም ይዞ፣ ብሎም የኢትዮጵያን ክህነት ቃል ኪዳን ያለ ክህነት ቅባት በ"ይሁዳ አንበሣ" ስም የጠቀለለው በእግዚአብሔር ስም ከማለ በኋላ አምልኮቱን ወደ ሰው "እኔነት" መንፈስ ያወረደውን የአጼውን ዘመን ነበር። (ክርስቶስ በይሁዳ አንበሣ ስም ሲነግስ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ፈራጅ፣ ለቤተ ክርስቲያንም ሊቀ ካህናት ነው፡፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ በ"ይሁዳ አንበሣ" ሲጠሩ ሁለቱን የኢትዮጵያ ቃል ኪዳን መንካቱ የግድ ነበር።

**ይህ ቀመር በ'ይሁዳ አንበሣ" ስም የነገሰ "እኛ" ብሎ ነግሶ በ"እኔነት" አምልኮ በተገለጠ በ "ጃ" መንፈስ ላይ የተሰጠ፡ፍርድ ነው። (ጥቅምት 1924 - ጥቅምት 1966) በፈንጆች አቆጣጠር (9/11/31 — 9/11/73) ይሆናል። የ 9-11 ኮድን ልብ ይሏል።**

"እግዚአብሔር የለም" የተባለበት የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ከመጀመሩ በፊት 42 አመት በሥልጣን ወንበር ላይ የቆየው የአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ መሃላ ፈጽሞ የነገሰ መንግሥት ነው። ፈሪሀ እግዚአብሔርን ያማከሉ ንጉሥ ሆነው ለእግዚአብሔር ክብር ለመቆም የተነሱ ንጉሥ ነበሩ፣ በላያቸው የሰራው የአለም መንፈስ ግን የፈረሙበትን ቃል ኪዳን ወደ ግል አምልኮ እንዲያወርዱ አስገድዷቸዋል። ከኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን በፊት በዘመን መጨረሻ የፍርድ ሚዛን

የተመዘነ በእግዚአብሔር ስም ሥርዓተ ሢመትን የፈጸመ፣ ይኸ ራሱን "የይሁዳ አንበሳ" ብሎ የሚጠራ ነጋሲ መንፈስ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ በወጣቱ ተፈሪ በኩል ተገልጧ ሰርቷል። ይኸው የአጼው መንግሥት የተቃኘበት ሥርዓት በአዳኙ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም (ራዕይ 5፡5) የተጠራ፣ የሥላሴ ኃይል ተብሎ የነገሠ መንፈስ ሲሆን በምሕረት አምላክ ስም ነግሶ ዙፋኑን ግን የሰው አምልኮ እንዲተካበት ያደረገ መንፈስ ነው። ራሱንም "ሥዩመ እግዚአብሔር" ብሎ ያዋቀረ፣ በፍሬ ከናፍር መገለጫው "እኛ" ብሎ የሚጠራ የስላሴዎችን ሶስትነት የወከለ መንፈስ ሳለ የሥላሴዎችን በአንድ አካል የሰየመ የዳዊት ወንበር ቃል ኪዳን ወደ ግላዊ ሥርዓት ሊያወርድ የተቀመረ ሆኖ ነበር። ይህ ከጥቅምት 23፣ 1923 ጀምሮ እስከ ጥቅምት 1966 ያለውን የ42 ዲግሪ ዘመን ይሸፍናል። ይኸ መንፈስ ራሱን በሥዩመ እግዚአብሔር መሰየሙ የክብሩ መገለጫ ሆኖ ቢቆይም፣ ከኢትዮጵያ ወንበር ከለቀቀ በኋላ "ራስተፋሪያን" በሚል አምልኮቱን በላቲን አሜሪካ የቀጠለ መንፈስ ነው። ….ለማስታወስ ያህል በአውሮጳ ጀርመን የበቀለው የ"ጀ"መንፈስ የላቲን የሥጋ ቋንቋ ያበቀለው ሲሆን በላቲን አልፋቤት ቁጥር 10ን የሚወክል መንፈስ ነው። "ኢየሱስ የግል አዳኝ ነው።" ብሎ የተነሳው የሉተር ብሎም የካልቢንን መንፈስ ለማራባት በ"ጅሰስ"(Jesus) ስም የተገለጠ "እኔ ኢየሱስ ነኝ" የሚል በክርስቶስ ስም የእኔነትን የግለኝነተን አምልኮ ያስፋፋ፣ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አቡነ ዘበሰማያት" ብሎ ያስተማረበትን የ"እኛ" መንፈስ የተቀናቀነ፣ ብሎም ከሁለቱ አቢይ ሕግጋት "ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ" የተባለው የፍቅር ሕግ የተገዳደረ የራስ ወዳድነት መንፈስ ነው። የሴቲቱን "ብጽእትነትና" የቃና ዘገሊላ ምስጢር የሚያቃልል፣ ኢየሱሰሰ የግል አዳኝ ነው የሚል አምልኮ የዳበረበት የአምልኮ መንፈስ ነው። "ጀ" ከዘጠነኛው የእንግሊዝ አልፋቤት ከ "አይ"፡(እኔ) የመነጨ ነው። በአማርኛ "ጀ" የሚለው ፊደል በቋንቋ ቀመር ግዕዝን ከ"እኔነት" መንፈስ ለመሸፈን የሰው ልጅ ጠላት የተባለ ዲያብሎስ ከሰው ልጅ አእምሮ እያፈለቀ የሚበትነውን የልሳን አረም ለመከላከል ይችል ዘንድ፣ ስለዚህም አማርኛ ሙዳየ ልሳን ሆኖ ይሸፍነው ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ጠባቂነት የተከወነ ፊደል ነው። በ"ጸወርተ ልሳነ-ግዕዝ" ምስጢር የተያዘ ነቢዩ ሶፎንያስ የገለጠው (3፡9) "ንጹሕ ልሳን ግዕዝ"ን "የሰው ልጅ ጠላት" ከተባለ በመንግሥተ ሰማያት እንደ አረም ከሚዘራ የአለም መንፈስ ለመጠበቅ የተሰየመ ድምጸት ነው። (የአማርኛው ጀ ግን በአምስት አወቃቀር የተነደፈ ፊደል ሲሆን

አምስቱን አዕማደ ምስጢራት እንዲወክል ተደርጎ የተቀረጸ ፊደል ነው።) የ “ጀ” ን ቅርጽ ከዚህ በታች ተመልከተው፦


(1)

(2)

(3)

(4)

(5)



ተመልከት የግዕዝን ምስጢር! በአውሮፓ የ “ህ” ፊደል በጀመርን ምድር ሲፈልቅና እነሉተር ክርስቶስ “የግል አዳኝ ነው” ሲሉ የግዕዝን ሰማያዊ ምስጢር ከአውሮጳ ወረራ ለማዳን በግዕዝ ፊደል ሰባት ፍጹም ቁጥር የሚወክሉ ፊደል የረቀቀ ቋንቋ በቃል ኪዳን ምድር ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ አድጓል። ይኸንን የሰው መንፈስ ከ “|” አስተሳሰብ

ለመከላከል በአምስት ስኬት የተቀረጸ ፊደል ጀ አንዱ ሲሆን የሚወክለውም ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ ቀኝ መጦ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው ሆኖ ራሱን ባዶ አድርጎ በመስቀል ላይ ሞቶ በትንሳኤ ሙታን ሥርዓት የእግዚአብሔርን መንግሥት የመሰረተበትን ምስጢር ነው። ጀ የተሰራባቸው በተራ ተዋረድ የተቀረጹ ምልክቶች የሚያመለክቱት የአምስቱ አዕማደ ምስጢራትን ፈለግ ነው። (የ ጀን ስእል በሥዕሉ ተመልከት።) በመንበሩ ካባቱ ጋር ሁል ጊዜ የሚኖርበት ምስጢር በ(1) ተራ ቁጥር ወደ ምድር የወረደበት ምስጢር በ (2) ተራቁጥር የተገለጠው ነው። በ (3)ኛ ተራ ቁጥር በአልቦ የተመሰለው “0” የሚያመለክተን ጌትነቱ በምልዐት ሳለ ራሱን ዝቅ አድርጎ ራሱን ባዶ አድርጎ የማይሞተው መሞቱን በሞቱ ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን ነው፡ በስሙ “26” ከብሮ ሳለ (ብሩክ ይመጽእ በስመ እግዚአብሔር” እንዲል ዳዊት) ግን በመስቀል መሰቀሉን እናያለን። በተራ ቁጥር  አምስት ሕይወት መስጠቱን (ከ (2) ጋር ይመስል ዘንድ፣ ብሎም በትንሳኤ ሙታን ስርዓት በጽዮን በጉ “ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ” ተብሎ መገለጡን በ(5) ተራ ቁጥር የምናመሰጥርበት ነው። የሰው መንፈስ የሆነ የአውሮፓን “J” ግዕዝ እንዴት ወደ ሕይወት ቋንቋ እንደሚቀይረው እናያለን።

በዚህ ከአውሮፓ ማኅጸን በፈለቀ በ”ጀ” መንፈስ ምክንያት በኢትዮጵያ ነፍስ ውስጥ ሠይፍ አልፏል። ሰይፉ ግን ይነቀላል፣ የኢትዮጵያ ቃል ኪዳንም ከወደቀበት ይነሳል። በአጼው ዘመን በ”ሥዩመ እግዚአብሔር” መንፈስ ነግሶ በእኔነት የጨረሰው የዘውድ መንግሥት ምድሪቱን ለኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን አመቻችቶ ተፈጽሟል። እኔነትን ከማንገስ ባሻገር የኢትዮጵያን የቃል ኪዳን መሠረት የሚያሳድድ፣ ጭራሽም እግዚአብሔር የለም የሚል መንፈስ ሲሆን፣ በሄሮድስ መንፈስ ሴቲቱንና የሴቲቱን ልጆች ከየገዳማት ለማሳደድ የተገለጠ የኃሳዊ መሲህ መንፈስ ነው። (ይኸ ግን በራዕይ 11፣ 12፣ 13) የተጠቀሰው የአውሬው ዘመን ይጠናቀቅ ዘንድ የፍርድ ምስጢርን የምትፈታ የንግሥተ አዜብ ዘመን ይጀምር ዘንድ የሆነ ነው።

## ሐ. “ሕዝቡም ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ ይሞት ዘንድ እንዲሻለን…”

ሊቀ ካህናት ቀያፋ (ዮሐ.11፡50)

ይኸው ኢትዮጵያን በመለኮት ቅኝት የሚያይ ሰማያዊ የፍርድ ሚዛን እንዲሁ በነሐሴ ወር 2004 ዓ.ም. የፍርድ ሚዛኑን በምድሪቱ ላይ ተክሎ በ42 ዲግሪ ሚዛን የኢካቦድ ዘመን መጠቅለያ ይሆን ዘንድ በሰው ውሳኔ የተለያዩትን የኢትዮጵያን የሰማያዊ ቃል ኪዳን ሁለት አይኖች ማለትም የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነትን ወንበሮች ለፍርድ ጠርቶ ከውኖአል። በመሆኑም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ለ21 ዓመት እንዲሁም ብፁዕ ፓትርያርክ ጳውሎስ ለ21 ዓመት ከገዙ በኋላ በአንድነት በዕረፍት መንፈስ ተጠርተዋል። ይህ ከግንቦት 20 1982 በኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ ግንቦት 18፣ 2012 በፈንጆች አቆጣጠር ያለውን ጊዜ ይሸፍናል። (ሁለቱ ቀናት በግሪጎሪያንና በጁሊያን ካሌንደር የተጠቀሱት) በሁለቱ በኩሮች መጠራት ውስጥ የሮምና የኢትዮጵያ ፍቅር ስለሚገለጽ ነው። ይህ የፍርድ ክንዋኔ የንግሥተ አዜብ ምስጢር የታወጀበት (አዋጅ፣ አዋዲ፣ አድዋ) የግዕዝንና (፩) የላቲንን (፵፪) ምስጢር ያቀፈ፣ የኢትዮጵያንና የሮምን ግንኙነት መንፈሳዊ ግንኙነትና ልዩነት የሚመሰክር የቤተ ክርስቲያን ቃል ኪዳን ይዘት ውስጠቱ የተገለጠበት ምሥጢር ነው። የክርስቶስ ባሕሪ አንድ ወይስ ሁለት? 6 የሰው ቁጥር ነው፤ 7 በእግዚአብሔር ያለ ዕረፍት ነው። የአምልኮን መንፈስ በ (6 ሲባዛ በ7) ምስጢር በ42 ቁጥር የተጠነቀቀ ምስጢር ነው። (21 ዓመት ቤተ ክህነት፣ 21 ዓመት ቤተ መንግሥት) ተብሎ የተቀመረ የንግሥተ አዜብን መነሳት ያበሰረ የፍርድ ቀመር ነው።

እኒህ ከላይ የተጠቀሱት መላምቶች አይደሉም። ልካቸው በሂኖክ የጊዜ አቆጣጠር ቀመር የተጠነቀቀ ነው። (በሚቀጥለው ሠንጠረዥ የአዜብን ፍርድ ሄኖካዊ ቀመር በአጭሩ ተከታተል)።

# ምዕራፍ ፮- ኢትዮጵያን የወጋ

## የአውሬው መንፈስ ማን ነው?

የሰባ ሙክት ሾተል ይልሳል እንዲሉ አውሬው “የመውጊያውን ብረት” ኢየሱስ ክርስቶስን የሚቃወም መንፈስ ሲሆን፣ በተዋሕዶ ምስጢር ሰው የሆነውን አምላክ የሚወጋ በ42 ዲግሪ በተቆጠረ ቀመር የነገሰ መንፈስ ነው። በዘፍጥረት ምዕራፍ ሶስት በእባብ መልክ የተገለጠው ዲያብሎስ የአውሬው መሠረት ነው፡ “በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።” (ዘፍ. 3፡15) በኢትዮጵያ ምድር በተገለጠበት መልኩ ይኸ ሴቲቱን የሚያሳድድ መንፈስ “ተዋሕዶን ማውረድ” ችለናል ብሎ የኢትዮጵያን ቃል ኪዳን በመውጋት፣ የተገለጠ ነው። የአውሬው መንፈስ፣ የመስቀሉ ጠላት ነው። የክርስቶስን በተዋሕዶ ምስጢር ከድንግል መወለዱን የሚጻረር መንፈስ በተለያየ መልኩ ሴቲቷንና በቃል ኪዳን የተሰጣትን ምድር ወግቷል። ለሁለት ሺ ዘመን በክርስቶስ መንግሥት አረም ሆኖ የቆየ በመጨረሻው ዘመን ሴቲቱን ለ42 ዘመን (1260 ቀን) ያሳደደ ይኸ መንፈስ ከባሕር ማዶ እየተንደረደረ የሚመጣውን የአለም መንፈስ ጨምሮ በውቅሩ የአውሬው ባሕሪ ነው። ከላይ እንተገለጠው የኢትዮጵያን፣ የምስለ ፍቁር ወልዳን የቀመር ስርዓት ተከትሎ ኢትዮጵያን የወጋ መንፈስ ነው።የኸ መንፈስ የጽዮንን ቀመር አስመስሎ የሚሰራ ሲሆን በቀመሩ መሠረት

ኢትዮጵያን የወጋ የአውሬው መንፈስ = (12 በ 12) + (13 በ 7)

የሚል ነው። ይኸን የሕይወት ተመን ተጣብቶ ኢትዮጵያን የወጋው ሴቲቱን የሚያሳድድ መንፈስ የቀደመው እባብ የወጠነው ሴራ ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ ቃል ኪዳን ጋር የሚያይዘው ግን በቀጥታ በጽዮን ሙሽራውና ሙሽራይቱ የሚገለጡበትን ቀመር ተጠቅሞ ነው። በ144

በ"አየሰሰ" መንፈስ ኤርትራ ባሕር ላይ አንገቱን ያሰገገ፣ በ '13" በ"ሰላም" መንፈስ ኢትዮጵያ ላይ መንገስ የቻለ የአለም መንፈስ ነው። አንባቢ ልብ በል፤ "ኢሳያስ" የሚለው ስም በቀመር 144፣ መለሰ የሚለው ቃል በቀመር "13" ናቸው። ይኽ መንፈስ ቀደም ሲል በእስራኤልና በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ግንኙነት መካከል ተገልጦ ታይቶአል። ይኸውም መሠረቱ ሥጋዊ የሆነ ጥልቅ፣ በሙሴ ዘመን የተገለጠ መንፈስ ነው። በዘር የመለየት መንፈስ መሠረቱ የተጣለ በሙሴ ዘመን በዘኁልቆ ፲፪ ላይ እንደተገለጠው ሙሴ ኢትዮጵያዊቱን ሴት በማግባቱ እስራኤላዊ ባለመሆኗ ከቤተሰቦቹ በደረሰበት ተቃውሞ የተገለጠ መንፈስ ነው። ሙሴን "የደም ሙሽራዬ" ያለች ኢትዮጵያዊቱ ሴት ግን ስለቤተክርስቲያን አምሳል ናት።ስለዚህም ይኽ ኢትዮጵያን የወጋ የአውሬ መንፈስ በኤርትራ ባሕር ከሰጠመው የፈርኦን መንፈስ ጋር መሠረቱ አንድ ነው። የቀደመው እባብ ነው። በራዕይ ፲፪ ላይ የተጠቀሰው የአውሬው መንፈስ ኢትዮጵያን ሊያሳድድ ሲነሳ በሰዎች ላይ አድሮ ስራውን ገልጧል። ኤርትራን የቆረሰው፣ በማሌሊት ተደራጅቶ ለጽዮን መሬት የዘመተው መንፈስ የነዚህ የሁለቱ ቀመሮች ውጤት ነበር። "አሰየሰ" የሚለው ቀመር 144 ነው። በ"ሰላም" መንፈስ ቁልቁል የወረደው የ"13" ቀመር ነው። ከአንድ ጸጉር ላይ የተሰነጠቁ ሁለት የጸጉር ጭራዎች እንደሚኖሩ ይኽ የሴቲቱን የቃል ኪዳን ምድር የወጋው መንፈስም እንዲሁ ሁለት አካል ያለው የዘር/የሥጋ መንፈስ ነው። ይኽ የሥጋ መንፈስ የሴቲቱን ቃልኪዳን የታቦተ ጽዮንን ተዋሕዶ መሰረት ለማሳደድ በግልጥ ተነስቷል። በ"144" የተሰለፈው ከባሕር ዳር ቆሞ ታየ። በኤርትራው መሪ ያደረው መንፈስ የ"144" (አሰየሰ) መንፈስ ነው። በጠ/ሚኒስቴር መለስ ያደረው ስማቸውን ከ"ለገሠ" ወደ "መለስ" ያስቀየረው የ"13" ቁጥር ቀመር ነው። ሁለቱን አጋጥመው፡

ሴቲቱን የወጋው መንፈስ = 144 (አሰየሰ) + 13 (ሰላም) * (-7)

በቀመር (-7) ብለን ያቀረብነው በዚህ ቁጥር የወከልነው ከእግዚአብሔር ያልሆነን ሰላም በ"አንድ ለአምስት" የተሰቀዘች ነፍስ የምትለፈልፈው "ሰላም ነው?" የሚያሰኘውን ሰላም ነው፡፤ ይኽ ለዘመናት ሴቲቱን ያሳደደ መንፈስ ከሴቲቱ የአስራት አገር ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ክብር እንዲለቅና የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን እንዲቆጠር እውን ያደረገ፣

ከአእምሮ የመነጨ የእኔነትን መንፈስ የሰበከና በምድሪቱ ላይ ያስፋፋ መንፈስ ሲሆን፣ በምድሪቱ ላይ "እግዚአብሔር የለም" እስከ ማለት የደረሰ በመጨረሻም በ42 ዘመን ግዛት በምድሪቱ ላይ ተንሰራፍቶ፣ የተገለጠ የአለምን ሥልጣኔ ወደምድሪቱ በመሳብ፣ የባቢሎንን ግንብ የሚገነባ የስድብን መንፈስ፣ የቃል ኪዳንን ባንዲራ ያወረደ፣ የማዋረድን መንፈስ የተቃኘ፣ ዳቦን በሰው ልብ የሚያነግሥ መንፈስ ነው። ለምድሪቱ ከተሰጣት ጸጋ ጋር በተጻራሪነት የቆመ የሥጋን መንፈስ፣ የባዕድ አምልኮን መንፈስ ያራመደ ነው። ይኸንን መንፈስ የሚያራምደውን ዲያብሎስን ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 13፡28 ላይ የ"ሰው ልጅ ጠላት" (ጸራዊ ብእሲ) ብሎ የገለጸው መንፈስ በተለያየ መንገድ ገዝፎ በሀገሪቱ ላይ ተገልጧል። ዝርዝሩን በጠቅላላ መጥቀስ ባይቻልም፡ ከብዙ በጥቂቱ፡ "የአብዮት መንፈስ፣ የኢህአዴግ መንፈስ፣ የወያኔነት መንፈስ፣ የደርግነት መንፈስ፣ የአማራነት መንፈስ፣ የትግሬነት መንፈስ፣ የደቡብነት መንፈስ፣ የወያኔነት መንፈስ፣ የቅንጅትነት መንፈስ፣ የግራ አብዮተኝነት መንፈስ፣ የኦሮሞነት መንፈስ፣ በጠቅላላው የዘርና የጎሳ መንፈስ፣ የኢህአፓነት መንፈስ፣ የመኢሶንነት መንፈስ፣ የኢዲዩነት መንፈስ፣ የመሳፍንትነት መንፈስ፣ የጭቁንነት መንፈስ፣ የማርክሲዝም መንፈስ፣ የጴንጤነት መንፈስ፣ የኦርቶዶክስነት መንፈስ፣ የሉተርነት፣ የአረብነት መንፈስ፣ የአይሁዳዊነት መንፈስ፣ በእኔነት የሰለጠነ ግላዊ ጥቅምንና በሥጋ የመድለብን ሥርዓት የሚያራምድ የኃይማኖተኝነት መንፈስ፣ የገንዘብ መንፈስ፣ በሀብት፣በሥልጣን ወይም በአምልኮ የተገለጡ ሟች ሰዎችንና ግለሰቦችን አምላክ የሚያደርግ የአምልኮ መንፈስ፣ የባዕድ አምልኮ መንፈስ፣ የጦረኝነት መንፈስ፣ የአሜሪካዊነት መንፈስ፣ የአውሮፓዊነት መንፈስ፣.....ወዘተ ሁሉ በአንድነት በሰው መንፈስ የተቃኘ የአለም መንፈስ ነው። የሰው መንፈስ ነው። ከ "6" የመነጨ ነው። በ666 መንፈስ የተጠነጠነ ነው። ይኸ ሁሉ መንፈስ የኢትዮጵያን መለኮታዊ ቃል ኪዳን መንፈሳዊ የቃል ኪዳን መንፈስ ዝቅ የሚያደርግ የአለም መንፈስ ነው። የኢትዮጵያ መልክ አይደለም፣ ኢትዮጵያን የሚያቆረቁዝ መንፈስ ነው።

በጠቅላላው ይኸ የመናፍስት ጥርቅም በግዕዝ "ጸራዊ" በሚል የሰው ልጅ ጠላት የሆነ ዲያብሎስን የሚያመለክት ነው። የሰው ልጅ ጠላት የተባለ ዲያብሎስ በሰው ልጅ ቁጥር የተተመነ ሲሆን "666" ተብሎ ይታወቃል። (ይኸውም በግዕዝ ቀመር ጸ=600፣ ረ=6

ና ወ=60 በድምሩ 666 የሚሆን ነው።) የእግዚአብሔርን መንበር የሚሸከሙትን “ጸወርተ መንበረ” ብለን እንደምንገልጠው በመስቀሉ “ተ” ላይ ራሱን አሳልፎ ሰጠ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወራሽ የሆነውን የጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ የሚቃወም የኃሣዊ መሲህ መንፈስ በጠቅላላው “ጸወር” ተብሎ ሲታወቅ ‘ጸወርተ” ከሚለው ቃል “ተ” የሚል የመስቀልን ምልክትን ቀንሶ በተገለጠ ቃል መታወቁን ልብ ይሏል። መስቀሉን ይክዳል፣ ከድንግል ተወልዶ ሰው ሆኖ አዳምን የማዳንን ምሥጢር በመስቀል ላይ የሰራውን ክርስቶስን፣ እናቱን ድንግል ማርያምን ብሎም ለሴቲቱ በቃል ኪዳን የተሰጠውን የቃል ኪዳን ምድር ይወጋል።

ይህ መንፈስ የክርስቶስን መንግሥት አመሳስሎ ስለሚሰራ አንድም ሶሰትም በሚል አደረጃጀት ይገለጣል። በ6ኛው ቀን የተፈጠረ አዳምን ስለሚያመለክት የሰው ቁጥር “6” የሚባል እንደመሆኑ፣ ሰው ደግሞ በአንድም በሶስትነትም የሚገለጡ የስላሴዎች የመንፈስ ማደሪያ ስለሆነ ሶስት ሰው ለማመልከት (6.6.6) ብለን የምናውቀው ነው። የዚህን ቀመር ብሂል በጥልቀት የምንረዳው ይኸው የአለም መንፈስ የሚፎካከረውን የእግዚአብሔርን መንግሥት መገለጫ ስናስብ ነው። የፈጣሪ ስሙ በግዕዝ “እግዚአብሔር” ብለን ስንጠራ “እግዚአ” የሚለው ስሙን “ብሔር” የሚለው ደግሞ ማደሪያውን የሚያመለክት ነው። ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ እንደሚሆን፣ በሶስቱ ሥላሴዎች የምናስበው የሶሰት ሰው ምልክት ሶስት በቁጥር 6 የሚገለጡ አካላትን ያሳስበናል። የዚህን ቃል ማለትም “ብሔር” የሚለውን ወደ ግዕዝ ቀመር ስንቀይረው (በ=9፣ ሐ=3፣ ረ=6 ጠቅላላ =18) ሲሆን እናያለን። የእግዚአብሔር ማደሪያው የምንለው “ብሔር” የሚለው ቃል፣ አውሬው ከሚወጣበት “ባሕር” ከሚለው ቃል ጋር በዮሐንስ ራዕይ ከሚገለጠው የአውሬው ማደሪያ ጋር ማገናዘብ ያሻል። ይኸ ቀመር “18” የሶስት ስድስት (6) ድምር መሆኑን ልብ ይሏል። ስለዚህም (6+6+6) ብለን የምናውቀው የሰው ቁጥር ይኸ ነው። ስለዚህም የአውሬው መንፈስ 666 ሆኖ በሰው ተገለጠ ስንል የእግዚአብሔርን መንግሥት ተቃውሞ የሚሰለፍ ሰው ውስጥ አድሮ የሚሰራውን አንድም ሶስትም ሆኖ የሚገለጠውን መንፈስ ነው። በአርዮስ ላይ አድሮ የሰራው መንፈስ ጥሩ ምሳሌ ነው። የ666 መንፈስ አድሮበት የእግዚአብሔርን ልጅ “ፍጡር ነው” ብሎ ተናገረ፡ (ሎቱ ስብሐት!)። ማርክስና ኤንግልስ ብሎም ሌኒን የእግዚአብሔርን

*መንፈስ ተቀናቅነው የዳቦን አምላክነት ሲያነግሱ በውስጣቸው የሰራው የ666 መንፈስ ነው። ስለዚህ ከሰው አእምሮ የሚመነጭ መንፈስ በሰው ልቦና ውስጥ ሲሰርጽና የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚቀናቀን አቋምን ሲገልጽ በውስጡ የዲያብሎስ መንፈስ የተባለ በ666 የሰው ቁጥር የተወከለ መንፈስ ይሰራል ማለት ነው።*

*በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔር መንፈስ ርቆ በሰው ቁጥር የከበረ በ666 መንፈስ የተቃኘ መንግሥት የአለም መንግሥት ይባላል። በዚህ አይነት የእግዚአብሔር ቅባት የጎደላቸው የእግዚአብሐርን መንፈስ የካዱ መንግሥታት በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀምጠው "መንግሥቱ ኃይለማርያም ደሣለኝ" ብለን በሰየምነው የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ውስጥ ይካተታሉ። በኢትዮጵያ ላይ 9/11/1974 ጀምሮ የሰፈነውን የአለም መንግሥት በሁለት እርከን ይገለጥ እንጂ (ማለትም ደርግና ኢህአዴግ ተብሎ) የሕዝብን መንግሥት ከእግዚአብሔር መንፈስ የሚነጥል የሥጋን ኃያልነት ከፍ የሚያደርግ፣ 'የምሥራቃዊነትንም ሆነ የምዕራባዊነትን ሽቶ የተቀባ በዘር በጎሳ፣ በቋንቋ መከፋፈልን የሥርዓት መንደፊያ የሚያደርግ የአለም ንጉሥ የሚበትነው መንፈስ ነው። ይህ መንፈስ ከኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ስጦታ ጋር የሚቃረን፣ የእውነተኛ የይሁዳ አንበሳ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጫ የሆነውን የቃልኪዳን ባንዲራ የሚረግጥ፣ ብሎም በአንበሳው ምትክ አንድ የድርጅቱ አካል የነበረ ተስፋዬ ገብረ አብ የሚባል ጸሐፊ በመጽሐፉ ያሳፈረው እውነት ከሆነ፣ በኅቡዕ አንባሻ ምስልን የያዘ ባንዲራ ነው። የብርሃንን አንድ መንፈስ፣ በሥጋዊ ብዙ መናፍስት ቀይሮ በምድሪቱ ላይ የበተነ መንፈስ ነው። በ"ይሁዳ አንበሳ" በሚቀመጥበት የቃል ኪዳን ባንዲራ ላይ የዳቦን አምልኮ ያነገሰ ነው፡፡ አንባቢ ልብ በል፣ "አንበሳ" የሚልና "አንባሻ" የሚሉ ቃላት የግዕዝ መሰረታቸው፣ "አነበሰ" ነው። ችግሩ የመጣው "ሸ" የሚለው በግዕዝ የብርሃን አምድ ውስጥ አለመኖሩ ነው። ይኸ ፊደል "ሸ" ግን አዳም "ሰብ" የመሆንን የገነት ብሂል በትዕቢት ሲተው የተሰጠው ጥረህ ግረህ" ብላ ያለውን ትዕዛዝ ሲሆን፣ የአዳም ተስፋው እስኪፈጸም ሰው ሊሄድ የሚገባውን የቅንነት ቀንበር ያመለክታል። "ሰ" ና ሸ በሁለት አቅጣጫ የሚሄድ የብርሃንን ጨረር እንደጽድቅ ጉዞ ይወክላሉ። "ሰ" ስለብርሃን ጉዞ ነው፣ የአለም አካሄድ "ሸ" ነው። በዘፍጥረት 2፡7 የተሳለው የነፍስ ጉዞ፣ በ14 ቀመር ያዕቆብ ያገለገለው አገልግሎት ለዚህ አምሳል መርገፍ ነው።*

“ሰብ” ለክርስቶስ ነው፤ “ሸ” ብርሃን በሌለበት ለሚጓዝ ነው። የግብጥ ጉዞ ነው። ያዕቆብ በላባ ቤት ለራሔል ስለራሱ ፈቃድ በ “ሸ”፣ ለልያ ስለእግዚአብሔር ፈቃድ በ”ሰ” መንፈስ አገለገለ። የጽድቅ ጉዞ ነው።”ሸ” ለ “ሸክም” ነው። ሰ ለብርሃን ቃል ኪዳን ነው። ሰብ 16 ነው። አዎ የግብጽ ጉዞ ጽዮን ለመግባት የሚጓዙት የጽድቅ ጉዞ ነው። የድንግል ማርያም የግብጽ ጉዞ “ልጄን ከግብጽ ጠራሁት፡፤” የተባለው ይፈጸም ዘንድ የቃል ኪዳን ጉዞ ነው።

በአጭሩ የአውሬው መንፈስ በዘመናት ትግሉ ያነጣጠረው የኢትዮጵያን መለኮታዊ ስጦታ ማንቋሸሽ ነበር። በሴት ተሰይማ የምትጠራ ኢትዮጵያም የመጨረሻው ዘመን የአውሬው መንፈስ የሚያሳድዳት መሆኑን በዕጣዋ የተቀበለችው ነው። ማለትም ሴቲቱን የሚያሳድድ ዲያብሎስ ለ42 ወር እንደሚነግስ፣ ለድንግል ማርያም የተሰጠቺን በአሥራትነት የተሰጠች ሀገር ለመቆጣጠር ለ400 ዓመት ከፍተኛ ትግልን ያደረገው የአለም ብሎም የአውሬው መንፈስ ሙከራው ተሳክቶለት፣ በማርክስዝም መንፈስ፣ በምሥራቃዊነት መንፈስ፣ በምዕራባዊነት መንፈስ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ሁለቱን የኢትዮጵያን አይኖች (ማለትም የዮቶርንና የመልከ ጸዴቅን ወንበሮች ) መጠንቆል ችሏል። የሀገሪቱን መንፈሳዊ ቃል ኪዳን አሳድዷል። በመልከ ጸዴቅ ወንበር ላይ የከበረው መንፈስ አሮን ለእስራኤል ከጥጃ ምስል እንደሰራላቸው የተቀደሰች መንፈሳዊ ታቦትን ለሚያከብር ሕዝብ የራሱን ምስል ከመድኃኔ ዓለም ስም ጋር አወዳድሮ አሮን ለእስራኤል ጥጃን እንደቀረጸላቸው የሰውን ምስል በጣኦትነት ያቆመ መንፈስ ነው። ብሎም የአሐቲ ቤተ ክርስቲያንን ጠባቂ ሲኖድ የበተነ በመሆኑ  የቤተ ክርስቲያንን ቃለ-አዋዲ ለመሻር የሚፈልግ መንፈስ ነው።

በጠቅላላው የአውሬው ስራ በኢትዮጵያ ምድር በሶስት መንገድ ተገልጧል፦

**ሀ. <u>አሐቲ ቤተ ክርስቲያንን የሚጻረር በ”አለትነትና”   በመጋቤነት” መንፈስ የተገለጠ የቤተ ክርስቲያን ፈርኦኖችን ያፈራ የአውሬው መንፈስ</u>** ፡ (ይኸ አምልኮን ከእግዚአብሔር ወደሰው ያወረደ መንፈስ በመጨረሻም ጣኦት ያስቆመ መንፈስ ነው)

ይኸ አሐቲ ቤተ ክርስቲያንን ሰንጎ ይዞ የሚያስጨንቅ የ “ሰአለከ” (99) መንፈስ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚሰራ የአውሬ መንፈስ ሲሆን የአሐቲ ቤተ ክርስቲያን ቃል ኪዳን

እየተፈታተነ ያለ በታች መንፈስ ነው። የኢትዮጵያና የሮም ቤተ ክርስቲያን የሚፈረጁበት ቀመር ነው። (ሮም "አለት" በሚል መሪ ቃል የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ በተቀበለ በጴጥሮስ ስጦታ፣ ኢትዮጵያ በአጥማቂነት በዮሐንስ መክሊት (ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎ የሴቲቱን ቃል ኪዳን እንደወከለ፣ ኢትዮጵየም በቀን ቆጠራዋ እንዳከበረችው ) እንዲሁም በጃንደረባው መክሊት ለአሕዛብ በተላከ በሐዋርያነት ሚዛን ላይ ይሰፈራሉ።) ሰአለከ የሚለው ቃል "ሰአለ" ከሚለው ለመነ ከሚል የግዕዝ ቃል የወጣ ነው። ሰው ለሕይወቱ የሚያስፈልገው፣ ሊማልድና ሊለማመን የሚያስፈልግ ፈጣሪውን ነው። ይኸ አዳም የተፈጠረበት አላማውና ምሥጢሩ ነው። ይኸ የመለመን፣ እጅን ወደ እግዚአብሔር የመዘርጋት የተፈጥሮ ሥርዓት ከእግዚአብሔር በስተቀር ወደ ሌላ አካል ሲሄድ ወደ ጣዖት አምልኮ ይለወጣል። ከኔ ሌላ የምታመልከው ጣዖት አይኑርህ ለሚል አምላክ፣ እግዚአብሔርን የሚያስክድ መንፈስ ጸያፍ ነው። ይኸንን አይነት በ99 መላእክት ጉባኤ የፈጠረ፣ እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ወደ ምድር በወረደበት ጊዜ "እኔን እንደ አምላካችሁ ቁጠሩኝ" ያለ የዲያብሎስን መንፈስ የሚወክል ነው። ዲያብሎስ በመላእክት መካከል ይኸንን ፈተና ሲፈጥር፣ ቅዱስ ገብርዔል "ንቁም በህላዌነ ነነአምር አምላክነ።" ብሎ መላእክት የተሰወራቸውን አምላክ እስኪያገኙ እንዲጸኑ ያደረገ መሆኑን መጻሕፍት ያስተምሩናል። ዛሬ በዲያብሎስ በሰማይ የተገለጠው የራስን አምላክ የማድረግ መንፈስ በካህናት መካከል እየታየ፣ የእግዚአብሔርን አምልኮ እየተፈታተነ ይገኛል። ካህናት የተሰጣቸውን አደራ ትተው ራሳቸውን አዋቂ አድርገው ሲቀርቡ፣ የሚጠብቁትን መንጋ ፈተና ሲሆኑትና በትዕቢት ሲገለጡ የአውሬው መጫወቻ እየሆኑ ነው። ይኸ የአውሬው መንፈስ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ተስለክልኮ ገብቶ ሲኖዶሱ ተከፍሎ መቀጠሉን ግድ የማይሰጣቸው፣ ሥልጣን ወዳድ ሰዎችን የገለጠ መንፈስ ነው።

በፈራጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የእግዚአብሔር ስም እየጠሩ በግለኝነትና በእኔነት መንፈስ የሚገለጡ አውደ ምሕረቱን በታላቁ አምላክ ስም ተቆጣጥረው በአውሬው የስድብ መንፈስ የሚገለጡ፣ የምሕረት አደባባይ፡የሚባለውን የቤተክርስቲያኗን የመስበኪያ መድረክ የምእመናንን ነፍስ በአውሬው የቃል ሰይፍ የሚወጉና የሚያሳድዱ ሰባኪዎች የተገለጡበት አውሬው በግልጽ ቤተ ክርስቲያኗን ያስጨነቀበት ዘመን ነው። በመሆኑም

የዘመኑ መጨረሻ የትንቢት መፈጸሚያ እየሆነ ነው። የ99ኙን ነገደ መላእክት በፈተነው እኔ ፈጠርኳችሁ ብሎ ከአምላክ ጋር እንደተገዳደረው መንፈስ “ስገዱልኝ” በሚል በ'ሰአለከ”(99) መንፈስ ራሳቸውን አምላክ ያደረጉ፣ “አንተ ነህ አዋቂ በሉኝ” እያሉ በትዕቢት የተወጠሩ የአውሬው መንፈስ ቤቱን የሰራባቸው ካህናት አለምን በኪሳቸው ይዘው በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ እንዲገለጡ ያደረገ መንፈስ ነው። በሥጋቸው የተገለጡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሰላሟን የምታገኝበትን መንገድ ለመሻት የመንፈስ ልብ ስለጎደላቸውና በእኔነነት መንፈስ ስለተገለጡ ቤተ ክርስቲያኗ ፈተና ላይ ትገኛለች። ሕግ ሰሪ ሕግ ለዋጭ፣ ምስጢር አባካኝ ሆነዋል። ቤተ ክርስቲያን የመጽናኛ፣ የደካሞች መሰብሰቢያ ሳለች፣ በስድብ አንደበታቸው፣ ምእመናን በመከፋፈል ስራቸው የተገለጡ የአውሬው ወኪሎች ሆነዋል። አለምን በጉያቸው ይዘዋት መንጋውን ከአውሬ ማዳን ሳይሆን ለአውሬው አሳልፎ መስጠትን ኩራት የሚያደርጉ አሉ፡ እግዚአብሔር ስለጾም የተናገረው ደወል ልብ ላለው ይደውላል፡፡-

> እነሆ፥ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ፤ ድምፃችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም። 5፤ እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን? ሰውስ ነፍሱን የሚያዋርደው እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? በውኑ ራሱን እንደ እንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን? በውኑ ይህን ጾም፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን? ኢሳ. (58፡4-6)

አለምን መጾም የካህንነት ወግ ነበር። በአለም የደለቡ፣ የሰለጠኑ ካህናት የምድር ግዛታቸውን እያሰፉ፣ በአውቃለሁ ትዕቢት እየደነፉ ነው። ይኽ ነውር የሆነ የእግዘአብሔርን ስም እየጠሩ ምዕመናንን የመበተን መንፈስ አክሊሉ የወደቀ የካህናት ባሕሪ መገለጫ ሲሆን ከመሠረቱ የምናገኘው ይኽንን የሚፈጽም በንግሥተ አዜብ የፍርድ ሚዛን ላይ እየተፈረደበት ያለ የአውሬው መንፈስ ነው።

ለ. በሥልጣን ሽሚያ የእግዚአብሔርን ሥልጣን የተቀናቀነ መንፈስ ነው። በኢትዮጵያ በሁለት መንገድ ተገልጧል። የመጀመሪያው አይነት የቤተ መንግሥቱን ሰማያዊ ቅባት ተጠቅሞ፣ በእግዚአብሔር ስም ከብሮ ግን ይኽንን በትረ ሥልጣን ወደ እኔነት ያወረደ ሥልጣን ነው። ይኽ የነጋሲነት መንፈስ “የይሁዳ አንበሳ” ተብሎ የጌታችን የአምላካችን

የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተላብሶ የቆየ ነው። የክርስቶስን ወንበር በእጁ ይዞም የኢትዮጵያን የክህነት ስጦታ በሰው ዘመን እንዲቆጠር ያደረገ ነው። የእግዚአብሔርን ስም ይዞ በመንገሱ የይሁዳ አንበሣ ከጥቅምት 23 ጀምሮ አስቆጥሮአል። ይኸ የሥልጣን ሁለት ዘመንን ይጠቀልላል። ስለቤተ መንግሥት አቆጣጠር በአዜብ መለኪያ በ42 ዲግሪ የተለካ መንፈስ ሲሆን (ጥቅምት 1924 እስከ ጥቅምት 1966) ያለው ነው። ስለመልከጸዴቅ የዘላለም ካህኔ የተባለ የተቆጠረው በሰው እጅ ያበቃው ክህነት ከሂኖክ ቀመር፣ በምድራቱ ዕጣ በ81 ዘንግ በ2004 ነው። (1923-2004)። የብጹዕ ፓትርያርክ ጳውሎስ በዕረፍት የተጠሩበት ቀመር የኢትዮጵያን ዘላለማዊ ክህነት በቀደመ ክብሩ የሚመልስ ነው። ይኸንን ምስጢር ያላስተዋለ የክህነት ሹመት፣ በተለይ አሁን በሲኖዶስ አካባቢ የሚስተዋለው የሹመት ሥርዓት፣ አለማዊና የኢትዮጵያን የክህነት ስጦታ ያላመሳከረ፣ ልብ ያላለ፣ ሐዋርያው “ትልቁ” ብሎ በዕብራውያን ላይ የገለጠውን የመልከጸዴቅን ክህነት ምስጢር ያላገነዘበ ነው። በእሳት መጫወት እንዳይሆን ተሳታፊዎች ጥበብን ሊያጠይቁ ያሻል። የኢትዮጵያ የክህነት ስጦታ ከሌዋውያን የክህነት ስጦታ ከፍ ያለ ነው።በርግጥ በመንግሥተ ሰማያት ሥርዓት ሊቀ ካህናቱ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ሳይል በክርስቶስ እጅ የተያዘ ነው።

> “አሥራትን የሚያስወጣ ሌዊ እንኳ በአብርሃም እጅ አሥራትን ሰጥቶአል፤ 10 መልከ ጼዴቅ በተገናኘው ጊዜ ገና በአባቱ ወገብ ነበረና። እንግዲህ ህዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን፥ እንደ አሮን ሹመት የማይቈጠር፥ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሳ ወደፊት ስለ ምን ያስፈልጋል? ክህነቱ ሲለወጥ፥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና።” (ዕብ. ፯፡፲-፲፪)

ይኸ የኢትዮጵያ የክህነት ስጦታ፣ ከሌዋዊ ክህነት የበለጠ በመሆኑ በቁጥር 81፡የሚለው የኢትዮጵያ መጽሐፍ “ሂኖክ” ከሚለው፣ “ካህን” ከሚለው ቃል ጋር ቀመሩ አንድ ነው። (ሀ=1፣ ነ=30፣ ከ=50 ድምር=81)። የኢትዮጵያን የክህነት ወንበር መልከጸዴቅ አብርሃምን የባረከበት ነው፤ በመንግሥተ ሰማያት የጌታን ቤተሰቦች የወከለ ዮሐንስ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያጠመቀበት ነው። የኢትዮጵያ የቤተ ክህነት ስጦታ የቃል ኪዳን ስጦታ ነው። በአዲስ ወንጌልም ይኸ የኢትዮጵያ የክህነት ስጦታ ከማርቆስ ወንበር ያይደለ በመንፈስ ቅዱስ አጥማቂነት፣ በፊልጶስ ተራዳኢነት፣ ለጃንደረባው የተሰጠ የክህነት ስጦታ ነው። የኢትዮጵያ ክህነት ከሌዋዊ ክህነት የላቀ ነው። ለኢትዮጵያ በክርስቶስ ማመን የተመሰከረ በ12ቱ ሐዋርያት ያይደለ በንግሥተ ሕንደኬ ጃንደረባ በኢትዮጵያዊው

ሰው በኩል መሆኑ ስለኢትዮጵያ የቤተ ክህነት ስጦታ የተለየ ምስጢር ነው። ዛሬም የኢትዮጵያ የክህነት ስጦታ ይኽንን የ”ዘላለም ካህኔ” የተባለ የመልከጸዴቅን ምስጢር መመርመር፣ ሄኖካዊ ብሂሉን ማወቅ፣ ብሎም የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ ማስተዋል ይኖርበታል።

ይኽንን የኢትዮጵያ መለኮታዊ ቃል ኪዳን ያልጠበቀ እስከሆነ ድረስ በሥልጣን ሽሚያ የሚገለጠው የ81 ዓመት ግርግር ዛሬም እልባት ሊያገኝ አይችልም። የኢትዮጵያ አባቶች በአለም መንፈስ በ”ሰአለከ” (99) የተገለጠውን የአውሬውን መንፈስ ከጉባኤያቸው አስወግደው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚተገብሩበት ሥርዓት መሻት፣ መፈለግና፣ የአለም ሥልጣንን (666) መንፈስ በእግዚአብሔር መንፈስ አስወግደው ሰዓቱ ጊዜው፣ የእግዚአብሔር ክብር መግለጫ ይሆን ዘንድ የመክሊታቸውን መስራት ይኖርባቸዋል። ይኽ ይሆን ዘንድ በማቴዎስ 12፡42 የተገለጠችው ንግሥተ አዜብ በፍርድ አደባባይ መገለጧን ልብ ሊሉ ይገባል። ይህ ይሆን ዘንድ እሳተ መለኮት የተላበሰውን የኢትዮጵያን ቃልኪዳን ያማከለውን የቤተ ክርስቲያንን ስምና ክብር በእጃቸው ለያዙ አባቶች ሁሉ ልቦና ይስጥልን። አክሊላቸውን ጠብቀው፣ እንዲመሩንና እግዚአብሔር ጥበቡንና ብርሃኑን ለግሶ አባቶቻችንን አሐቲ ቤተ ክርስቲያንን በፍጹም ትሕትናና በትጋት ያገለግሉልን ዘንድ ብርታቱን ይስጥልን ለክብሩም ያብቃልን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስተያንም በታቦተ ጽዮን ኃይል፣ በእስራኤል አምላክ በቀደመ ክብሯ ትቆማለች። ይኽ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚወናጨፈው የሚስለከለክ የአውሬው መንፈስም ይመታል።

### ለ. <u>በምድር በአዳም ነፍስ የሚስለከለከው ልቡሰ ሥጋዎችን ያፈራ መንፈስ፡</u>

በመንፈስ “ሰአለከ” (99) እንዳለ ግን በአካል ደግሞ በ “ስልክ” መንፈስ ወርዶ ይኽ ክፉ የዲያብሎስ መንፈስ አለምን እያወካት ይገኛል። በእያንዳንዱ ነፍስ ውስጥ መረቡን ዘርግቶ አለምን ተቆጣጥሮ የሚገኝ መንፈስ ነው። በስልኩ ውስጥ የሚሰራውን መንፈስ በእያንዳንዱ ነፍስ ውስጥ የሚሰራበት ኮድ ተክሏል። ካህናት ሳይቀሩ ተሸክመውት ቅዳሴ እንደሚገቡ ይታያል። ዛሬ በኢትዮጵያ ከገጠር እስከ ከተማ የገባው በስልክ ውስጥ የሚስለከለክ መንፈስ በጠቅላላው በአለም ላይ አውሬው አለምን የሚቆጣጠርበት መሳሪያ

ሆኗል። ባለሥልጣናትን፣ የተከበሩ ሰዎችን፣ ነገሥታትን ከሥልጣን ለማውረድ፣ ለማዋረድ፣ የሰውን ገመናና ክብር ለመግለጥና ለማራከስ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተውን የዘመኑን ቴክኖሎጂ የሚጠቀም ሲሆን፣ በተለይ ስልክ ግን በቀላሉ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ አለምን ለመቆጣጠር የሚያስችል አውሬው በኮድ የሚሰራበት ጥበብ ነው። ልብ አድርግ አውሬው በስልክ ይሰራል ስልህ ስልኩ በራሱ ችግር የለውም። ግን “ሰለከ” የሚለውን ቃል ወስህድ ቀምረው። “59” ነው። ይኸንን ኮድ ተጠቅሞ ለ42 ወር ግዛቱ መፈጸሚያ ያደረገበት መንፈሳዊ ክህሎቱ የረቀቀ ነው። በተለይ ይኽ የሚገለጠው የሕይወት መርበብ ወይም የአውሬው መርበብ ሊሆን በሚችል መንፈሳዊ ቀመር ውስጥ ያለው ቦታ ሲታወቅ ነው። ይኽ ቀመር እንዲህ ይጻፋል፦

[59 X 260 ] = [42 X 365 ¼ ]

ተመልከት። መንፈሱ ወደ ሰው ነፍስ የሚገባበት ኮድ “59፡ ነው። የሚገለጠው በዘመኑ፣ በሚቆጠር በ42 ዲግሪ ነው። ይኽ በጥበበኛው ሰሎሞን ዘመን አጋንንትን ለማጥመድ ይውል የነበረውን “መርበብተ ሰሎሞን” በግዕዝ ሰማያዊ ቀመር የሚያስቀምጥ ነው። አውሬው የሚጠቀመው ይኸንኑ መርበብት ነው። ክርስቶስ ከአብራም (59) ተወልዶ በዘር ሐረግ ቆጠራ 42ኛ ላይ ተገልጠ የድኅነትን ቀመር ሰራ። በዚህ ፍጥረትን ሁሉ ወደ ሕይወት ከፍ ከፍ ያደርጋል። በራዕይ 13 የተገለጠው የቀደመው እባብ የተባለው፣ በኃሳዊ መሢሕ መንፈስ የሚሰራውም መንፈስ ይኸንኑ መርበብት ይጠቀማል። ነፍስን ጥገኛ ለማድረግ (ሰ አለ የሚለው ለመነ ነው። ከዚህ የሚወጡ የግእዝ እርባታዎች ውስጥ “ሰአለከ” “ሰለከ” “ተሰለከለከ” ስልክልከ..ወዘተ) የሚል ነው። ከዚህ ውስጥ ገዝፎ በየሰዉ እጅ የገባ “ስልክ” የአውሬው መጠቀሚያ ሆኗል። በቀመር 59 ነው( ሰ=7፣ለ=2፣ከ50)። በስልኩ ፍቅር የሚገባው ፍቅር የአውሬው ዘመን መቁጠሪያ ሆኖ ሁሉንም የአውሬው ሰለባ እያደረገው ነው። እስኪ ከራስህ ጀምሮ አካባቢህን ተመልከት በስልክ ፍቅር ያልወደቀ ማን አለ። ሰው ለሰው በስልክ ነው። ሰው ለሰው መድኃኒት፣ ጓደኛው፣ ሕይወቱ ነበር። አሁን ለሰው ታማኝ ጓደኛው፣ ስልክ ነው። ስልክህን ለአንድ ቀን ተወው፣… የሞትክ ያህል ይጨንቅሃል… ታማኝህ እሱ ነው። ብትቸገር ፖሊስ፣ አንቡላንስ ትጠራበታለህ… ሰው ለሰው ጨክኗል… ኮምፒዩተር፣ ኢንተርኔት፣ ስልክ… በተለይ ስልክ… ማን “አይፎንን” ያክላል… አዎ

*መንፈሱ የስልክ ነው። የሰው ታማኝ ጓደኛው ስልክ ነው። አዎ የመጽሐፉ ሕግ ተቀይሯል። "ጎረቤትህን እንደራስህ ውደድ" የሚለው የክርስቶስ ሕግ :(ማቴ ፳፪፡፴፰-፴፩) የሚገዳደረው መንፈስ በአለም ላይ ሰፍኗል። "ስልክህን እንደ ነፍስህ ውደድ" ሆኗል። የክርስቶስ ሕግና :የአውሬው ህግ ተናንቀዋል። ግን ይኸም ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ነው፦*

> **አ**ውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። 16 ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥ 17 የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። 18 አእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፤ ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነውና፥ ቍጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው።

*አንባቢ ሆይ ልብ አድርግ! እሳት በጣም ለሕይወት አስፈላጊ ነው። ግን እሳት ምግብ ካበሰሉበት በኋላ ወይ ያዳፍኑታል፣ ወይ ያጠፉታል። ዛሬ በስልክ ተመስሎ አለምን የተቆጣጠረው መንፈስ ምግብ እያበሰሉበት ግን ሳያጠፉ የተዉት እሳት ማለት ነው።*

*የአዳም ልጅ ሆይ ጠይቅ! ነፍስህ ከማን ጋር ናት በስልኩ ውስጥ ያለው መንፈስ በቁጥጥር ውስጥ አውሎሃል? ወይስ ነፍስህ ከምታመልከው ከእግዚአብሔር ጋር ናት? በኢያሱ አድሮ የተናገረ እግዚአብሔር ለእስራኤል የነገረውን ማሰብ ጠቢብ መሆን ነው፦*

> "**አ**ሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ፥ በፍጹምም በእውነተኛም ልብ አምልኩት፤ አባቶቻችሁም በወንዝ ማዶ በግብፅም ውስጥ ያመለኩአቸውን አማልክት ከእናንተ አርቁ፥ እግዚአብሔርንም አምልኩ። እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን። ሕዝቡም መልሰው እንዲህ አሉ። እግዚአብሔርን ትተን ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከእኛ ይራቅ፤ እኛንና አባቶቻችንን ከባርነት ቤት ከግብፅ ምድር ያወጣን፥ በዓይናችንም ፊት እነዚያን ታላላቅ ተአምራት ያደረገ፥ በሄድንባትም መንገድ ሁሉ ባለፍንባቸውም አሕዛብ ሁሉ መካከል የጠበቀን፥ እርሱ አምላካችን እግዚአብሔር ነውና።

*አዎ ሰዓቱ እያንዳንዱ የራሱን ነፍስ የሚዋጅበት ሰዓት ነው። ማንን እያመለክን ነው? የኢያሱን ጥበብ የቀሰመ አውቆበታል፡*

> "የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።"

## ምዕራፍ ፺ :የመጨረሻው ዘመን ፍርድ ሰዓት አቆጣጠር።

ከላይ የዘረዘርናቸው የፍርድ ቀመር ምስጢራት በመንፈስ አይናችን መመልከተ እንድንችል የፍርድ ቀመር መለኪያ የሆኑ የጊዜ ቀመሮችን እንጥቀስ።

ይኸንን ጽሑፍ ለሚያነብ "እንዴ እንዲህ ነበር እንዴ ስለመጨረሻወ ዘመን አፈጻጸም ሰባኪያን ያስተማሩን? ብሎ የማይገረም አይኖርም፣ ይኸንን ጸሀፊ ጨምሮ። እውነት ነው ለዚህ ጸሀፊም የፍርድ ቀመር ጊዜና ክህሎቱ የሚያስገርም ነው። ግን ሰው ከሥጋዊ ሕይወቱ ከፍ ብሎ እግዚአብሔር ፍጥረትን የቀመረበትን መንፈሳዊ ሥርዓት ካላሰተዋለና በተለይ አዳምን ከመፍጠር እስከ ማዳን ድረስ ያደረገውን ድንቅ ተአምር የሚያይበት የጥበብ አይን ካልታደለ ይኸንን ምስጢር ማየት አይቻልም። አዎ የዘመኑ አፈጻጸም፣ የደብረ ሲና ፍርድ አሰጣጥና የደብረ ጽዮን የእግዚአብሔር መንግሥት አወቃቀርና በአዳም ሕይወት ውስጥ የመገለጡ ነገር በእግዚአብሔር እርዳታ በጥሞና በአዲስ መንገድ የሚመረምሩት ነው። ሰለዚህም ማንም ሰው ስለፍርድ ሰዓትና ቀመር አመለካከቱን ማስተካከል ተገቢ ነው። ይኸንን ምስጢር ለማየት ግን ከሁሉም በላይ አንድ ነገር ያስፈልጋል፣ ይኸውም የተሰበረ ልብ ብቻ ነው። የተሰበረ ልብ እግዚአብሔርን ያያልና።

> በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። 4 የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና። የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና። ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና። የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና። ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና። የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ (ማቴ. ፭፡፩-፲፩)

ንጹህ ልብ ደብረ ሲናንና ደብረ ጽዮንን ለማየት አይቸገርም።

ሀ. **- የፍርድ ሰዓት መለኪያ ቀመር (ጊዜ)**

በእግዚአብሔር ፊት አንድ ቀን አንድ ሺ አመት የሚሆንበትን ብሂል የመንፈስ ጥበብ ሥርዓት አለ፣ ከዚህም በመነጨ አንድ ቀን አንድ ወር፣ አንድ ቀን አንድ አመት የሚሆንበት ምስጢር ይታቀፋል። የእግዚአብሔር የጊዜ ቀመር፣ በመንፈስ፣ በ አእምሮ፣ በአካል ይገለጣል። በሰማያዊው ሥርዓት፣ የአብ ጊዜ፣ የወልድ ጊዜ፣ የመንፈስ ቅዱስ ጊዜ አለ። ሁሉም ጊዜ ግን ከአንድ የእግዚአብሔር የእረፍት ቀን የፈሰሰ ነው። በዚሁ የጊዜ ቀመር የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት የተነደፈበት እንደመሆኑ በተቃራኒው በንጽጽር እንዲሁ የዲያብሎስ፣ የኃሳዊ መሢህና ብሎም የሁለቱ ሕይወት የሆነ የውሸት መንፈስ የሚሰሩበት ቀመር ሆኖ ይገለጣል። ይኸ በአንድም በሶስትም መንፈስ የሚሰራ የአውሬው መንፈስ በመጨረሻው ዘመን በ42 ዘመን ግዛት የተወሰነ የመሆኑን ያህል በጠቅላላው የእግዚአብሔር የፍርድ መቃጥን አውሬውን ለማጥመድ የሚሰራበት ቀመር እንዲሁ በአካል፣ በአእምሮ፣ ብሎም በመንፈስ ልክ የተነደፈ የጊዜ ቀመር ነው።

ማለትም በዚህ ሥርዓት አለም ባለሶስት ጎን የጊዜ ፒራሚድ ውስጥ እየተፈረጀ፣ እየተፈረደበት ይገኛል። ይኸ ሶስት ገጽ የፍርድ ጊዜም የሚቀጥሉትን ይሸፍናል፦

ሀ. በእግዚአብሔር ፊት ሁለት የፍርድ ቀን አለፈ (2000 እንደ ሁለት ቀን)

ለ. በሰው ልጅ አቆጣጠር ሁለት ሺ ዘመን አለፈ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እስኪገለጥ ያለው ነው፤

ሐ. እያንዳንዱ ቀን የፍርድ ቀን ሆኖ እያንዳንዱ ነፍስ በመርበብተ ሞት ወይም በመርበብተ ሕይወት ውስጥ ተጠምዷል። የመርበብተ ሞት ግን ብዙ ነፍሳትን አጥምዷል።

ከላይ የጠቀስናቸው የቀመር ስሌቶች የዘመኑ መጨረሻ መቀመሪያ የጊዜ ሁነቶች ናቸው፡፡ በዚህ የጊዜ ቀመር ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት 1 ቀን 1000 ዓመት የሚለው ምስጢር

**የጊዜን ፈሻሽነት የሚያመለክት ፩ ቀን ፩ ወር፣፩ ቀን ፩ ዓመት፣ ፩ ቀን ፩ሺ ዓመት የሚሆንበትን ምሥጢር ያካተተ ነው። ይኽ የጊዜ ፈሳሽነት እንደሚከተለው ይቀመጣል። በመንፈሳዊ ቀመር ጊዜ ኃይል ሆኖ ፈሳሽ ሲሆን ዘላለማዊ የሆነ የማያልቅ የማይቃጠል ጊዜ ይሆናል፡፡ የዘላለማዊ ቀን ምስጢር ይኽ ነው። የቀደመው ቀን ሆኖ እግዚአብሔር በቅድምና የሚኖርበት፣ የማይፈጠር፣ ያልተፈጠረ፣ የማይቃጠል፣ የማያልፍ፣ የማያልቅ ጊዜ ይሆናል፤፡ በዚህ መንፈሳዊ እይታ፣ አንድ ደቂቅ፣ እንደ አንድ ሰዓት፣ አንድ ሰዓት እንደ አንድ ቀን፣ አንድ ቀን እንደ አንድ ወር፣ እንደ አንድ አመት፣ አንድ አመት እንደ እንድ ሺ አመት፣ ይሆናል።** "በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት ፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።"( 2 ጴጥ. 3፡8.)

**የማያልቅ ዘላለም ጊዜ ቀመር እንዲህ ይቀመራል።**

| |
|---|
| **አንድ ደቂቅ=አንድ ሰዓት= አንድ ቀን=አንድ ወር=አንድአመት= አንድ ሺ ዓመት = ዘላለማዊ ቀን** |

## ሐ. "እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤" (ራዕይ ፲፮፡፲፭)

**ከላይ የጠቀስነውን የጊዜ ቀመር ስንረዳ ክልብ የምናስብበት ጌታ የተናገረው ነገር አለ። ዘመን የሚጠቀለልበትን ምስጢር ለማወቅ ለሰው ልጅ እንደሚያስቸግረው በማሰብ እንዲህ ብሎ ነበር።** "እነሆ ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።" (ራዕይ ፲፮፡፲፭) ። ለማንኛውም ይኽንን የፍርድ ሰዓት ምስጢር ለመረዳት የሚሞክር የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ሊላቸው ይገባል፦

**ሀ.** ዲያብሎስ በመስቀል ከተሰቀለ፣ ክርስቶስ ሞትን በሞቱ ድል አድርጎ በትንሳኤ ሙታን ሥርዓት ለሰው ልጅ ሁሉ የድኅነትን ቀመር በደሙ ከሰራ

በኋላ መንፈስ ቅዱሰ ለፍርድ ተልኳል። በኢየሩሳሌም ሐዋርያትን ያጠመቀ መንፈስ ቅዱስ፣ ሕያው የሚያደርግ፣ ኃይል የሚሰጥ እንደመሆኑ በዲያብሎስ ላይ ፈራጅ ነው። ይኸ የፍርድ ዘመን ሲቆጠር በእግዚአብሔር ፊት ሁለት ቀን አለፈ (1000 ዓመት እንደ አንድ ቀን)፤ “እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ ስለ ኃጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው።” (ዮሐ. ፲፮፡፰-፲፩)። ዲያብሎስ ተፈርዶበት ዘመኑ የተቆጠረ ክርስቶስ በመስቀል ድኅነትን ከሰራ ጊዜ ጀምሮ መሆኑ ልብ ይሏል። ሐዋርያትን በኢየሩሳሌም የጎበኛቸው መንፈስ ቅዱስ አንዱ ሥራው የፍርድ ሥራ ነው። ስለዚህ በአውሬው ላይ ፍርድ የተጀመረው፣ በመስቀል ላይ ከተፈረደበት ሰዓት ጊዜ ጀምሮ ነው። ስለዚህ ያለፈው የ2000 ዓመት በእግዚአብሔር ፊት ያለፈ ሁለት ቀን ማለት ነው። ስለዚህ የቀረው የፍርድ ሰዓት የፍርድ ቀመር “የመጨረሻው ሰዓት’ ማለትም “ማጣሪያው” ማለት ነው።

ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ ጀምሮ በከዋክብት የጊዜ ቆጠራ 2000 ዓመት ዑደት ተለካ። የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር የተገለጠበትን ጊዜ ጀምሮ የሕይወት ዘር አብቅሎ፣ አፍርቶ፣መኸሩ ለመታጨድ እስኪደርስ ድረስ ያለውን ጊዜ ይጠቀልላል። ይኸ የ2000 የሰው ዘመን በማቴዎስ ወንጌል “መኸሩ እስኪደርስ” የተባለው ጊዜ ሲሆን በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ጠላት የተባለ ዲያብሎስ የዘራው ክፉ እንክርዳድ ዘር ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር እየተቀናቀነ ያደገበት የአለም ንጉሥ፣ ገዥ ሆኖ የተገለጠበት ዘመን ነው። “እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ” የተባለው ይፈጸም ዘንድ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ የክርስቶስን መንግሥትን የሚቀናቀን በ”አቡነ ዘበሰማያት” ምትክ

"የእኔነነት" የአምልኮ መንፈስን የዘራ ኃይል በፍጥረት ላይ ሰርቷል። የአዳም ዘርም የዚህ መንፈስ ሰለባ ሆኖ ቀጥሏል።ይኸ መንፈስ የገነነና ጊዜው የሰው ልጅ የተባለ የዚህ እንክርዳድ ስለሆነ፣ የጽድቅ ሕይወት አስቸጋሪ፣ ፈታኝና ከፍተኛ መስዋዕትን የሚጠይቅ ሆኖ ቆይቶአል። "በጠባቡ መንገድ ግቡ" የተባለም ስለዚህ የጽድቅ ጉዞ አስቸጋሪነት ነበር።

ሐ. **ለሰው ልጅ እያንዳንዱ ቀን ፡የፍርድ ሰዓት ነው።** "ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፥" (1 ቆሮ 15፡22) ክርስቶስ የተለካባት የትንሳኤ ሙታን ሥርዓት ለሁሉም በእግዚአብሔር መንግሥት ለሚገባ ሁሉ መለኪያ ናት። ይኸው ክርስቶስ ፡የተገለጠበት የመንፈስ ሕግ ሁሉም የሚገለጥበት የፍርድና የሕይወት ቀመር ነው። እያንዳንዱ ነፍስ በምድያም ሕግ (ማይ/ደም) በተቀመረ የመንፈስ ሕግ በመቃጥን የተያዘ ነው። ይኸውም በአፍአዊ የአስትሮኖሚ ቀመር ማወዳደሪያ ሲሆን በውስጠቱ ግን የመንፈስ ፡ሕግ ነው ይኸው ሕግ እንዲህ ይቀመራል።

[59 X 260] = [42 X 365 ¼]

ይኸ ሕግ እያንዳንዱን ነፍስ በሚተነፍሰው ነፋስና በደሙ ውስጥ በሚዘዋወረው ደም የሚይዝ ነው። ሕጉ ለአዳም ድኅነት በአብርሃም የቃል ኪዳን ሥርዓት የተሰራ ነው። በዚህ ሕግ መሠረት እግዚአብሐር በስሙ ለአብራም(59) (አ=40፣በ=9፣ ረ=6፣ መ=4፣ ድምር=59) የገባው ቃል ኪዳን ፀሐየ (365 ¼) ጽድቅ የተባለ ክርስቶስ ከ42ኛው የዘር ሐረግ ተወልዶ የሚያድንበት ምስጢር ነው። የቀመሩ ግራ ክፍል ለአብርሃም በስሙ የተገባውን ቃል የሚያመለክት ሲሆን፣ በግራ በኩል የተነደፈው ደግሞ በደሙ ይኸንን አለም የተቤዠውን ክርስቶስ የሚጠቅስ ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰራው ይኸ የድኅነት ቀመር በውሃ (ማይ) ስለሕጽበት (የማያ ካሌንደርን በግራ በኩል ልብ ይሏል)፣ በደም ስለድኅነት የተሰራውን (በቀኝ

በኩል ያለው ቀመር ሲሆን ይኸ በጋራ የተገለጠ እኩዮሽ ነው፤ ስለዚህም ቀመሩ የመንፈስ ቅዱስ ሥርዓት የሚያካትት፣ የሶስቱ ምስክርነት ነው። ውሃ፣ ደም፣ መንፈስ። (፩ ዮሐ. 5፡7) በዚህ ቀመር ውስጥ ይካተታሉ።

መ. ለመጨረሻው ፍርድ ሰዓት የደረሰበት፣ ብሎም ፈራጁ የሚገለጥበት ሰዓት ዘመኑ የተለካ ነው. ይኸውም አሁን ነው።" በመከር ጊዜም አጫጆችን። እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፥ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ።" ይኸ እየተከወነ ነው። ይኸ መሆኑን የሚያመለክቱን በቂ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል። በ42 ዲግሪ እየተለኩ የተፈጸሙ የፍርድ ቀመሮች በሠንጠረዥ ቀርቦ ተመልክተሃል። እነዚህ በግዮን ምስጢር በ59 (ከበ) ኮድ የተነደፉ ናቸው፡፡ በገነት ሄዋንን ያሳተው እባብ የተፈረደበትም በዚሁ መቃጥን እየተለካ ነው። በሁለት መንገድ ይኸ ተፈጽሟአል። በአለም አቆጣጠር (የግሪጎሪያን ካሌንደር) ዘመኑ በ2000 ተቆጥሮ ሲገባደድ የዚህ የፍርድ ቀመር ሳያዛንፍ ለአለም መንግሥት መጠናቀቅ ምልክት አድርጎ ያቀረባቸውና በመቃጥኑ የተሰፈሩ የአሜሪካ መንግሥት 42ኛ ፕሬዚዳንት ፡የነበሩት ቢል ክሊንተን በአለም የፍርድ ሚዛን (impeachment trial due to the Monica Lewnisky Scandal) በፍርድ መቃጥን የተያዙበት ምስጢር ነው። ይኸው በአፍአዊ የአንድ ግለሰብ ፍርድ ይመስላል እንጂ ፍርዱ በመንፈስ ሥርዓት የሰው "የግል ፍላጎት" (self will) ሄዋንን በገነት ያሳተ መንፈስ በጠቅላላው በጅምላ የተፈረደበት ቀመር ነበር። ከላይ በጠቀስነው መቃጥን የተቀመረው የኒህ ፕሬዚዳንት የፍርድ ሕይወት በስልክ በተቀዳ መረጃ የተመሰረተ ነበር። በቀመሩ ላይ (59 በ 260) የሚታየው በ"59" ኮድ የአለም መንፈስ የገባበት ረቂቅ ምስጢር ነው። በቀመር ሲለካ "ስልክ" (59) ቀመር ነው። "260" የሚለው በእግዚአብሔር ስም (ሀሎ ዘይሄሎ=YHVH=26) የተሰጡ አስርቱ ትዕዛዛትን የመፈጸምን ብሂል የሚያመለክት ነው። ፕሬዚዳንቱ 42ኛው መሪ መሆናቸው መንፈሱ ስራውን የገለጠበት ሰው መሆኑ ነው። (42 በ 365 ¼)

የሚለውን ያመለክተናል። ልክ በአለም አቆጣጠር 2000፣ 42ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በ59 ኮድ በተስለከለከ መንፈስ ምክንያት የአለም ንጉሥ የሆነ ሰውን የሚያስት መንፈስ የተፈረደበት ክንውን መገለጫ ነበሩ። በዚህ ዓይነት ከላይ በጠቀስነው ቀመር እያንዳንዱ ነፍስ ይመዘናል። ዛሬ የስልክልኩ እባብ መንፈስ በስልክ ውስጥ ሆኖ አለምን በተቆጣጠረበት ዘመን የዚህን ቀመር አሰራር ሁሉን ነፍስ ቀስፎ የያዘ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም። (የጄኔራል ፔትረየስ (General Patreaus) ና በጎልፍ ጨዋታ የአለምን ዝና ያተረፉት ታይገር ውድ (Tiger Wood) በአለም የፍርድ ሚዛን መገለጥ እንዲሁ ከስልክ (59) ጋር የተያያዘ ሲሆን ለ42 ዘመን ግዛት የተሰጠው የአውሬው መንፈስ በሕይወታቸው ውስጥ ተስለክልኮ የሥራው መገለጫ እንዳደረጋቸው የተገለጠበት ምስጢር ነው።)

ሠ. ይኸንን ጽሁፍ የጻፈው ሰው በሰለሞን መርበብት በ "59" ዲግሪ የአውሬው መርበብት ወይም መቃጥኑ ይዞት ለሰባት ቀን በ"ሲኦል" ቆይቷል። የአውሬው የ42 ዘመን ግዛት በጸሐፊው ነፍስ ውስጥ ይሰራ ዘንድ በሰው ቁጥር በ"6' ቁጥር መንፈስ፣ በ7 ቀን ሕግ በ42 ዲግሪ (7 በ 6) ተመዝኖ፣ ተፈርዷል።

## ምዕራፍ ፰ - የፍርድ ቀን መስፈሪያ የመቃጥን ቀመር።

### (መርበብተ ሕይወት/ሞት - የምድያም ሕግ)

(59 X 260) = (42 X 365 ¼)

በቁሙ ሲታይ ይህ ቀመር የሚያመለክተው የሁለት ካሌንደሮችን ንጽጽር ነው። ማለትም በግራ በኩል የተገለጠው የቀመሩ ይዘት፣ (59 X 260 ) የሚያመለክተው ለ59 አመት የተቆጠረን በ”13” ቁጥርና በ “20” ቁጥር ላይ የተንተራሰ የማያ ካሌንደር ሲሆን በቀኝ በኩል የተገለጠው ቀመር፣ (42 X 360 )፣ የሚያመለክተው ደግሞ የፀሐይንና የጨረቃን ሥርአት ያገናዘበ በትሮፒካል አቆጣጠር የተለካ የ42 ዓመት ካሌንደር ነው። እነዚህን ሁለት ካሌንደሮች በማወዳደር በ59 ዓመት የሚቆጠር የማያ ካሌንደር በ42 ዓመት ከተቆጠረ ካሌንደር ጋር ተመጣጣኝ ጊዜን እንደሚወክሉና እኩል እንደሚሆኑ የሚያመለክት ቀመር ነው።

ከዚህ ቀመር ባሻገር ግን መለኮታዊ ምስጢር ተደብቋል። ይኸውም ይህ ቀመር የሚያሳየው እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠውን የድኅነት ቀመር ነው። ማለትም አዳም ከኃጢአት ጎዳና ይወጣ ዘንድ በአብርሃም ጀምሮ የሰራው የዘር ሐረግ በአርባ ሁለተኛው ትውልድ ላይ በሚወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ይጠነቀቃል። አብራም በግዕዝ ቀመር 59 ይሆናል፤ ስለዚህ በእግዚብሔር ስም የከበረ አብርሃም የተቀበለው ቃል ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶሰ በኩል የተሟላ መሆኑን የምንገነዘብበት ቀመር ሆኖ እናገኘዋለን። “260” ትዕዛዛትን ስለመፈጸም (የእግዚአብሔር ስም (26=YHVH) በቃሉ ምስጢር (10=ተ) ተባዝቶ የምናገኘው ነው።በሌላ አነጋገር “260’ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የመፈጸም ምልክትም

ይሆናል። የእግዚአብሔር ስሙ በ26 ቀመር እንደሚለካ በአሥርቱ ቃላት (10) ሲለካ 260 የሚሆን መሆኑን እናስተውላለን።

ስለዚህ የአዳም ልጅ ሁሉ ሕግጋትን በመፈጸም በክርስቶስ በማመን የድኅነቱ ሥርዓት ተካፋይ ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ቀመር ሁሉም ፍጡር ይከወናል። ይኽ ሰውን ሁሉ መቆጣጠር የሚችል ቀመር የፍርድ ባለቤት የሆን የእግዚአብሔር ፍጥረትን በሕይወት፣ በመለወጥና በመታደስ ሥርዓት የሚከውንበትን ምሥጢር የያዘ ነው። እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል የሰራውን ቃል ኪዳን ነው። አብራም የሚለው ቃል በግዕዝ 59 ይመጣል (አ=40፣ በ=9፣ ረ=6፣ መ=4 በድምር = 59). 260 የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ቃሉን የማክበር ምስጢር የታቀፈበት ነው። ይኸውም በ”13” ቁጥር የሚወከል ሰላም በእግዚአብሔር ስም ሲከብር የሚሰጠን ቁጥር ነው። ማለትም 260 (13 ሲባዛ 20) ማለት ነው።

ከላይ እንደጠቀስነው የቀመሩ የግራ ክፍል የሚያመለክተው ውኃን ነው። የማያ ሥልጣኔ የሚጠቀምበትን ካሌንደር ይወክላል፤ ግን ማየ ማለት በግዕዝ ወኃ መሆኑን እናውቃለን። ስለዚህ በግራ የተጠቀሰው የሚወክለው በውኃ በመንፈስ መጠመቅን ሲሆን በቀኝ በኩል ደግሞ የተጠቀሰው የሚያመለክተው ደግሞ ደሙን በመስቀል ላይ ያፈሰሰ ኢየሱስ ክርስቶስን ይሆናል። ስለዚህ ለአብርሃም የተሰጠ ቃል ኪዳን ከወገቡ ፍሬ በወጣ በ42ኛው የዘር ሐረግ ላይ በተቆጠረ በኢየሱስ ክርስቶስ ተሟልቷል ማለት ነው። (ማቴዎስ ፩ ላይ የተዘረዘረውን ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ የተጠቀሰ ቃል ያንብቡ።) ስለዚህ በግራ በኩል የውኃ የመንፈስን ጥምቀት፣ በዮሐንስ 3 ላይ ክርስቶስ የጠቀሰውን እንደገና የመወለድ ቃል ኪዳን ስናስብ፣ ይኸንን ቃል ኪዳን የሚያሟላውን “ሥጋዬን ብሉ፣ ደሜንም ጠጡ” ያለ ክርስቶስ በሰማያዊ ሥርዓት በመንግሥቱ አክብረነው የምንኖርበት ሥርዓት በቀኝ በኩል ባለው ቀመር ይወከላል። ስለዚህ ይህ ቀመር በደም፣ በውሃ በመንፈስ የሚገለጥን ምስክርነት ይይዛል። ስለዚህም የአዳም ልጅ ሁሉ በሰዓቱ በሁሉ ጊዜ ለመጠየቅ የተቀመረ ነው። የአዳም ልጅ ሁሉ ይተነፍሳል፣ ውሃ ይጠጣል፤ በሰውነቱ ውስጥ ደም ይፈሳል። የፍርድ ቀን ሥርዓት በተግባር የሚገለጠው በነዚህ በሶስቱ በሚገለጥ

ሥርዓት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ነፍስ ላይ፡ያለውን ገዥነት የሚገልጥበት የሕይወትና የፍርድ ሚዛን ነው።

ይኸ ቀመር እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን [59 X 260 ] በ42ኛ የትውልድ ሐረግ ላይ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸመው መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን፣ በመጨረሻው ዘመንም አውሬው የ42 ዘመን አገዛዙን ሲፈጽም ስለሚጠቀምበት "59" ቁጥር የሚለው የአምልኮ ቁጥርን ይወክላል። ይህን ቁጥር የአውሬው መንፈስ የተጠቀመበት በስልክ ውስጥ በሚሰራ መንፈስ ነው። በግዕዝ ቀመር ስልክ 59 ቁጥርን ይወክላል። ማለትም ሰ=7፣ ለ=2፣ ከ=50 ድምር =59. ስለዚህ በስልክ (59) ውስጥ በሚሰራ መንፈስ የሚገለጥ የ666 መንፈስ አለምን ተቆጣጥሮ ለ42 ዘመን ይገዛል ማለት ነው።ይኸንን ቀመር አውሬው እየተጠቀመበት ሲሆን የሰውን ልጅ በገነት ያሳተውን መንፈስ ዛሬም በመጨረሻው ዘመን ተነስቶ በፍርድ ስርዓት ተገልጧል። ይኸ መንፈስ የተፈረደበት የአለም ሕዝብ በገሀድ በተመለከተውና የመጨረሻ ዘመን ፍርዱን የተቀበለው በአሜሪካን ሀገር የ42ኛው ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ከሥልጣናቸው እንዲወገዱ በኮንግሬስ የአሰራር ሥርዓት ለፍርድ (impeachment) በቀረቡበት ምሥጢር ነው። ፕሬዚዳንት ክሊንተን በአሜሪካ የሹም ሽር ሥርዓት የሚሊኒየሙ የመጨረሻ ፕሬዚዳንት ነበሩ። እኚህ ፕሬዚዳንት በ42ኛ ቁጥር ሲለዩ፣ በኮንግሬስ ለፍርድ የቀረቡበት ዋነኛው ምክንያት ከሳቸው ጋር ግንኙነት የነበራት ሴት (ሞኒካ ሊውኒስኪ) በስልክ ውስጥ ለወ/ሮ ሊንዳ ትሪፕ ያወራቻት ምሥጢር በቴፕ ተቀድቶ ለአባሪነት ስለቀረበ ነው። ስለዚህ አውሬው በ59 ዲግሪ መንፈስ ውስጥ ሰርቶ የ42ኛውን ፕሬዚዳንት ውስጥ የሰራ የሰው ፈቃድ (self-will) አምሳል የተፈረደበት የሰው ፈቃድ መንፈስ ነው። አንባቢ ሆይ አስተውል። የተፈረደበት መንፈስ ነው። በሰዎች ውስጥ እያደረ አዳምን ለውድቀት ያበቃ እሱ ነው። የዚህ ምስጢር ግን ለሁሉም የአዳም ልጅ ነው። በገነት ሄዋንን ያሳተ እባብ የተጠቀመበት የሰው ፈቃድ(self-will) ሲሆን ይኸ መንፈስ መንፈስ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ አረም ሊቆጣጠር የተነሳ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት እርሻ ነው። በሰው ልጅ የቀን አቆጣጠር 2000 ዘመን የወሰደው ይኸ ሰማያዊ እርሻ ዘሩን አብቅሎ፣ አድጎ፣ አጎምርቶ፣ አፍርቶ አሁን እየታጨደ

ነው።በውስጡ ግን ይኸ የአለም መንፈስ የዘራው አረም አለ። መኸሩ ደርሶአል ፣ አጫሾች ተልከዋል። ንግሥተ አዜብ የእግዚአብሔርን ቤተሰቦች ወክላ የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ማደሪያ የሆኑ የነነዌን ሰዎች ይዛ እየፈረደች ነው። ፈራጁ ፍሬውን ለመሰብሰብ፣ ሁሉንም እንደ መክሊቱ ለመጠየቅ የሚጠቀምበት መቃጥን ሁሉንም ይይዛል፣ ሁሉንም ይሰበስባል፣ በዚህ መቃጥን ግን አውሬውም አስመስሎ ተጠቅሞበት ነፍሳትን አሳድዶአል። ጥያቄው ለእያንዳንዱ ነፍስ ነው።

የትኛው መቃጥን አጥምዶሃል? የእግዚአብሔር መርበብት ወይስ የአውሬው መርበብት? ለእግዚአብሔር የጥበብ መስዋዕትን እያቀረብህ ነው ? ወይስ ፡የገንዘብን አምልኮ ለአውሬው እያቀረብክ እየሰገድህ ነው? ማንን ታመልካለህ? እግዚአብሔርን ወይስ ገንዘብ? እግዚአብሔርን ወይስ የአለምን ጣኦት? ይኸ መንፈሳዊ የሆነ ህምሌታዊ ጥያቄ ነው? መሆን ወይስ አለመሆን?

## ምዕራፍ ፱፡ የ42 ዲግሪ የፍርድ ቀመር።

### ሀ. የ42 ዲግሪ ሰማያዊ መሠረት።

እነዚህ አራቱ የፍርድ ምስጢራት በ42 ቀመር የተነደፉ ናቸው። 42 ቁጥር የምንለው እግዚአብሔር “ሁሉን የፈጠረ” በሚባልበት፣ ኃይሉን የገለጸበት፣ ብሎም ለእስራኤል ባወረሰው ስም “ኤል” በሚለው የምናውቀው ነው። ይኽ ስም በግዕዝ ቀመር 42 ይሆናል። (አ=40 ፣ ለ=2 ድምር=42). እግዚአብሔር ስሙን ለእስራኤል እንዳወረሰው እንዲሁ አዳኝ ሆኖ ከሰማይ የወረደው እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም የተወለደው በ42 የዘር ሐረግ በተቆጠረ (ማቴ. 1፡1-18)በአብርሃም ቤት፣ በዳዊት ቤት ነው። የዚህን ምስጢር ለማመስጠር፣ ያዕቆብ 14 ዓመት በላባ ቤት ማገልገሉን እናውቃለን። በአንድም በሶስትም የስላሴዎች ምስጢር 42 መሆኑ ነው። እንዲሁም ሰው፣ በእግዚአብሔር ዕረፍት ሲሆን በ42 ቁጥር ይወከላል። ይኸውም “6”ኛው ቀን የተፈጠረ ሰው፣ በሰባተኛው የእግዚአብሔር ዕረፍት ውስጥ መሆኑ 42 ነው (6 ሲባዛ 7). አንድም ሶስትም የምንላቸው ስላሴዎች በሰባት ቤት ዕረፍት “21” እንደሚሆን፣ በሰማይም ያለ፣ በምድርም ያለ ብለን በሁለቱ ስናሰላው (2 ሲባዛ 21) እንዲሁ 42 ይመጣል። እነዚህ ቀመሮች የፍርድን ቀን ለማጥናት ብሎም የክርስቶስ ሙሽራ ጽዮንን ለማወቅ የሚረዱን ቀመሮች ናቸው።

በዘመናችን እንግሊዘኛ ቋንቋ የአለም መንፈስ መገለጫ የሆነበትም ምስጢር ከዚሁ ከ42 ቁጥር ቀመር ጋር በተያያዘ ነው። እንግሊዝ ከላቲን የወጣ ነው። ላቲን ግን በግዕዝ ሲገለበጥ 42 ነው፡(ለ=2፣ ተ=10፣ ን=30)።

## ለ. የ42 ዲግሪ ያማከለ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል

1. “እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። 3፤ እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና። 4፤ እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን ባደረገ አምላክ ሰማይንና ምድርን ቀን፥ በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው። (ዘፍ. ፪፡፫)

2. እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። (ዘፍ. 2፡7)

3. በአገራችን ታላቂቱ ሳለች፥ ታናሺቱን እንሰጥ ዘንድ ወግ አይደለም፤ 27፤ ይህችንም ሳምንት ፈጽም፤ ሌላ ሰባት ዓመት ደግሞ እኔን ስለምታገለግለኝ አገልግሎት እርስዋን ደግሞ እሰጥሃለሁ። 28፤ ያዕቆብም እንዲህ አደረገ፥ ይህችንም ሳምንት ፈጸመ፤ ልጁን ራሔልንም ለእርሱ ሚስት ትሆን ዘንድ ሰጠው።

4. እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አሥራ አራት ትውልድ፥ ከዳዊትም እስከ ባቢሎን ምርኮ አሥራ አራት ትውልድ፥ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶስ አሥራ አራት ትውልድ ነው። (ማቴ. ፩፡፩-፲፰)

5. “ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።” (ራእይ 11፡3)።

6. “ለዘንዶውም ሰገዱለት፥ ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና፤ ለአውሬውም። አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል? እያሉ ሰገዱለት። 5 ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፥ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው።” (ራእይ 13፡4-5)

7. "ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።" (ራዕይ ፲፪፡፩-፯)

የአውሬው መንፈስ ለ42 ዘመን የተከሰተባቸውን ሁኔታዎች ባለብዙ ዘርፎች ናቸው። ይኸንን ሰማያዊ የጊዜ ቀመር ለመረዳት፣ አንድ መሠረታዊ ምስጢር መረዳት ያስፈልጋል፤ ይኸውም መንፈሳዊ የጊዜ ቀመር በንጹሕ ልሳን በግዕዝ የሚታሰብበትን ሥርዓት ነው፦

ለነገሩ ቀመሩንም ምስጢሩንም ሁሉንም የዘመኑን መጨረሻ ዕንቆቅልሽ መፍታት በግዮን ውኃ የተከበበች የተባለች የመንፈሳዊ ኢትዮጵያ ስጦታ ነው። ይኸንን ምሥጢር ፈትታ ለአለም ሕዝብ ሁሉ የብርሃኑን መንገድ የምታሳይ የሰማያዊ ግዕዝ ባለቤት ኢትዮጵያ ናት። አዎን ዛሬ አለምን ጉርንቦውን አንቆ ከያዘው የጨለማ መንፈስ ወጥቶ ወደ ብርሃኑ ይጓዝ ዘንድ ኢትዮጵያን ከነሰማያዊ የግዕዝ ሐብቷ የምትጫወተው አይነተኛ ሚና አለ። ስለዚህም የሰው ልጅ ሁሉ፣ የአዳም ዘር የተባለ ሁሉ አይኑን ከፍቶ ኢትዮጵያን ሊያዳምጥ ያሻል፣ የግድም ይላል። ከላይ በተጠቀሱት ሰማያዊ ምሥጢራት እየተፈረደበትና አዲስ አለምን እንዲያዋልድ የሚያቃትተው ምልክት ፈላጊ ትውልድ ንግሥተ አዜብ እያንኳኳች ነውና ሊቀበላት፣ ተጠርቷል። ይኸ የሚቀጥለው የኢትዮጵያ ሥልጣኔ የሚገለጥበት፣ ዘመኑ የሚዋጅበትን ምሥጢር ለመግለጥ… መጀመሪያ የቆምንበትን ጊዜ ማስተዋል ያስፈልጋል።

አዎን የኢትዮጵያን የኢካቦድ ዘመን ምን እንደሆነ ይህ ትውልድ ማስተዋል አለበት። የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ምንድን ነው? በዚህ ጥበብ አለ፡ ጆሮ ያለው ይስማ!

## ሐ. የመጨረሻው ዘመን የ42 ዲግሪ ትንቢቶች

ከዚህ ከአዳም መንፈሳዊ የድኅነት ታሪክ ጋር የተያያዘ ይኸው ቀመር የመጨረሻው ዘመን የተመሰጠረበት ምስጢር ስለሆነ በራዕይ ዮሐንስም እንዲሁ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። እነሆም፦

፩. <u>ስለሰማያዊና ምድራዊ ጽዮን ወኪሎች፤-</u> "ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።" (ራዕይ ፲፩፡፫) ይህ በጽድቅ መንገድ የሚጓዙ አሐቲ ቤተ ክርስቲያንን ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ አጽድቶ ለጽዮን ትዕይንት መገለጫ ለማድረግ የተሰጠ መገለጫ ነው። ይህ በክርስቶስ ስም ለመሰከሩ፣ ኢትዮጵያና የሮም ቤተ ክርስቲያን መመዘኛ ነው። በሰባተኛው ቀን የእግዚአብሔር ዕረፍት የተለካ የሰውን አካሄድ የሚለካ ነው። ትዕዛዛትን ፈጽሙ ለተባሉ ሐዋርያት መለኪያ ነው። የጳውሎስና የጴጥሮስን ወንበር ለያዙ መለኪያ የተሰጠ ነው። የሮምና የኢትዮጵያ ክህነት በዚህ ይለካል። የሮም ክህነት የሌዋዊ ክህነት ነው። የኢትዮጵያ ክህነት የመልከጸዴቅ ክህነት ነው። ሮም ጴጥሮሳዊ ነው፣ አለትነትን የሚያጠይቅ ነው፣ ኢትዮጵያ ጳውሎሳዊ ነው፣ በጃንደረባው የተላከ መልዕክት ነው። ሁለቱ ምስክሮች በግራና በቀኝ ስለሚቆሙት ነው። ጴጥሮስ ስለእምነት ነው፣ ኢትዮጵያ ስለጸድቅ መንገድ ነው። ሁለቱም በ "1-2-2-1" መለኪያ የተፈረጁ የ "26000" ምስጢርን የተላበሱ ናቸው። አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ምን ትመስላለች? አለት ማነው? መጋቤ ጳውሎስ ሕግን መሻር ይችል ነበር? በአለትነትና በመጋቤነት በቤተ ክርስቲያን ላይ የሰራው፣ አሐቲ ቤተ ክርስቲያንን የሚበትን መንፈስ የሚፈረጅበት ነው።

ራዕይ 11፡3 ሮምና ኢትዮጵያ የእግዚአብሔርን ምስክሮች ስለሆኑ የሚገለጥ ነው። ይኸ በ "አልፋ-ቤታ" ምስጢር ወይም "12" የሚከወን ነው። ይኸ ቅዱስ ሚካኤል የወረደበትና ሙሽራውና ሙሽራዋ የሚገለጡበት ክንዋኔ ነው። ኢትዮጵያ በቃና ዘገሊላ ምስጢር፣ ሮም በ"ሰለከ" ምስጢር ይገለጣሉ። ሁለቱም በ"1221" ምስጢር በፍርድ ሚዛን

ላይ ይቀመጣሉ። የተፈጸመ ነው። የኢትዮጵያን መንፈሳዊ ቃል ኪዳን የምታውቅ ሮም ሁለት ጊዜ የኤርትራን ባሕር የተሻገረችበት ምክንያት ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ ወይስ አንድ ባሕሪ? አሐቲ ቤተ ክርስቲያንን ማን ይወክላል? ሕጉ ቅዱስ መሆኑ የሚታወቀው ስለሚከበር አይደለምን? ከቃና ዘገሊላ ሠርግ በኋላ ዮርዳኖስ መጠመቅ ይገባልን?

የሮምና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የሚሰጠውን የፍርድ ክንውን በሚካኤል (12) ምስጢር ስለጳውሎስና ስለጴጥሮስ ሥርዓት ነው። (ይኸ የምህረትን ቃል በአራት ማዕዘናት፣ በሶስቱ ስላሴዎች ስም የሚገልጥ የሚካኤል ፍርድ ነው። 12 ነው፡፡ ይኸ ለሮም በአየሰሰ ምስጢር በ144 (12/12) ለኢትዮጵያ በ”5/12/5 ምስጢር በ60 (5 በ12) ብሎም በ360 ምስጢር የተጠነቀቀ ነው። ሮም በ”አብራም” ፈርጅ፣ ኢትዮጵያ በ”አብርሃም” ፈርጅ በ ’59/60” ምስጢር ይፈረጃሉ። ሙሽሮች የተገለጡበት ነው። በሁለቱም ምስጢራት ቤተ ክርስቲያን ለአለም መንፈስ የተሸነፈችበት ምስጢር ይገለጣል። ዋናው አላማ ግን ክርስቶስ አንድ ባሕሪ ወይስ ሁለት ባሕሪ የሚለውን ለመግለጥ ነው። ተዋህዶ ወይስ ኬልቄዶን? የኢትዮጵያና የሮም ሊቃውንት ጥበባቸውን ይገልጡልናል። እነ ሉተርም (18) በዚህ ምስጢር ይረዱናል።

ለ. <u>ሴቲቱን ስለሚየሳድደው አውሬ፡</u> አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ። 6 ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች። (ራዕይ ፲፪፡ ፭፡፮)። ይኸ የድንግል ማርያምንና የደናግልትን ሁሉ ፈተና የሚከታተል የአውሬው መንፈስ ነው። በድንግል ማርያም “ሰማያዊ ሐብት” ማለትም በጽዮን ታቦትና በመቀመጫዋ ማለትም በቃል ኪዳን ምድር ላይ ለተገዳደሩ መለኪያ ሥርዓት ነው።

በራዕይ 12 የተጠቀሰው የኢትዮጵያን የቃል ኪዳን ምስጢር ማለትም በመዝ. ፷፯፡፴፩ የተገለጠውንና በዘፍ. ፪፡፫ የተጻፈውን በፍርድ ሚዛን የሚያስቀምጥ ነው፡፡ ይኸም የጌታን ቤተሰቦች ንግሥተ ሳባ ባቀረበችው በ120 ምስጢር የሚገልጥ ቀመር ነው። የአሐቲ

ቤተ ክርስቲያን አካላት በ 72 ሊቃውንት፣ በ12 ሐዋርያት፣ በ36ቱ አርድዕት የሚገለጥበት ምስጢር ነው። ሴቲቱንና ቅዱሳንን የሚያሳድደው፣ መንፈስ የሚገለጥበት የጊዜ ቀመር ነው።

የቅድስት ማርያም ሀገር የኢካቦድ ዘመንን የምታልፍበት ወደ ቀደመ ክብሯ የምትመለስበት ቀመር ነው። ይኸውም ክብር ከኢትዮጵያ ምድር በ42 ዲግሪ የተነጠቀበት ተዋህዶና፣ ጥበብ (አእመረ) የተሳደዱበት ምስጢር ነው። ይኸ በእግዚአብሔር ስም የተሰራ ሂኖካዊ ሥርዓት በ"9/11 ምስጢር የምናይበት ነው። እግዘአብሔር ክብሩን ገልጧል። አስኳሉ የእግዚአብሔር መሐላ ነው። "መሀላ (፩"፣ "መሐላ"፣ ወይም መኃላ"። ይኸ የ "ሀሎ ዘይሄሉ" የተባለ ያለና የነበረ እግዚአብሔር፣ የንጉሡ ፈራጅ የ"ይሁዳ አንበሳ" ምስጢር፣ ብሎም የሰማያዊው የእግዚአብሔር ምስጢር በኢየሩሳሌም "ኃ" የሚገለጥበት (1-3-20//7፡9፡26) ግዕዝን፣ ታቦተ ጽዮንን፣ የመልከጸዴቅንና፣ የዮቶር ወንበር ብሎም የሂኖክን ምስጢር ያዘለ ቀመር ነው። ቄሱ ዮሐንስ (Prester John) ይገለጣል። የቅዱስ ዮሐንስ ሀገር፡ የመናፍስት ሀገር አይደለችም፤ የሙሽራዋ የድንግሏ ኢትዮጵያ ጠባቂ አንድ እግዚአብሔር ነው። የተበተነው መንፈስ ጸዋ ይላል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ይከብራል።

ሐ. <u>**ስለአውሬው የሥልጣን ዘመን፡**</u> ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፥ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው። (ራዕይ ፲፫፡፭)፡ይኸ ዘመን በመጨረሻው ዘመን የሚገነው መንፈስ ሊነግሥበት ለተሰጠው ዘመን መለኪያ ነው። በራዕይ ፲፫፡፭ ላይ የተጠቀሰው የአውሬው መንፈስ በጠቅላላው በአዳም የድኅነት ቃል ኪዳን ላይ በዘፍጥረት ፫ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ካለመፈጸም የሚመጣን ሞት በተመለከተ ለስህተት ምክንያት የሆነውን የእባቡን፣ ማለትም የቀደመውን ዲያብሎስ መንግሥት፣ ሥልጣን፣ ኃይልና ግዛት ፡የሚገልዋ ነው። ይኸ መንፈስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚቀናቀን በማቴዎስ 13፡28 "የሰው ልጅ ጠላት" የተባለ ዲያብሎስን ሲያመለክት በመጨረሻው ዘመን ለ42 ወር ለመንገሥ የተፈቀደለት ነው። የድኅነት ምስጢር የተከወነበት የአብርሃም የዘር ሐረግ ለዚህ ቀመር አይነተኛ ስለሆነ

በአብርሃም ቤት የተገለጠ ቅራኔ የትዕይንቱ መገለጫ ሆኖ ከአብርሃም ምድር የተነሳ መንፈስ ለ126 ወራት ነግሶ ዘመኑን ጠንቅቋል።

ይኽ ግን አዳም የተፈተነበት ትልቁ የአምልኮ ምስጢር ነው። የሰው ልጅ መንፈስ እንዲገዛ ፈቃድ ይሰጠዋል። በአብርሃም ማዕድ ዙሪያ ፊታቸውን የተዟዟሩ እስማኤልና ይስሐቅ የሚፈረጁበት የፍርድ ምስጢር ነው። በ42 ምስጢር የተጠነቀቀ ነው። ከ9/11/2001 እስከ 5/2/2011 ያለውን የሚቆጥር ነው። በመሰረቱ ግን የአዳምን የገነት ፈተና ያማከለ ነው። ይኽ በኢትዮጵያ የጥበብ ሐብታት ቁልፍነት የሚፈታ ነው። ኢትዮጵያ ይኽንን ምስጢር ለአለም የምትገልጥበት ስጦታዋ ሶስቱንም አብርሃማዊ ሃይማኖቶች በሰላም ፡ያስተናገደች የእግዚአብሔር የጸሎት ሀገር ስለሆነች ነው፡፡ የአለም ንጉሥ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስመስሎ ስለሚሰራ የአንድነትና የሶስትነት አሰራር የተከተለ ነው።

ይኽንን ፍርድ ለአለም ለመግለጥ ኢትዮጵያ የግዕዝ ሐብቷን ይዛ ትገለጣለች፡፤ ይኽ ሰማያዊ ዕጣዋ ነው። የኢትዮጵያ ቦታ የሁሉም እናት፣ ፍጥረት የተለከባት ሰማያዊ የወርቅ ቀለበት ናት።  ይህቺን መንፈሳዊ ቀለበት አጥልቆ በብረት ቀጥቅጦ የሚገዛው የድንግል ማርያም ልጅ ነው። በርሱ ኃይል የኢትዮጵያ የኢካቦድ ዘመን ይጠቃለላል። በምድሪቱ የተበተኑ መናፍስት ሁሉ ጸጥ ይላሉ።

> "በዓለም የምትኖሩ ሁሉና በምድር የምትቀመጡ ሆይ፥ ምልክት በተራሮች ላይ በተነሣ ጊዜ እዩ፤ መለከትም በተነፋ ጊዜ ስሙ። 4፤ እግዚአብሔር። በፀሐይ ጮራ እንደ ደረቅ ትኩሳት፥ በአጨዳም ወራት እንደ ጠል ደመና ሆኜ በማደሪያዬ በጸጥታ ተቀምጬ እመለከታለሁ ብሎኛልና።" (ኢሳ. 18፡3)

ሁሉም ልቡንና አእምሮውን፣ ኃይሉንና ነፍሱን ሰትሮ ኢትዮጵያን ያዳምጣል።


### መ. በ42 ዲግሪ የተለካ የፍርድ ኮምፓስ።

ከላይ እንዳየነው 42 ቁጥር ከፍተኛ መንፈሳዊ ምሥጢርን ያዘለ እንደመሆኑ በተለያየ ፈርጁ የፍርድ ሚዛን መቀሰሪያ ሆኗል። በዚም መሠረት የ42 ቁጥር ብዜትና ክፋይ ፡የፍርድ ሥርዓት የተሰራበትን ቀመር ይገልጡልናል፡፤ የ42 ቁጥር ቀመሮች በሰንጠረዥ ላይ ተመልክተዋል፦

ሠንጠረዥ - የደብረ ሲና ቀመር

| 42 ዲግሪ | 42 | 42 | 42 | 42 |
|---|---|---|---|---|
| ሰማያዊ | 1 | 2 | 3 | 7 |
| ምድራዊ | 42 | 21 | 14 | 6 |
| የፍርዱ ባሕሪ | የምድያምን ሕግ ለእያንዳንዱ ነፍስ መመዘኛ | ለሁለቱ ቃል ኪዳኖች፡ እስራኤልና ኢትዮጵያ | የአዳምን ስደት የተመለከተ | የጽድቅን መንገድ የተመለከተ<br><br>ቤተ ክርስቲያን የተፈረደችበት ምስጢር |

## ሥዕል ፡ የ42 ዲግሪ የአዜብ ፍርድ በኮምፓስ ላይ ሲገለጥ




ይኸንን በእግዚአብሔር ስም በመንፈሳዊ ኮምፓስ ላይ የተቀረጸ ምስጢር መረዳት ንግሥተ አዜብ ከነነዌ ሰዎች  ጋር ሆና የምትፈርድበት የዚህ የኔ ትውልድ ዕጣ ነው።